


ችንጊስ ፡ አይትማቶቭ ።

ከችንጊስ፡ አይትማቶቭ።

# ጀ ሚ ላ ።

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡
ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

በጐበዜ ፡ ጣፈጠ ፡ ተተረጐመ ።

በሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ታተመ ።

እንደገናም ፡ ደግሞ ፡ ከአንዲት ፡ እንሥተኛ ፡ ከሆነች ፡ የእጅ ፡ ሥዕል ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እገኛለሁ ። ወደ ፡ ፊት ፡ ላለው ፡ ረዥም ፡ ጉዞዬ ፡ አንዲት ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ሊሰጠኝ ፡ እንዲችል ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ እሄድና ፡ የሥዕል ፡ ሸራዬን ፡ አተኩሬ ፡ እመለከታለሁ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ዘመዶች ፡ ከአገር ፡ ለመጐብኘት ፡ ሲመጡ ፡ የማይታይ ፡ መሆኑን ፡ አረጋግጣለሁ ። ከአንድ ፡ እውነተኛ ፡ የእጁ ፡ ጥበብ ፡ ሙያ ፡ ያልላቀ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ ምንም ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገር ፡ የለም ። መሬቱ ፡ እንዳለ ፡ በግልጽ ፡ ተሥሎአል ።

መሠረቱም ፡ የበልግ ፡ ወራት ፡ ሰማይ ፡ ሆኖ ፡ በተራሮች ፡ ሸንተረሮች ፡ ላይ ፡ ነፋስ ፡ ደመናዎችን ፡ ያንጐማልላቸው ፡ (ይነዳቸው፤) ነ

በር ። የወየቡ ፡ ሣሮች ፡ ሜዳውን ፡ ሸፍነውና ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የዘነበው ፡ ዝናም ፡ መንገዱን ፡ አጨቅይቶት ፡ ርጥብ ፡ ነበር ፡ የተንከፈረሩ ፡ ቁጥቋጦችም ፡ በጐዳናው ፡ ዳር ፡ የምድርን ፡ ትርኢት ፡ ያሳዩ ፡ ነበር ። የሁለት ፡ መንገደኞች ፡ ዱካዎችም ፡ አንድ ፡ ጋሪ ፡ ሄዶበት ፡ የነበረውን ፡ ድምድም ፡ ይከተሉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የመንገዱ ፡ ርቀት ፡ ዱካቸውን ፡ እያመነመነው ፡ ሄደ ። ሌላ ፡ እርምጃ ፡ ወስደው ፡ በነበረ ፡ ኖሮ ፡ ከገጹ ፡ ይጠፉ ፡ ነበር ፤ ከእነሱ ፡ አንዱ ፡... የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ነገሮችን ፡ እቀድማለሁ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሆነው ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ በነበርኩበት ፡ ዘመኔ ፡ ነው ። እሱም ፡ የጦርነቱ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ነበር ። ባንድ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ኩርስክና ፡ ኦሬል ፡ ላይ ፡ አባቶቻችንና ፡ ወንድሞቻችን ፡ ጠላትን ፡ ወጉ ። እኛ ፡ የአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጐልማሶችም ፡ በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ እንሠራ ፡ ነበርን ። የእኛ ፡ የጐልማሶች ፡ ያልጠነከሩ ፡ ትከሻዎችም ፡ የትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ ሸክሞችን ፡ መሸከም ፡ ነበረባቸው ። የመከር ፡ ወራትም ፡ ከሁሉ ፡ የጠነከረ ፡ ወራት ፡ ነበር ። እስከ ፡ አያሌ ፡ ሳምንቶች ፡ ድረስም ፡ ቀኖቹና ፡ ሌሊቶች ፡ በማሳዎቹ ፡ ውድማዎች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በባቡር ፡ ጣቢያ ፡ እህልን ፡ በማስረከብ ፡ እናሳልፍ ፡ ነበር ።

ባንዲት ፡ በጠረረች ፡ ዕለት ፡ ባዶ ፡ ጋሪ ፡ ይዤ ፡ ከጣቢያ ፡ ስመለስ ፡ ከማጨድ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ማጭዶቻችን ፡ ግለው ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ለትንሽ ፡ ጊዜ ፡ ለመመለስ ፡ ቁርጠኛ ፡ ሀሳቤን ፡ አደረግሁ ።

ባንዲት ፡ እኑሥተኛ ፡ ወንዝ ፡ መፍሰሻ ፡ አጠገብ ፡ በፀሐይ ፡ ግለት ፡ የደረቁ ፡ የአፈር ፡ ካብ ፡ የከበባቸው ፡ ሁለት ፡ ቤቶች ፡ አሉ ። ከካቦቹ ፡ ዙሪያዎችም ፡ ረግኸርም ፡ ዛፎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ካቦች ፡ ቤቶቻችን ፡ ናቸው ። ለብዙ ፡ ዓመታትም ፡ ወላጆቻችን ፡ አብረው ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተቀራርበው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። እኔ ፡ ከትልቁ ፡ ቤት ፡ ነበርኩ ። ገና ፡ ትዳር ፡ ያልያዙ ፡ ሁለት ፡ ታላቅ ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩኝ ። ሁለቱም ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ ተሠልፈው ፡ ስለነበር ፡ ከማንኛቸውም ፡ ወሬ ፡ አልደረሰንም ፡ ነበር ።

አባቴም ፡ ሽማግሌ ፡ አናጢ ፡ ነበር ። እሱም ፡ ማለዳ ፡ ጐሕ ፡ እንደቀደደ ፡ የጧት ፡ ፀሎቱን ፡ አድርሶ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ሄዶ ፡ እስከ ፡

ምሽት ፡ ድረስ ፡ የእናጢነት ፡ ተግባሩን ፡ ያከናውን ፡ ነበር ።

እናቴና ፡ ታናሽ ፡ እህቴ ፡ ብቻ ፡ እቤት ፡ ይውሉ ፡ ነበር ።

የቅርብ ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶቻችንም ፡ በአቅራቢያችን ፡ ይኖሩ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ በመንደረተኞቹ ፡ ዘንድ ፡ ትንሿ ፡ ቤት ፡ በመባል ፡ ትጠራ ፡ ነበር ። አያቶቻችንና ፡ ቅድመ ፡ አያቶቻችንም ፡ ወንድማማቾች ፡ ነበሩ ። አብረን ፡ እንዳንድ ፡ ቤተሰብ ፡ እንኖር ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ የቅርብ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ብዬ ፡ እጠራቸዋለሁ ። ሰዎቻችን ፡ ዘላኖች ፡ ከነበሩበት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ ዳሳቸውን ፡ እያፈረሱ ፡ ከነመንጋቸው ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ይዘዋወሩ ፡ እስከነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እንደዚሁ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ወግ ፡ ለዘለቄታ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አደረግን ። በመንደራችን ፡ ውስጥ ፡ የተራድዖ ፡ መኖር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችን ፡ ቤቶቻቸውን ፡ አጠገብ ፡ ላጠገብ ፡ ሠሩ ። በእውነትም ፡ ደግሞ ፡ ባልንጀራሞች ፡ ነገዶች ፡ ነን ። እስከ ፡ ወንዙ ፡ በሚደርሰው ፡ በአራልስካያ ፡ መንገድ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የኛ ፡ ወገኖች ፡ በሞላ ፡ ይኖሩበት ፡ ነበር ።



በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ እንደገባን ፡ ወዲያውኑ ፡ የትንሿ ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ ሞተ ። በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱንና ፡ ሁለት ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ትቶ ፡ ሞተ ። ሲያያዝ ፡ በወረደው ፡ በዘር ፡ ልማዳችን ፡ መሠረት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ የወለደች ፡ ሴት ፡ ከወገን ፡ እንዳትወጣ ፡ ይደረግ ፡ ነበርና ፡ አባቴ ፡ እንዲያገባት ፡ ተወሰነ ። የቅድመ ፡ አያቶቹ ፡ ወግና ፡ መንፈስም ፡ ይህን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አስገደደው ። ምክንያቱም ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

ሁለተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ ለማበርከት ፡ የተቻለው ፡ በዚሁ ፡ ሁኔታ ፡ ነበር ። ትንሽቷ ፡ ቤትም ፡ ራስዋን ፡ የቻለች ፡ የራስዋ ፡ የአትክልት ፡ ቦታና ፡ የራስዋ ፡ ከብት ፡ ነበራት ፤ በእውነቱ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንኖር ፡ ነበር ።

ትንሿ ፡ ቤትም ፡ እንደዚሁ ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ አስማርታ ፡ ታላቅየው ፡ ሰዲቅ ፡ ትዳር ፡ እንደያዘ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሄደ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በጊዜ ፡ የተራራቁ ፡ ቢሆኑም ፡ ደብዳበዎቻቸው ፡ ደርሰውን ፡ ነበር ።

እንደዚሁ ፡ በትንሿ ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ ኪቺ ፡ አጋ ፡ (ትንሿ ፡ እናት ፡) ብዬ ፡ የምጠራት ፡ ብቻና ፡ ምራቷ ፡ የሰዲቅ ፡ ሚስት ፡ ነበሩ ። ሁለቱም ፡ በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ ማሳዎች ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። ወጣትዋ ፡ እናቴም ፡ በጣም ፡ ደግ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላትና ፡ ትዕግሥተኛ ፡ ነበረች ። በማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ በዕድሜ ፡ ከእሷ ፡ ካነሡት ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ በይም ፡ በመቆፈር ፡ ሆነ ፡ ማሳዎችን ፡ በማጠጣት ፡ ዕኩል ፡ መሥራት ፡ ቻለች ። ዕድሏም ፡ የድካምዋ ፡ ተካፋይ ፡ የምትሆን ፡ ምራት ፡ አስገኝቶላት ፡ ነበር ። ጃሚላ ፡ ለአማቷ ፡ መልካም ፡ መቀናጆ ፡ ነበረች ። ምንም ፡ እንኳን ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ ቢኖራትም ፡ የማትደክምና ፡ ቀልጣፋ ፡ ነበረች ።

ጃሚላን ፡ ከልቤ ፡ እወዳት ፡ ነበር ። እሷም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ትወደኝ ፡ ነበር ። የተቃረብን ፡ ወዳጆች ፡ ነበርን ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በስማችን ፡ አንጠራራም ፡ ነበር ። ከልዩ ፡ ቤተሰቦች ፡ ብንሆን ፡ ኖሮ ፡ ጃሚላ ፡ ብዬ ፡ እጠራት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ ባለቤት ፡ ስለሆነች ፡ «ጅን ፡» (ሙሽሪት ፡) ብዬ ፡ እጠራት ፡ ነበር ። እሷም ፡ ደግሞ ፡ መልሳ ፡ «ኪቺኔ ፡ ባላ ፡» (ዋርሳዬ ፡ ትንሹ ፡ ልጅ ፡ ማለት ፡) ብላ ፡ ትጠራኝ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ አልነበርኩም ፤ ሁለታችንም ፡ በዕድሜ ፡ መኻል ፡ የቱንም ፡ ያህል ፡ አንበላለጥም ፡ ነበር ። የመንደሮቻችን ፡ ባሕልም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነበር ፤ ምራቶች ፡ ሁሉ ፡ የባሎቻቸውን ፡ ታናሽ ፡ ወንድሞች ፡ ኪቺኔ ፡ ባላ ፡ (ዋርሳዬ ፡) ብለው ፡ ይጠሩአቸው ፡ ነበር ።

እናቴም ፡ ሁለቱንም ፡ ቤቶች ፡ ታስተዳድር ፡ ነበር ። ታናሽ ፡ እህቴ ፡ ጉንጉን ፡ ፀጉርዋን ፡ በክር ፡ አሥራ ፡ እናታችንን ፡ ታግዝ ፡ ነበር ፡ እሷም ፡ በጣም ፡ የምታስገርም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። በእነዚያ ፡ አስቸጋሪ ፡ ዓመታት ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ በጥንካሬ ፡ ትሠራ ፡ የነበረው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይረሳኝም ። የሁለቱንም ፡ ቤቶች ፡ በጎችና ፡ ጥጆች ፡ ታሠማራና ፡ ታግድ ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ ለማገዶ ፡ የሚሆን ፡ እንጨት ፡ ሁልጊዜ ፡ ሰብራ ፡ ታቅርብ ፡ ነበር ። የእናቴን ፡ የብቸኝነት ፡ ኑሮ ፡ ማጽናናት ፡ የቻለችው ፡ አፍንጫ ፡ ደፍጣጣይቱ ፡ ታናሽ ፡ እህቴ ፡ ነበረች ። በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡

ስለነበሩት ፣ ልጆቿ ፡ ይሰማት ፡ የነበረውን ፣
ትካዜ ፣ ታስወግድላት ፡ ነበር ።
ታላቁ ፣ ቤተሰባችንም ፣ የመንፈስ ፡ ብር
ታትና ፡ የቤት ፡ ውስጥ ፣ ችግር ፣ ማስወገድ ፡
የቻለው ፡ በእናታችን ፣ ብርታት ፡ ነው ። የሁ
ለቱ ፡ ቤቶች ፣ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አስተዳዳሪ ፣
ነበረች ፤ ማለት ፡ ንብረት ፡ ጠባቂ ፡ ነበረች ።
ዘላን ፡ ከነበሩት ፣ አያቶቻችን ፡ ቤት ፡ ስትገባ ፡
ወጣት ፡ ልጃገረድ ፡ ሆና ፡ ቤተሰቡን ፡ በትክ
ክል ፡ በማስተዳደር ፡ ረገድ ፡ ሁልጊዜ ፣ ሥር
ዓታቸውን ፡ አክብራ ፡ ትከተል ፡ ነበር ። ብል
ሃቷ ፤ አስተዋይነቷና ፡ የቤት ፡ አስተዳደር ፡ ች
ሎታዋ ፡ በመንደሩ ፡ ግምት ፡ አስጣለባት ። እ
ቤት ፡ ውስጥ ፡ እናቴ ፡ የማናቸውም ፡ ጉዳይ ፡ ኃ
ላፊ ፡ ነበረች ። እውነት ፡ ለመናገርም ፡ መን
ደረተኞቻችን ፡ አባቴን ፡ የቤተሰቡ ፡ አለ
ቃ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አያስቡም ፡ ነበር ። ብዙ ፡
ጊዜያትም ፡ «ወደ ፡ ዑስታካ ፡ ሠራተኛው ፡ ቤ
ት ፡ አትሒዱ ፡ የሚያውቀውም ፡ ምሣሩን ፡ ብ
ቻ ፡ ነው ። ታላቂቱ ፡ እናታቸው ፡ የማናቸውም ፡
ነገር ፡ ኃላፊ ፡ ነች ። ወደ ፡ እሷ ፡ በመሄድ ፡ ብ
ዙ ፡ ጥቅም ፡ ታገኛላችሁ ፡» ይሉ ፡ ነበር ።



ምንም ፡ እንኳን ፡ ገና ፡ ወጣት ፡ ብሆ
ንም ፡ በቤት ፡ ጣጣችን ፡ እባዝን ፡ ነበር ፤ እን
ዲህ ፡ ለመሆን ፡ የበቃሁት ፡ ታላላቅ ፡ ወንድሞ
ቼ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ሄደው ፡ ስለነበር ፡
ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዋዛ ፡ አንዳንድ ፡ ጊ
ዜም ፡ ለቁም ፡ ነገር ፡ እታገል ፡ ነበር ። የሁለ
ቱም ፡ ቤቶች ፡ አለቃ ፡ ጠባቂና ፡ አብዪ ፡ ተ
ብዬ ፡ እጠራ ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ በመባሌ ፡ ተዝ
ናንቼ ፡ ይበልጥ ፡ ኃላፊነቴ ፡ ተሰማኝ ። ከዚህ
ም ፡ ሌላ ፡ ደግሞ ፡ እናቴ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡
ነፃ ፡ ስሜት ፡ ትደግፍና ፡ ታደፋፍረኝ ፡ ነበረች ።
ጥንቁቅና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምኞት ፡ ያለኝ ፡ አራሽ ፡
እሆን ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደች ። እንዳባቴ ፡ እንዳል
ሆን ፡ ተመኘች ፡ ምክንያቱም ፡ እሱ ፡ ዘመኑ
ን ፡ ያሳለፈው ፡ ግንዲላዎችን ፡ ሰንጥቆ ፡ በመላ
ግ ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።
እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጋሪዬን ፡ ባን
ድ ፡ ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ ሥር ፡ አላልቼ ፡ አኖርኩና ፡
ወደ ፡ ደጅ ፡ አምርቼ ፡ የጓዳችን ፡ መሪ ፡ የነ
በረውን ፡ አሮዝማትን ፡ ተመለከትሁ ። እንደ
ተለመደው ፡ ሁሉ ፡ ምርኩዙን ፡ እኮርቻው ፡
ላይ ፡ አብቶ ፡ በፈረስ ፡ ነበር ። እናቴም ፡ ከጕ

ኑ ፡ ቆማ ፡ ይከራከሩም ፡ ነበር ። ወደ ፡ እነሱ ፡
እንደቀረብኩ ፡ «ከቶ ፡ አይሆንም! አላህን ፡
አትፈራም? እህል ፡ የቋጠሩ ፡ ጆንያዎች ፡
አገላብጣና ፡ አንከባክባ ፡ በመሸከም ፡ በጋሪ ፡
ወስዳ ፡ የምታስረክብ ፡ ሴት ፡ የት ፡ ታይታ ፡
ትታወቃለች? የለም ፤ አይደለም ፡ ተው ፡ እባ
ክህ ፡ ምራቴን ፡ ትተህ ፡ ዘወር ፡ በል ፤ እንደ ፡ ለ
መደችው ፡ ሁሉ ፡ ሥራዋን ፡ ትቀጥል ። የቀኑ
ን ፡ ብርሃን ፡ ለይቼ ፡ ማወቅ ፡ አልችልም ። በሁ
ለት ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡
ለማለት ፡ ትሞክራለህ! አሁን ፡ ልጄ ፡ አድጋ ፡
ለመርዳት ፡ መብቃቷ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ።
ወገቤን ፡ ስለሚያመኝ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡
ተላውሼ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልቻልኩም ።
እስቲ ፡ ውሃ ፡ አጥቶ ፡ የጸወለገውን ፡ ቡቃያ ፡
ተመልከተው!» ብላ ፡ ስትናገረው ፡ ሰማኋት ።
የራስ ፡ ሻሽዋን ፡ እየደባበሰች ፡ መናገርዋም ፡
የመቆጣቷ ፡ ምልክት ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ አሮዝማት ፡ ተስፋ ፡ ቆ
ርጦ ፡ «ምን ፡ ሆንሻል? በማለት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
ተራመደ ። «በዚህ ፡ ባለ ፡ ምርኩዝ ፡ ፊንታ ፡



እግር ፡ ቢኖረኝ ፡ ኖሮ ፡ ልለምንሽ ፡ እመጣ ፡
ነበር? እራሴ ፡ የእህል ፡ ጆንያዎችን ፡ እጋሪ ፡
ላይ ፡ ጭኜ ፡ እንደተለመደው ፡ ፈረሴን ፡ እኮ
ለኩል ፡ ነበር! የሴት ፡ ሥራ ፡ አለመሆኑንም ፡
አውቃለሁ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ወንዶችን ፡ የት ፡ ላገ
ኝ ፡ እችላለሁ? የወታደሮችን ፡ ሚስቶች ፡ ለመ
ለመን ፡ የደፈርንበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይኸው ፡
ነው? ምራትሽ ፡ እንድትሄድ ፡ አትፈልጊም ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የእርሻ ፡ ኃላፊው ፡ ሹም ፡ ከራ
ሴ ፡ ላይ ፡ አይወርድም ። ወታደሮቹም ፡ ምግ
ብ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ ድር
ጅቱን ፡ ማሰናከላችን ፡ ነው ። ይህን ፡ ማስተ
ዋል ፡ አትችይምን?» ብሎ ፡ ተናገረ ።

አለንጋየን ፡ እየጐተትሁ ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡
ተጠጋሁ ። የቡድን ፡ ሹሙም ፡ እኔ ፡ መሆኔን ፡
ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በሀሳብ ፡ ተውጦ ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡
የፈገግታ ፡ ገጽ ፡ ታየበት ።

«መልካም ፡ ነው! ስለ ፡ ምራትሽ ፡ መሄ
ድ ፡ ፈቃደኛ ፡ ካልሆንሽ ፡ ኪቺኔ ፡ ባላ ፡ ዋር
ሳዋ ፡ ማንም ፡ እንዳይነካት ፡ ይፈልጋል ።»
በማለት ፡ በቅርታ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አሳየ ። «አትፍ
ሪ ፡ ሰይት ፡ መልካም ፡ ጐልማሳ ፡ ነው ። እን

ኑ ፡ ቆማ ፡ ይከራከሩም ፡ ነበር ። ወደ ፡ እነሱ ፡
እንደቀረብኩ ፡ «ከቶ ፡ አይሆንም! አላህን ፡
አትፈራም? እህል ፡ የቋጠሩ ፡ ጆንያዎች ፡
አገላብጣና ፡ አንከባክባ ፡ በመሸከም ፡ በጋሪ ፡
ወስዳ ፡ የምታስረክብ ፡ ሴት ፡ የት ፡ ታይታ ፡
ትታወቃለች? የለም ፤ አይደለም ፡ ተው ፡ እባ
ክህ ፡ ምራቴን ፡ ትተህ ፡ ዘወር ፡ በል ፤ እንደ ፡ ለ
መደችው ፡ ሁሉ ፡ ሥራዋን ፡ ትቀጥል ። የቀኑ
ን ፡ ብርሃን ፡ ለይቼ ፡ ማወቅ ፡ አልችልም ። በሁ
ለት ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ ጥልቅ ፡
ለማለት ፡ ትሞክራለህ! አሁን ፡ ልጄ ፡ አድጋ ፡
ለመርዳት ፡ መብቃቷ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ።
ወገቤን ፡ ስለሚያመኝ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡
ተላውሼ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አልቻልኩም ።
እስቲ ፡ ውሃ ፡ አጥቶ ፡ የጸወለገውን ፡ ቡቃያ ፡
ተመልከተው!» ብላ ፡ ስትናገረው ፡ ሰማኋት ።
የራስ ፡ ሻሽዋን ፡ እየደባበሰች ፡ መናገርዋም ፡
የመቆጣቷ ፡ ምልክት ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላም ፡ አሮዝማት ፡ ተስፋ ፡ ቆ
ርጦ ፡ «ምን ፡ ሆነሻል? በማለት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡
ተራመደ ። «በዚህ ፡ ባለ ፡ ምርኩዝ ፡ ፈንታ ፡



እግር ፡ ቢኖረኝ ፡ ኖሮ ፡ ልለምንሽ ፡ እመጣ ፡
ነበር? እራሴ ፡ የእህል ፡ ጆንያዎችን ፡ እጋሪ ፡
ላይ ፡ ጭኜ ፡ እንደተለመደው ፡ ፈረሴን ፡ እኰ
ለኩል ፡ ነበር! የቤት ፡ ሥራ ፡ አለመሆኑንም ፡
አውቃለሁ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ወንዶችን ፡ የት ፡ ላገ
ኝ ፡ እችላለሁ? የወታደሮችን ፡ ሚስቶች ፡ ለመ
ለመን ፡ የደፈርንበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይኸው ፡
ነው? ምራትሽ ፡ እንድትሄድ ፡ አትፈልጊም ፡
ነገር ፡ ግን ፡ የእርሻ ፡ ኃላፊው ፡ ሹም ፡ ከራ
ሴ ፡ ላይ ፡ አይወርድም ። ወታደሮቹም ፡ ምግ
ብ ፡ ያስፈልጋቸዋል ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ ድር
ጅቱን ፡ ማሰናከላችን ፡ ነው ። ይህን ፡ ማስተ
ዋል ፡ አትችይምን?» ብሎ ፡ ተናገረ ።

አለንጋየን ፡ እየጐተትሁ ፡ ወደ ፡ እነሱ ፡
ተጠጋሁ ። የቡድን ፡ ሹሙም ፡ እኔ ፡ መሆኔን ፡
ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ በሀሳብ ፡ ተውጦ ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡
የፈገግታ ፡ ገጽ ፡ ታየበት ።

«መልካም ፡ ነው! ስለ ፡ ምራትሽ ፡ መሄ
ድ ፡ ፈቃደኛ ፡ ካልሆንሽ ፡ ኪቹኔ ፡ ባላ ፡ ዋር
ሳዋ ፡ ማንም ፡ እንዳይነካት ፡ ይፈልጋል ፡»
በማለት ፡ በቅርታ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አሳየ ። «አትፍ
ሪ ፡ ሰይት ፡ መልካም ፡ ጐልማሳ ፡ ነው ። እን

ደ ፡ እሱ ፡ ያሉት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ እንጀራን ፡ የሚያተርፉልን ፡ ሁልጊዜም ፡ ለዘለቄታ ፡ ክንውኖችን ፡ የሚያስቡ ፡ ናቸው ፡» ባለ ፡ ጊዜ ፡ እናቴ ፡ ንግግሩን ፡ አቋረጠችው ።

«ምነው ፡ እቴ! እስቲ ፡ ራስህን ፡ ተመልከት ፡ ከርታቴ!» ብላ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ጠንቁላ ፡ ጮኸችብኝ ፡ «የራስ ፡ ጸጉርህም ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ ጋማ ፡ ረዝሞአል! አባትህ ፡ ማለፊያ ፡ ነው ፡ የልጁን ፡ እራስ ፡ ለመላጨት ፡ ያህል ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ የለውም ።»

«እንግዲህ ፡ ልጁ ፡ ከወላጆቹ ፡ ጋር ፡ ዛሬ ፡ እቤት ፡ ይዋልና ፡ ራሱን ፡ ይላጭ ።» ብሎ ፡ አሮዝማት ፡ ከናቴ ፡ ጋር ፡ ተነጋገረ ፡ «ሰይት ፤ ዛሬ ፡ እቤት ፡ ዋልና ፤ ፈረሶችህን ፡ ቀልብ ፤ ነገ ፡ ጧት ፡ ለጃሚላ ፡ ጋሪ ፡ እንሰጣታለን ። አብራችሁ ፡ ትሠራላችሁ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለእሷ ፡ ኃላፊ ፡ መሆንህን ፡ አትዘንጋ! አሁን ፤ ባይቢቼ ፡ አትስጊ ፤ ሰይት ፡ ይጠብቅሻል ። ሌላስ ፡ ምን ፡ አለ? ዳንያርን ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ እንዲሄድ ፡ አደርጋለሁ ። ታውቂዋለሽ ። ገራም ፡ ልጅ ፡ ነው ። እሱም ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ የተሰናበተ ፡ ነው ።



ሦስቱም ፡ እህሉን ፡ ወስደው ፡ ለጣቢያው ፡ ያስረክባሉ ፡ እንግዲህስ ፡ ምራትሽን ፡ ማን ፡ ደፍሮ ፡ ይጠጋታል? ትክክለኛ ፡ ነኝ? ሰይት ፡ አንተስ ፡ ምን ፡ ትላለህ? ጃሚላ ፡ ነጂዋ ፡ እንድትሆን ፡ እንፈልጋለን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እናትህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አትሰማም ፤ ስለዚህ ፡ አንተ ፡ እሷን ፡ አባብለህ ፡ ለማስረዳት ፡ ሞክር ።» አለ ።

እሱ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌ ፡ ሆኖ ፡ በመከረኝ ፡ ምክር ፡ ተደልዬ ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ከጃሚላ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጣቢያው ፡ መሄድ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ታየኝ ። አተኩሬ ፡ በመመልከት ፡ እናቴን ፡ እንዲህ ፡ አልኳት ።

«ምንም ፡ አትሆንም ፤ በመንገዳችንም ፡ ተኩሎች ፡ የሉም ።»

እንደ ፡ ደምበኛ ፡ ጋሪ ፡ ነጂ ፡ ጢቅ ፡ ብዬ ፡ ተፋሁና ፡ አሳቢ ፡ በመምሰል ፡ አለንጋየን ፡ እየጐተትሁ ፡ ተራመድሁ ።

«አዳምጭው!» በማለት ፡ በተናገርሁ ፡ ጊዜ ፡ እናቴ ፡ በመገረም ፡ ጮኸች ። ጥቂት ፡ የተደሰተች ፡ መስላ ፡ በድንገት ፡ ቁጡ ፡ ድምጽ ፡

አሰማች ፣ አንት ፡ ባለጌ ፡ ስለ ፡ ተኩሎች ፡ ምን ፡
ታውቃለህ!» አለች ።
«በጄ! እንግዲህ ፡ እሱ ፡ ማወቅ ፡ ካልቻ
ለ ፡ ምን ፡ ሊያውቅ ፡ ነው ፣ እሱ ፡ የሁለት ፡ ቤ
ተሰቦች ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነው ፣ ልትኮሪበትም ፡
ይገባሻል!» እንደገና ፡ እንዳትቆጣ ፡ አሮዝማት ፡
ወደ ፡ እኔ ፡ ተንጠራርቶ ፡ ወደ ፡ እሷም ፡ በመገ
ረም ፡ ተመለከታት ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ እናቴ ፡ አልተቃወመችም ፡ ነበር ።
በድንገት ፡ ራስዋን ፡ ደፍታ ፡ በኃይል ፡ ተነፈ
ሰች ።
«እሱ ፡ ከዚህ ፡ ስሜት ፡ በጣም ፡ ሩቅ ፡
ነው ። ገና ፡ ልጅ ፡ ነው ፣ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡
ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በሥራ ፡ ተጠምዶአል ። የኛ ፡
ባለቤቶች ፡ ወዴት ፡ እንዳሉ ፡ አላህ ፡ ብቻ ፡ ያ
ውቃል ። ቤቶቻችንም ፡ እንደተለቀቁ ፡ ሠፈ
ሮች ፡ ወና ፡ ሆነዋል ።»
አሁን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አንገፈገፈኝ ፡
ስለዚህ ፡ የእናቴ ፡ ቃላት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ሠፈሩ ።
ወደ ፡ ቤቱ ፡ መታጠፊያ ፡ በፍጥነት ፡ ተራመ
ድኩና ፡ አቧራ ፡ አፍሼ ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሄድኩ ፡
በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ለእህቴ ፡ ፈገግታ ፡ ምንም ፡



መልስ ፡ አልሰጠሁም ። አጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡
ለማገዶ ፡ የሚያገለግል ፡ እበት ፡ ትጠፈጥፍ ፡
ነበረች ። እበሩ ፡ ላይ ፡ ቁጢጥ ፡ ብዬ ፡ ተቀመ
ጥኩና ፡ ከአንድ ፡ ማንቆርቆሪያ ፡ እየቀዳሁ ፡
እጆቼን ፡ ታጠብሁ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡
ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ገባሁና ፡ አንድ ፡ ፍንጃል ፡ ኮ
ምጣጣ ፡ ወተት ፡ ጠጥቼ ፡ ሁለተኛውን ፡ ፍን
ጃል ፡ ወተት ፡ ከመስኮቱ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ የ
ዳቦ ፡ ፍርፋሪ ፡ ጨምሬ ፡ አስቀመጥሁ ።
እናቴና ፡ አሮዝማትም ፡ እስካሁን ፡ ድረ
ስ ፡ እደጅ ፡ ነበሩ ፣ ከርከራቸውን ፡ አቁመው ፡
በለስላሳ ፡ ቃል ፡ ይመላለሱ ፡ ነበር ። ስለ ፡ ወን
ድሞቼ ፡ ተነጋግረው ፡ ይሆናል ። እናቴም ፡ ራ
ስዋን ፡ አቀርቅራ ፡ በእጅጌዋ ፡ እንባዋን ፡ ታብ
ስ ፡ ነበረች ። አሮዝማትም ፡ በግልጽ ፡ ያጽና
ናት ፡ ነበር ። እናቴ ፡ ሩቅ ፡ በሆኑት ፡ ዛፎች ፡ ላ
ይ ፡ በመመልከት ፡ የተደናገራት ፡ ሁሉ ፡ ለል
ጆቿ ፡ የሚደርሳቸው ፡ ይመስል ፡ ነበር ።
በአሳዛኝ ፡ ሀሳቦቿ ፡ ተከዛ ፡ በመጨረሻ ፡
በአሮዝማት ፡ አሳብ ፡ የተስማማች ፡ ሆና ፡ ተ
ገኘች ። ዓላማው ፡ ስለተፈጸመለት ፡ በጣም ፡
ተደስቶ ፡ በልምጩ ፡ ፈረሱን ፡ መታ ፡ መ

ታ ፡ አደረገና ፡ ከአጥር ፡ ግቢው ፡ በሶምሶማ ፡
ወጣ ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እኔም ፡ ሆንኩ ፡ እናቴ ፡ ይ
ህ ፡ ሁሉ ፡ ከምን ፡ እንዲያደርሰን ፡ ወይም ፡
ምን ፡ እንደሚያስከትል ፡ አላወቅንም ፡ ነበር ።

ጃሚላም ፡ የሁለት ፡ ፈረሶች ፡ ጋሪ ፡ ለመ
ያዝ ፡ የማያቅታት ፡ ለመሆኑ ፡ አልተጠራጠር
ኩም ፡ ነበር ። መልካም ፡ የሴት ፡ ፈረሰኛ ፡ ነበ
ረች ፡ ምክንያቱ ፡ በባካይር ፡ መንደር ፡ ያንድ ፡
አዋቂ ፡ ፈረስ ፡ አርቢ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡
ነው ። የኛው ፡ ሰዲቅም ፡ ፈረስ ፡ አርቢ ፡ ነበር ፡
በፀደይ ፡ ወራት ፡ በሚደረገው ፡ የፈረስ ፡ እሽ
ቅድምድምም ፡ ጃሚላን ፤ አይቀድማትም ፡ ነበር ፡
ተብሎ ፡ ይወራል ። ምናልባት ፡ እንዲህ ፡ ኖሮ
አል ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የተቀደመው ፡ ሰዲቅ ፡
ጠለፋት ፡ ይላሉ ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ሁለቱም ፡
ተፋቅረው ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡
ተጋብተው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡት ፡ ለ
አራት ፡ ወራት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ግን ፡ ጦርነት ፡ ታወጀና ፡ ሰዲቅ ፡ እንዲሠለ
ፍ ፡ ተጠራ ።



ምክንያቱን ፡ ለይቼ ፡ ማወቅ ፡ አልችል
ም ፤ ምናልባት ፡ ከልጅነቷ ፡ ጀምሮ ፡ ከአባቷ ፡
ጋር ፡ ፈረሶችን ፡ ታግድ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡
ወንድም ፡ ሴትም ፡ ሆና ፡ ልጁ ፡ እሷው ፡ ብቻ ፡
ነበረች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በእሷ ፡ የወንድነት ፡ ጠባ
ይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆራጠኝነት ፡ አንዳን
ድ ፡ ጊዜም ፡ እልኸኝነት ፡ እየታዩባት ፡ ወን
ድ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ አቀላጥፋ ፡ ስታከ
ናውን ፡ ትታይ ፡ ነበር ። ከሌሎችም ፡ ሴቶች ፡
ጋር ፡ በመግባባት ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡
በማይገባ ፡ ያሽሙአጠጧት ፡ እንደሆን ፡ አታሳ
ልፋቸውም ፡ በቁጣ ፡ የሌላዩቱን ፡ ሴት ፡ ጸጉ
ር ፡ የነጨችበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ጐረቤቶችም ፡ «እንዴት ፡ ያለች ፡ ምራት ፡
አለችሽ? ከአንቺ ፡ ጋር ፡ ለመኖር ፡ መ
ጥታለች ። ምላሷ ፡ አንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ያህ
ል ፡ የረዘመ ፡ ነው! ሰውን ፡ ማክበርና ፡ ትሕት
ናም ፡ የላትም!» እያሉ ፡ ያሽሙአጥጡ ፡ ነበር ።

«እንዲህ ፡ በመሆንዋ ፡ ደስ ፡ ይለኛል!»
ብላ ፡ እናቴ ፡ ትመልስላቸው ፡ ነበር ። «ም
ራታችን ፡ ለሰው ፡ የምትመልሰው ፡ በቀጥታ ፡
ፊት ፡ ለፊት ፡ ነው ። ባለ ፡ ሁለት ፡ ፊት ፡ ከመ

ሆን ፡ ይሻላል ። የእናንተ ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ተወ ዳጆች ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ሆኖም ፡ የእነሱ ፡ ተወዳጅነት ፡ እንደ ፡ ገማ ፡ እንቁላል ፡ ነው ። በስተውጭ ፡ በኩል ፡ ማለፊያና ፡ ለስላሳ ፡ መስ ለው ፡ ይታያሉ ፡ ውስጣቸውን ፡ ብትመለከቱ ፡ ግን ፡ አፍንጫችሁን ፡ ትይዛላችሁ ፡» አለች ።

አማቶች ፡ በምራቶቻቸው ፡ እንደሚያደር ጉት ፡ ሁሉ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ በጀሚላ ፡ ላይ ፡ ከቶ ፡ የጭቆናና ፡ የማረም ፡ አስተያየት ፡ አል ነበራቸውም ። ለእሷ ፡ ደጐችና ፡ ያፈቅሩአትም ፡ ነበር ፤ የእነሱም ፡ ዋናው ፡ ምኞታቸው ፡ ለአላህና ፡ ለባልዋ ፡ ታማኝ ፡ እንድትሆን ፡ ነበር ።

አስተዋልኳቸው ። አራት ፡ ወንዶች ፡ ል ጆቻቸው ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ተሠልፈው ፡ ስለነ በር ፡ በጀሚላ ፡ መጽናናትን ፡ አግኝተው ፡ ነበር ፡ እሱም ፡ የሁለቱም ፡ ቤቶች ፡ ምራት ፡ ስለነበ ረች ፡ ስለ ፡ ደህንነትዋ ፡ ያሰቡበት ፡ ምክንያ ቱ ፡ ይኸው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የገዛ ፡ እናቷ ን ፡ እንኳን ፡ አላስተውላትም ። እሷም ፡ በቀ ላሉ ፡ ፍቅርዋን ፡ ለሌላ ፡ የማታበረክት ፡ ነበ ረች ። እናቴም ፡ በተፈጥሮዋ ፡ የበላይነት ፡ የ



ሚሰማትና ፡ ኃይለኛ ፡ ነበረች ። በራስዋ ፡ ሥር ዓት ፡ የምትኖርና ፡ ሕገጋትዋንም ፡ የምታከ ብር ፡ ነበረች ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፤ ፀደይ ፡ ሲመጣ ፡ አ ባቴ ፡ በልጅነቱ ፡ ሠፍቶ ፡ የነበረውን ፡ የዘላን ፡ ድንኳን ፡ እየተከለች ፡ የጥድ ፡ ቀንዘሎችን ፡ ታነድበት ፡ ነበር ። ብርቱ ፡ ሠራተኞች ፡ እን ድንሆን ፡ አሳደገችን ፡ ሽማግሌዎቻችንን ፡ እ ንድናከብርና ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ቤተሰብ ፡ መታ ዘዝን ፡ እንድናውቅ ፡ ፈለገች ።

በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጀሚላ ፡ ተስማሚ ፡ ምራት ፡ መስላ ፡ አልታየችም ፡ ነበር ። በእ ውነቱም ፤ ሽማግሌዎችዋን ፡ አከበረች ፡ ታዘዘ ቻቸውም ፡ በእነሱ ፡ ፊት ፡ አትርበተበትም ፡ ነበር ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጀርባዋን ፡ ግርዶሽ ፡ አድርጋ ፡ አታጉመተምትም ፡ ነበር ። ሌሎች ፡ ምራቶች ፡ ሲፈጽሙ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ሁልጊዜም ፡ በልቧ ፡ ያለውን ፡ ሀሳብ ፡ ትናገር ነበር ፡ ሀሳብዋን ፡ ለመግለጥም ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ ፍርሃት ፡ አይሰማትም ። እናቴም ፡ ሁልጊዜ ፡ ትደግፋትና ፡ ከእሷም ፡ ጋር ፡ ትስማማ ፡ ነበር ፡ ሆኖም ፡ በመጨረሻ ፡ ተናጋሪዋ ፡ እሷው ፡ ነበ ረች ።

የጃሚላ ፡ ግልጥነትና ፡ ቅንነትም ፡ እንደ ፡ ራስዋ ፡ ስለመሰላት ፡ የኋላ ፡ ኋላ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንዲት ፡ ኃይለኛ ፤ ባልትና ፡ ያላት ፡ እመቤት ፡ የቤት ፡ አስተዳዳሪ ፡ (ባይቢቼ ፡) እንደምትሆን ፡ በምሥጢር ፡ ያለመች ፡ መሆኑን ፡ አምናለሁ ።

«ልጄ ፡ ሆይ ፡ በስምምና ፡ ብሩክ ፡ ቤተሰብ ፡ መኻል ፡ ስለገባሽ ፡ አላህን ፡ አመስግኚ ፡» እያለች ፡ እናቴ ፡ መላልሳ ፡ ትናገር ፡ ነበር ። «ዕድልሽ ፡ ነው ። የሴት ፡ ተድላም ፡ ልጆችን ፡ መውለድና ፡ እተሙአላለት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ ነው ። አላህ ፡ ይመስገን ፡ እኛ ፡ ሽምግሌዎቹ ፡ ያጠራቀምነው ፡ ሁሉ ፡ አለሽ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ አብሮን ፡ እንደማይቀበርም ፡ ታውቂአለሽ ። ነገር ፡ ግን ፡ ክብራቸውንና ፡ ሕሊናቸውን ፡ በንጹሕ ፡ የሚጠብቁ ፡ ደስታ ፡ ለእነሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ዘወትር ፡ አስታውሽና ፡ ተጠንቀቂ!»

ነገር ፡ ግን ፡ ሁለቱን ፡ እናት ፡ አማቶችዋን ፡ ያስቸገረ ፡ ነገር ፡ ነበር ፤ እንደ ፡ ሕፃንነትዋ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስዋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ። በድንገት ፡ ድምጿን ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ በደስታ ፡ ትስቅ ፡ ነበር ። ከሥራ ፡ ስትመለስም ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ 



ቤት ፡ በመግባት ፡ ፈንታ ፤ ወደ ፡ ጓሮ ፡ ትሮጥ ፡ ነበር ፡ የቦይን ፡ ጉድጓድም ፡ ትረግጠው ፡ ነበር ። እንደገናም ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ ግልጥ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ የመጀመሪያዪቱን ፡ አማትና ፡ የሁለተኛዪቱንም ፡ አማት ፡ አንገት ፡ ተጠማጥማ ፡ አቅፋ ፡ ትስማቸው ፡ ነበር ።

ጃሚላ ፡ ዜማ ፡ ማዜም ፡ ወደደች ። የሽማግሌዎች ፡ መኖር ፡ ሳይሰማት ፡ ሁልጊዜ ፡ ታንጕራጕር ፡ ነበር ። በግልጥም ፡ እንደዚህ ፡ ያለችው ፡ ምራት ፡ ጠባይ ፡ በመንደራችን ፡ ውስጥ ፡ ከልማዳችን ፡ ጋር ፡ ስምም ፡ አልነበረም ። ሆኖም ፡ ሁለቱም ፡ አማት ፡ እናቶች ፡ ጃሚላ ፡ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ ትበርዳለች ፡ ሁሉስ ፡ በልጅነታቸው ፡ ዘመን ፡ እንደዚሁ ፡ አልነበሩምን? በመባባል ፡ ይጽናኑ ፡ ነበር ። እንደተረዳሁት ፡ ሁሉ ፡ በሞላ ፡ ዓለም ፡ ከጃሚላ ፡ የሚሻል ፡ አይገኝም ። በአጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ እየተሩአሩአጥን ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ጨዋታዎችን ፡ እየተሳሳቅን ፡ እንጫወት ፡ ነበር ።

ጃሚላ ፡ በጣም ፡ ቆንጆ ፡ ነበረች ። አቋቋመ ፡ መልካምና ፡ ለዛ ፡ ያላት ፡ የራስ ፡ ጸጉርዋም ፡ ለሁለት ፡ ተከፍሎ ፡ የተጐነጐነና ፡ ራሷም ፡

ላይ ፡ ያሠረችው ፡ ነጭ ፡ ሻሽ ፡ ጠየም ፡ ላለ ፡ መልኳ ፡ ለዛ ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ። ፈገግታን ፡ ባሳየች ፡ ጊዜም ፡ ጥቁር ፡ ዓይኖቿ ፡ ያበሩ ፡ ነበር ፤ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ ለዛ ፡ ቢስ ፡ የሆኑ ፡ ዘፈኖችን ፡ ስትሰማ ፡ ደግሞ ፡ ተወዳጆች ፡ ዓይኖቿ ፡ ይንቀለቀሉ ፡ ነበር ።

ወጣቶች ፤ በተለይም ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ የተመለሱት ፡ ሰዎች ፡ በእሷ ፡ ይሳቡ ፡ ነበር ። ጃሚላም ፡ አዘወትራ ፡ ትቀልድ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በቀልድ ፡ መልክ ፡ ወሰን ፡ የሚያልፉትን ፡ ሳታሳልፍ ፡ ትቆጣጠር ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፤ ዘወትር ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ይዞታ ፡ እቃወም ፡ ነበር ። ታናሽ ፡ ወንድሞች ፡ በእህቶቻቸው ፡ እንደሚቀኑ ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ እቀናባት ፡ ነበር ። አንድ ፡ ጐልማሳ ፡ ከእሷ ፡ ጋር ፡ ሲነጋገር ፡ ያየሁ ፡ እንደሆነ ፡ ንግግራቸውን ፡ ለማቋረጥ ፡ የተቻለኝን ፡ ያህል ፡ እጥር ፡ ነበር ። አፉአጭና ፡ በጥላቻ ፡ ዓይን ፡ እመለከተዋለሁ ። «ተጠንቀቅ ፤ የወንድሜ ፡ ባለቤት ፡ ናት ፡ የሚጠብቃት ፡ የሌለ ፡ አይምሰልህ!» እል ፡ ነበር ።

በእዚህ ፡ ጊዜ ፡ በማጋነን ፡ ሁኔታ ፡ ዘው ፡ ብዬ ፡ እንግግራቸው ፡ መኻል ፡ እገባና ፡ በአ



ጃቢዎቿ ፡ አፈዛለሁ ። እንዲህ ፡ ለማድረግ ፡ ሳይሳካልኝ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ደግሞ ፡ ራሴ ፡ የዞረ ፡ እመስልና ፡ ጸጉሬን ፡ እያንቀሳቀስኩ ፡ እጀንናለሁ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ጐልማሶቹ ፡ ከት ፡ ብለው ፡ ይስቃሉ ።

«ተመልከቱት! ለምን ፤ ዋርሳው ፡ ነች ። ይህስ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አይደለምን? ለምን ፡ አናውቅም ፡ ነበር!» ይላሉ ።

ራሴን ፡ ለመግዛት ፡ ሞከርኩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጆሮቼ ፡ ይግላሉ ፡ የልብ ፡ እንባም ፡ ያንቀኛል ። ሆኖም ፡ ዋርሳዬ ፡ ጃሚላ ፡ አስተዋለችኝ ። በውስጧ ፡ ሊገነፍል ፡ የደረሰውን ፡ ሳቅ ፡ በማፈን ፡ በግልፍተኝነት ፡ ጽኑ ፡ ሀሳብዋን ፡ ለመግለጥ ፡ ትጠይቃለች ።

«ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ዋርሳን ፡ መጠየቅ ፡ ተገቢ ፡ ይመስላችኋልን? ምናልባት ፡ እናንተ ፡ ከመጣችሁበት ፡ እንዲህ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ፤ እዚህ ፡ ግን ፡ መሆን ፡ አይችልም ። ና ፤ ዋርሳዬ ፡ ኪቺኔ ፡ ባላ ፡ አናዳምጣቸውም!» ጐልማሶቹን ፡ እያሳየች ፡ በኩራት ፡ ራሷን ፡ ዘወር ፡ ታደርጋለች ። የንቀት ፡ መልክ ፡ በማሳየት ፡ ከዚያ ፡

ብድግ ፡ ብለን ፡ ስንሄድ ፡ ለራስዋ ፡ ፈገግታን ፡
ታሳያለች ።

በፈገግታዋም ፡ ቅርታና ፡ ደስታ ፡ ተጣ
ምረው ፡ ይታዩባት ፡ ነበር ። ምናልባትም ፡ ታ
ስብ ፡ ኖሮአል ። «ቂል ፡ ልጅ ፡ ከቶ ፡ ብፈልግ ፡
የሚያግደኝ ፡ ሰው ፡ ይኖር ፡ ይመስልሃልን? ቤተ
ሰቡ ፡ በሞላ ፡ ስለላ ፡ ሊያደርግብኝ ፡ ይችላል ፤
ዳሩ ፡ ግን ፡ እንደፈቀድሁት ፡ ማድረግ ፡ እችላ
ለሁ ፡» ብላ ፡አስባለች። በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ጊዜያት
ም ፡ ዝም ፡ እል ፡ ነበር ። አዎ ፡ በጀሚላ ፡ እቀ
ና ፡ ነበር ፡ አከበርኋት ፤ ዋርሳዬ ፡ በመሆንዋ ፡
በውበቷ ፡ በነፃ ፡ ፈቃደኝነቷና ፡ በግዴለሽነቷ ፡
እኮራባት ፡ ነበር ። እጅግ ፡ በጣም ፡ የምንፋቀር ፡
ስለነበርን ፡ በመሓላችን ፡ የተሰወረ ፡ ምሥጢ
ር ፡ አልነበረም ።

በጦርነቱ ፡ ዘመንም ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፡
ብቻ ፡ በመንደራችን ፡ ቀርተው ፡ ነበር ። በእ
ንደዚህ ፡ ባለው ፡ ሁናቴ ፡ በመጠቀም ፡ አንዳ
ንድ ፡ ጐልማሶች ፡ የብልግናን ፡ ሙያ ፡ ያሳዩ ፡
ነበር ፤ ሴቶችንም ፡ ያፌዙባቸው ፡ ነበር ፡ «ል
ታደርጉት ፡ የሚገባችሁ ፡ የምትፈልጉአትን ፡
ሴት ፡ በጣታችሁ ፡ መጥቀስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እ



ንጂ ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ለምን ፡ ትነታረካላችሁ?»
ይባበሉ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ድርቆሽ ፡ ሲከመር ፡ ሳለ ፡
ዝምድናው ፡ ሩቅ ፡ የሆነው ፡ ዑስማን ፡ ከጀሚ
ላ ፡ ጋር ፡ እፍ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ አድሮበት ፡ ነበር ።
ማንም ፡ ሴት ፡ ብትሆን ፡ የማትቋቋመው ፡ መሆ
ኑን ፡ አምኖበት ፡ ነበር ። ጀሚላ ፡ ግን ፡ ተቀም
ጣ ፡ ከነበረችበት ፡ ከክምሩ ፡ ጥላ ፡ ብድግ ፡ ብ
ላ ፡ በቁጣ ፡ እጁን ፡ ገፈተረችው ፤

«ተወኝ!» ብላ ፡ በሐዘን ፡ ፊት ፡ ነሣችው ።
ቀጥላም ፡ «የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እንዳንተ ፡ ካሉት ፡ ወ
ጣት ፡ አለሌዎች ፡ ምን ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል!»
አለችው ።

ዑስማንም ፡ ከድርቆሹ ፡ ክምር ፡ ተደግ
ፎ ፡ የረጠበ ፡ ከንፈሩን ፡ በንቀት ፡ ሽምቅቅ ፡
አደረገ ።

«ድመት ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ርቆ ፡ የተ
ሰቀለ ፡ ሥጋ ፡ ስታይ ፡ ትንቃለች ። ለማግኘት
ስ ፡ አጥብቀሽ ፡ ለምን ፡ ትጥርይለሽ? በጣም ፡
ጉጉ ፡ ስለመሆንሽ፡ ልወራረድ ፡ እችላለሁ ።
ስለዚህ ፡ ስለምን ፡ አጥብቀሽ ፡ በኃይል ፡ ትንጠ
ራርያለሽ?»

ጀሚላም ፡ ተንኰራደደች ።

«ምናልባት ፡ ይሆናል! ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዕጣችን ፡ ነው ። አንተ ፡ ቂል ፡ ነህ! ከመሳቅ ፡ በቀር ፡ ስለሚሻል ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ አትችልም ። እኔም ፡ የአንድ ፡ ኮስታራ ፡ ወታደር ፡ ለአንድ ፡ መቶ ፡ ዓመታትም ፡ ቢሆን ፡ መበለቱ ፡ ሆኜ ፡ እንደእናንተ ፡ ባላችሁት ፡ ላይ ፡ ልተፋባችሁ ፡ እንኳን ፡ አልፈቅድም ። ታስጠሉኛላችሁ ። የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ባልሆነ ፡ ኖሮ ፡ በዓይኑ ፡ ሙሉ ፡ እንኳን ፡ ያሚያያችሁ ፡ አልነበረም ፡» አለች ።

«የምለውም ፡ ይህ ፡ ነው! የጦርነት ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ የባልሽ ፡ አለንጋ ፡ ሳይጨርፍሽ ፡ ስድ ፡ ሆነሽ ፡ ትገኛለሽ ፡» ሲል ። አሁንም ፡ ዑስማን ፡ ተነፈሰ ። «አዬ ፡ የኔ ፡ ሚስት ፡ በሆንሽ ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ አትናገሪም ፡ ነበር ። »

በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ጀሚላ ፡ ዘላ ፡ ልታንቀው ፡ ደርሳ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እሱ ፡ ጋር ፡ መነታረክ ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳች ፤ አመለካከትዋም ፡ በቁጣ ፡ የተሞላ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ በንቀት ፡ ተፍታበት ፡ መንሽዋን ፡ ብድግ ፡ አድርጋ ፡ ጉዞዋን ፡ ቀጠለች ።



እኔም ፡ ከሣሩ ፡ ክምር ፡ በስተኋላ ፡ እጋሬ ፡ ላይ ፡ ነበርኩ ። ጀሚላም ፡ እኔን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ አኳኋኔ ፡ በመረዳት ፡ ፊቷን ፡ መለስ ፡ አደረገች ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ እሷ ፡ ሳትሆን ፡ የተዋረድኩት ፡ እኔው ፡ መሆኔ ፡ ተሰማኝ ፡ የተናቅሁትም ፡ እኔው ፡ ስለሆንኩ ፡ ተቆጣኋት ፤ አዋኪም ፡ አልኳት ።

«ከእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አለሽ? ስለምንስ ፡ ታነጋግሪአቸዋለሽ?»

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ የጀሚላ ፡ ፊት ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ጥቁር ፡ ደመና ፡ መስሎ ፡ ዋለ ። ምንም ፡ አላነጋገረችኝም ፤ እንደወትሮዋም ፡ አልሳቀችም ፤ ጋሪውን ፡ ሣር ፤ እንደተጫነ ፡ ወደ ፡ እሷ ፡ ባቀረብኩት ፡ ጊዜ ፡ መንሿን ፡ አነሳችና ፡ ከሣሩ ፡ አንስታ ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ አደረገች ። እንዲህ ፡ ለማድረግም ፡ የበቃችው ፡ እሷ ፡ ከእኔ ፡ ለመሰወር ፡ ስለነበራት ፡ የብስጭት ፡ ጉዳይ ፡ እንዳላነጋግራት ፡ ፊቷን ፡ ከእኔ ፡ ለመከለል ፡ ነበር ። ሣሩንም ፡ መልሳ ፡ ከጋሪው ፡ ላይ ፡ ታኖርና ፡ ሌላም ፡ ለማምጣት ፡ ትጣደፋለች ። ጋሪው ፡ በፍጥነት ፡ ሞላ ። ከእዚያ ፡ ተነስቼ ፡ ጋሪዬን ፡ እየነዳሁ ፡ መንገዴን ፡

በቀጠልኩ ፡ ጊዜ ፤ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ብመለከታት ፡ በሐሳብ ፡ ተውጣ ፡ የመንጃን ፡ እጀታ ፡ በትካዜ ፡ ደገፍ ፡ ብላ ፡ አየኋት ። ቀጥላም ፡ ሥራዋን ፡ መሥራት ፡ ጀመረች ።

የመጨረሻውን ፡ ጋሪ ፡ ከጫን ፡ በኋላ ፡ ጃሚላ ፡ ረዘም ፡ ላለ ፡ ጊዜ ፡ የፀሐይዋን ፡ መጥለቅ ፡ አተኩራ ፡ ትመለከትና ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስላለው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ የማታስብና ፡ የረሳችው ፡ ትመስል ፡ ነበር ። እዚያም ፡ ከወንዙ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ከካዛኽ ፡ ሜዳ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ዝግ ፡ ያለችው ፡ የመከር ፡ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ እቶን ፡ እሳት ፡ ትጋረፍ ፡ ነበር ። ከአድማስ ፡ ማዶ ፡ በዝግታ ፡ በመጥለቅ ፡ ላይ ፡ ነበረች ። የተበታተኑትን ፡ ደመናዎች ፡ በቀላቷ ፡ እየነካችና ፡ የመጨረሻ ፡ ጨረሮችዋንም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ቀለም ፡ ዓይነት ፡ በለበሰው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ትፈነጥቅ ፡ ነበር ። ጃሚላም ፡ የፀሐይን ፡ ጥልቀት ፡ ተመለከተችና ፡ ከልብ ፡ ደስ ፡ አላት ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ተአምር ፡ የሆነ ፡ መስሎአት ፡ ነበር ። ፊቷም ፡ በገርነት ፡ ፈገግ ፡ አለ ፤ የጸወለጉት ፡ ከንፈሮችዋም ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ከንፈሮች ፡ ፈገግታን ፡ አሳዩ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በምላሴ ፡



ጫፍ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ገና ፡ ላልተወረወሩት ፡ ዘለፋዎቼ ፡ መልስ ፡ የሚሆኑ ፡ ዘወር ፡ አለችና ፡ እንደፈቱ ፡ ንግግራችንን ፡ በመቀጠል ፤

«ዋርሳዬ ፡ ሆይ ፤ ስለ ፡ እሱ ፡ አታስብ ፡ አታዳምጠውም! በውነቱ ፡ ሰው ፡ ይመስልሃልን?» ጃሚላም ፡ የፀሐይን ፡ ጨርሶ ፡ መጥለቅ ፡ እየጠበቀች ፡ ዝም ፡ አለች ። ከእዚያ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የትካዜ ፡ እስትንፋስ ፡ ተነፈሰችና ፡ «እንደ ፡ ዑስማን ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ ምን ፡ ማወቅ ፡ ይችላል? ማንም ፡ ቢሆን ፡ ያን ፡ ማወቅ ፡ አይችልም ። ምናልባትም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በሞላ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ አይገኝም ፡ ይሆናል ፡ » አለች ።

ፈረሶቹን ፡ ስመልስ ፡ ሳለ ፡ ጃሚላ ፡ ብድግ ፡ ብላ ፡ ጥቂት ፡ ሴቶች ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ሥፍራ ፡ ሄደች ፡ በደስታ ፡ እንደ ፡ መረዋ ፡ ድምጽ ፡ ይሰማ ፡ የነበረውን ፡ ድምጽዋን ፡ እሰማ ፡ ነበር ። በእሷ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰው ፡ መለወጥ ፡ ጉዳይ ፡ አብራርቶ ፡ ለማስረዳት ፡ ያዳግታል ። ምናልባትም ፡ የፀሐይ ፡ ጥልቀት ፡ ሀሳብዋን ፡ አረጋግቶት ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዕ

ለቱ ፥ ተግባርዋ ፡ በመገላገልዋ ፡ ተደስታ ፡ ይሆናል ። ድርቆሽ ፡ ተቆልሎበት ፡ በነበረው ፡ ጋሪ ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ ተቀመጥኩና ፡ ጃሚላን ፡ እመለከት ፡ ጀመር ። ነጭ ፡ የራስ ፡ ሻሽዋን ፡ ከራስዋ ፡ ላይ ፡ አንስታና ፡ ጥላ ፡ አርፎበት ፡ በነበረው ፡ በታጨደው ፡ መስክ ፡ አቋርጣ ፡ እጆችዋን ፡ እያርገበገበች ፡ ነፋስም ፡ ቀሚስዋን ፡ እያውለበለበው ፡ የልብ ፡ ወዳጅዋ ፡ የነበረችውን ፡ ልጃገረድ ፡ ፍለጋ ፡ ሮጣ ፡ ሄደች ። «ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ዑስማን ፡ ጉዳይ ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ያሳስባል!» ፈረሶቼንም ፡ መታትቼ ፡ ቼ ፡ ብዬ ፡ ጮኽሁ ።

በዚያን ፡ ዕለትም ፡ የጓድ ፡ መሪውን ፡ ምክር ፡ ተቀብዬ ፡ አባቴ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመልሶ ፡ እራሴን ፡ እንዲላጨኝ ፡ ተጠባበቅሁ ። እስከዚያም ፡ ድረስ ፡ ወንድሜ ፡ ሰዲቅ ፡ ልኮአቸው ፡ ለነበረው ፡ ደብዳቤዎች ፡ መልስ ፡ ለመጻፍ ፡ ተደላድዬ ፡ ቁጭ ፡ አልኩ ። በዚህም ፡ ደግሞ ፡ ያልተጻፉ ፡ ደንቦች ፡ ይገኛሉ ፤ ወንድሞቼም ፡ ደብዳቤዎቻቸውን ፡ አድራሻ ፡ በአባቴ ፡ ስም ፡ አድርገው ፡ ስለነበረ ፡ የመንደራችን ፡ ፖስተኛ ፡ ግን ፡ ለእናቴ ፡ አስረክቦ ፡ ነበር ። አንብቦና ፡ መልስ ፡ መስጠቱ ፡ ግን ፡ የእኔ ፡ ተግባር ፡ ነበር ። ደብዳቤውን ፡ ከመግለጤ ፡ በፊት ፡ ሰዲቅ ፡ የጻፈውን ፡ በትክክል ፡ ተገንዝቤ ፡ ነበር ። ደብዳቤዎቹም ፡ ባንድ ፡ በረት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኙ ፡ ጠቦቶች ፡ ተመሳሳይ ፡ ነበሩ ። ሰዲቅም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሲጽፍ ፡ በሰላምታ ፡ ይጀምርና ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ። «ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ የምልከው ፡ በፖስታ ፡ ሆኖ ፡ መዓዛው ፡ በሚጥምና ፡ አበቦች ፡ ፈክተው ፡ በሚገኙበት ፡ በታላስ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ለሚገኙት ፡ ዘመዶቼ ፡ ነው ፤ በጣም ፡ የምወደዎት ፡ የተከበሩ ፡ አባቴ ፡ ጆልቼባይ ፡ ሆይ ፡» ብሎ ፡ ከዚህም ፡ ለጥቆ ፡ የእናቴንና ፡ የእናቱን ፡ እንደዚሁ ፡ የቀረነውን ፡ ቤተሰብ ፡ ስሞችም ፡ በየእድሜአችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይጽፋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ነገዳችንና ፡ ስለ ፡ ቅርብ ፡ ዘመዶቻችን ፡ ደህንነት ፡ ይጽፍና ፡ በደብዳቤው ፡ መጨረሻ ፡ መስመር ፡ ላይ ፡ በጥድፊያ ፡ እንደጻፈው ፡ መስሎ ፡ «ለባለቤቴ ፡ ለጃሚላ ፡ ሰላምታዬን ፡ አድርሱልኝ ፡» ይል ፡ ነበር ።

በእውነትም ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ካሉ ፡ መንደሩ ፡ በቅርብ ፡ ዘመዶች

ና ፡ በወገን ፡ ተሞልቶ ፡ ሳለ ፡ የራስን ፡ ባለቤት ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ መጥራት ፡ የማይገባ ፡ ነው ። በእሷ ፡ አድራሻ ፡ በቀጥታ ፡ አይጻፍም ። ሰዲቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እያንዳንዱ ፡ ክብሩን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ የሚያደርገው ፡ ነው ። ይህ ፡ የማያከራክር ፡ የደረጀ ፡ ባሕል ፡ ነው ። ምንም ፡ ክርክር ፡ የማያስከትል ፡ ቀዋሚ ፡ ደንብ ፡ ነው ። እኛም ፡ ደግሞ ፡ በበኩላችን ፡ ይህ ፡ ይገባል ፡ ወይንስ ፡ አይገባም ፡ ብለን ፡ አንወያይበትም ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ደብዳቤ ፡ በናፍቆት ፡ ስንጠብቀው ፡ የነበረ ፡ ደስታን ፡ የሚያጐናጽፈን ፡ ነው ።

እናቴም ፡ ደብዳቤዋን ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ታስነብበኛለች ። ቀጥሎም ፡ በተቀደሰ ፡ ፍቅር ፡ የሥራ ፡ ብዛት ፡ በጐለደፉት ፡ ጣቶቿ ፡ ደብዳቤውን ፡ ብድግ ፡ ታደርግና ፡ ለመብረር ፡ ክንፎቿን ፡ እንደዘረጋች ፡ ወፍ ፡ መስላ ፡ ትታያለች ። በመጨረሻም ፡ ሥራ ፡ ያሻከራቸው ፡ ጣቶቿ ፡ ደብዳቤውን ፡ እንደሚገባ ፡ ለማጠፍ ፡ ተቸገሩ ።

«እዬ! የተወደዳችሁ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ ደብዳቤዎቻችሁን ፡ እንደተከበረ ፡ ዕቃ ፡ እንጠብቃቸዋለን!» ዓይኖቿ ፡ በእንባ ፡ ሞልተው ፥



«አባቱ ፡ እናቱና ፡ ዘመዶቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ እንዳሉ ፡ ይጠይቃል ። እኛን ፡ ምን ፡ ይደርስብናል? እቤታችን ፡ በትውልድ ፡ አገራችን ፡ አለን! እናንተስ ፡ እዚያ ፡ እንዴት ፡ ናችሁ? በሕይወት ፡ ለመኖራችሁ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ላኩልን ፤ የምንፈልገውም ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሌላ ምንም ፡ ነገር ፡ ከናንተ ፡ አንሻም ።»

እናቴም ፡ የታጠፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ደጋግማ ፡ ከተመለከተች ፡ በኋላ ፡ ባንዲት ፡ ትንሽ ፡ የቆዳ ፡ አኮፋዳ ፡ ውስጥ ፡ ከሌሎቹ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ጋር ፡ ደባልቃ ፡ በትልቁ ፡ ሳጥን ፡ አግብታ ፡ ትቆልፍባቸዋለች ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሰዲቅ ፡ ደብዳቤ ፡ «ማራቶቭ ፡» የሚል ፡ ምልክት ፡ ተጽፎበት ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ታሞ ፡ ሀኪም ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። ሰዲቅም ፡ በአላህ ፡ አጋዥነት ፡ ለበልግ ፡ ወራት ፡ አገሬ ፡ እገባለሁ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ። ስለዚሁ ፡ ጉዳይም ፡ አስቀድሞም ፡ ጽፎ ፡ ስለነበረ ፡ እንደገና ፡ ስለመገናኘታችን ፡ በናፍቆት ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበርን ።

በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ጃሚላ ፡ ከቤት ፡ ስለነበረች ፡ ደብዳቤውን ፡ እንድታነበው ፡ ተፈቀደላት ።

የታጠፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ብድግ ፡ ባደረገች ፡ ጊ ዜ ፡ ዓይነ ፡ አፋርነት ፡ እንደተሰማት ፡ ገባኝ ፡ መ ስመሮቹንም ፡ በስስት ፡ ገጽ ፡ አነበበች ። ማንበ ብዋን ፡ እንደ ፡ ቀጠለችም ፡ ትከሻዎችዋ ፡ ዛሉ ፡ እፊትዋ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ የማፈር ፡ ቅ ላትም ፡ ከጉንጮችዋ ፡ ላይ ፡ ፈገግ ፡ ማለት ፡ ጀመረ ። አፍራ ፡ የመጨረሻ ፡ መስመር ፡ ስታ ነብ ፡ ቀዝቃዛ ፡ በሆነ ፡ ግድየለሽነት ፡ ደብዳ ቤውን ፡ ለእናቴ ፡ መልሳ ፡ ሰጠች ፡ አመላለስዋ ም ፡ ተውሳ ፡ የነበረችውን ፡ ዕቃ ፡ እንደመመለ ስ ፡ ያህል ፡ ነበር ።

እናቴም ፡ የምራትዋን ፡ ሁኔታ ፡ የቻለች ውን ፡ ያህል ፡ ተገነዘበችና ፡ ልታጽናናትና ፡ ልታስደስታት ፡ ፈለገች ። ደብዳቤዎቹ ፡ የተቀ መጡበትን ፡ ትልቅ ፡ ሳጥን ፡ በመመልከት ፤

«ምን ፡ ሆንሻል?» ትላት ፡ ነበር ። «በመደ ሰት ፡ ፈንታ ፡ መከፋትሽን ፡ ልብ ፡ አድርጊ! በወታደርነት ፡ ተግባር ፡ ከሀገሩ ፡ የወጣው ፡ ያ ንቺ ፡ ባል ፡ ብቻ ፡ ይመስልሻል? በሥቃይ ፡ ውስጥ ፡ ያለሽው ፡ አንቺ ፡ ብቻ ፡ አይደለሽም ። ሕዝባችን ፡ በሞላ ፡ ደሙን ፡ እያፈሰሰ ፡ ነው ። ከሌሎቹ ፡ ጋር ፡ መታገሥ ፡ ይገባሻል ። ብቻ



ቸውን ፡ ያልሆኑና ፡ ባሎቻቸውን ፡ የማይናፍ ቁ ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙ ፡ ይመስልሻል? ብትፈቅ ጂ ፡ ብቸኝነትሽ ፡ ይሰማሽ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አትግ ለጪው ፡ ስሜትሽን ፡ ለራስሽ ፡ አድርጊ ።»

ጃሚላም ፡ ምንም ፡ አልተናገረችም ፡ ዳ ሩ ፡ ግን ፡ በትካዜ ፡ የተሞላው ፡ ሰውነቷ ፡ «እ ማማ ፡ ሆይ ፤ ምንም ፡ አይገባሽም!» የምትል ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

በመጨረሻም ፤ በዚያች ፡ ዕለት ፡ ከቤ ት ፡ አልዋልኩም ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እውድማ ፡ ሔጄ ፡ አዘውትሬ ፡ በማድርበት ፡ ቦታ ፡ እገኝ ፡ ነበር ። ፈረሶቹም ፡ ለምለም ፡ ሣ ር ፡ ወዳለበት ፡ ሜዳ ፡ እንዲግጡ ፡ ነዳኋቸው ። የኅብረት ፡ እርሻ ፡ ሊቀ ፡ መንበርም ፡ ከብቶችን ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ለምለም ፡ ሳር ፡ ይግጡ ፡ ዘንድ ፡ አይፈቅድልንም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ሕጉን ፡ ተላልፌ ፡ ፈረሶቹ ፡ በሚገባ ፡ ይመግ ቡ ፡ ዘንድ ፡ ከጨፌው ፡ አገድኋቸው ። ነጠል ፡ ብላ ፡ በምትገኝ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ሌሊት ፡ ማንም ፡ ማየት ፡ አለመቻሉን ፡ አወቅሁ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፈረሶቹን ፡ ፈትቼ ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ በነዳኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ ቀድሞ ፡ አራት ፡

ፈረሶች ፡ ሲያግጥ ፡ አገኘሁት ። በበኩሌም ፡ ተቆጣሁ ። ሁለት ፡ ፈረሶች ፡ መያዝ ፡ የሚችል ፡ ጋሪ ፡ ስለነበረኝ ፡ ይህም ፡ እንድቆጣ ፡ አደረገኝ ። በቦታዬ ፡ እንዲህ ፡ ማድረግ ፡ የደፈረውን ፡ ሰው ፡ ፈረሶች ፡ ለማባረርና ፡ ትምህርት ፡ ልሰጠው ፡ ቁርጥ ፡ የሆነ ፡ ሀሳብ ፡ አደረግሁ ። በድንገትም ፡ ሁለቱ ፡ ፈረሶች ፡ የዳንያር ፡ መሆናቸውን ፡ ተረዳሁ ። በዚያኑ ፡ ዕለት ፡ ጓድ ፡ መሪው ፡ የተናገረለት ፡ ሰውዬ ፡ ነበር ። ከሚቀጥለው ፡ ዕለት ፡ ጀምሮ ፡ አብረን ፡ ስለ ምንሠራ ፡ የእሱን ፡ ፈረሶች ፡ ተውኳቸውና ፡ ወደ ፡ አውድማው ፡ መጣሁ ።

እዚያም ፡ ዳንያርን ፡ አገኘሁት ፡ እሱም ፡ የጋሪውን ፡ መንኮራኩር ፡ ዘይት ፡ ሲያጠጣና ፡ የላሉትን ፡ መገጣጠሚያዎች ፡ ሲያጠባብቅ ፡ ነበር ።

«ዳንያር ፡ ሆይ ፤ እዚያ ፡ ማዶ ፡ እሸለቆው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ፈረሶች ፡ ያንተ ፡ ናቸውን?» ብዬ ፡ ጠየቅሁት ።

በቀስታ ፡ ራሱን ፡ ዘወር ፡ አደረገና ፤

«ሁለቱ ፡ ናቸው ።»

«ሌሎቹ ፡ ጥንድ ፡ ፈረሶችስ?»



«የጀሚላ ፡ ፈረሶች ፡ ናቸው ።»

«እሷ ፡ ማን ፡ ናት? ዋርሳህ ፡ ነችን?»

«አዎን ።»

«ጓድ ፡ መሪው ፡ ራሱ ፡ እዚህ ፡ ተዋቸውና ፡ እንድጠብቃቸው ፡ ለመነኝ ።»

ባለማባረሬ ፡ እንዴት ፡ ያለሁ ፡ ዕድለኛ ፡ ነኝ!

መሸ ፤ የምሽት ፡ ለስላሳ ፡ ነፋስም ፡ ከተራሮች ፡ ጸጥ ፡ አለ ። በእህል ፡ መውቂያው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ዳንያርም ፡ ከሣሩ ፡ ክምር ፡ አጠገብ ፡ እጎኔ ፡ ጋደም ፡ አለና ፡ ጥቂት ፡ እንደቆዬ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ አመራ ። ጀርባውን ፡ ወደኔ ፡ መልሶ ፡ ከገደሉ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ዘንበል ፡ አድርጎ ፡ ቆመ ። ረዥምና ፡ ቅርጸ ፡ መልካም ፡ ሰውነቱ ፡ በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ግትር ፡ ብሎ ፡ በደንብ ፡ እንዳልተጠረበ ፡ እንጨት ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በፍጥነት ፡ ይንቧቧ ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ የሚጠባበቅ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በሌሊትም ፡ ጠርቶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ድምጽና ፡ የወንዙን ፡ ሹክሹክታ ፡ ያዳምጥ ፡ እንደ ፡ ነበረም ፡ ለይቼ ፡

ማወቅ ፡ አልችልም ። እንደገናም ፡ ከወን
ዙ ፡ ዳር ፡ ለማደር ፡ የፈቀደ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ።
ስለዚህም ፡ አሰብኩና ፡ ፈገግታን ፡ አሳየሁ ።

ዳንያርም ፡ ለመንደራችን ፡ አዲስ ፡ እን
ግዳ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡
አንድ ፡ ልጅ ፡ ከመስክ ፡ በሩጫ ፡ መጥቶ ፡ እየ
ጮኸ ፡ ቁስለኛ ፡ ወታደር ፡ መንደር ፡ ገብቷል ፡
በማለት ፡ ማን ፡ እንደሆነና ፡ ከወዴትስ ፡ እን
ደመጣ ፡ ለይቶ ፡ አላወቀም ፡ ነበር ። የቀጠለ
ው ፡ ድንጋጤም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከጦር ፡ ግን
ባር ፡ ሲመለስ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሄዶ ፡
ይጎበኘዋል ፤ እጁን ፡ ጨብጦ ፡ አድርጎ ፡ ሰላ
ምታ ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ዘመዶቹን ፡ አግኝቶ ፡
እንደሆነ ፡ ይጠይቀውና ፡ የመጨረሻው ፡ ወሬ ፡
ምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይጠይቀዋል ። በዚህ ፡
ጊዜም ፡ ጩኸቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስለነበረ ፡ ለመ
ገለጥ ፡ ያቅት ፡ ነበር ። እያንዳንዱ ፡ ሰውም ፡
ተገረመ ፤ «ምናልባት ፡ ወንድሞቻችን ፡ ተመ
ልሰው ፡ መጡልን ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ ይ
ሆን?» ይሉ ፡ ነበር ። ሰውዬው ፡ ማን ፡ እንደነ
በረ ፡ ለማወቅ ፡ አጫጆች ፡ ሁሉ ፡ በሽቅድም
ድም ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ መጡ ።



እንደገባን ፡ ዳንያር ፡ የመንደራችን ፡ ሰው ፡
ነው ። ገና ፡ በሕፃንነቱ ፡ የሙት ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡
ከቤት ፡ ቤት ፡ እየዞረ ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ያ
ህል ፡ አሳልፎ ፡ በመጨረሻ ፡ ግን ፡ በቻክማክስ
ክ ፡ ሜዳ ፡ ከካዛኽስ ፡ ጋር ፡ ለመኖር ፡ ሄዶ ፡ ነበር ።
በእናቱ ፡ በኩል ፡ ወገኖቹ ፡ ከካዛኽስ ፡ ጎሣ ፡
ስለነበረ ፡ ነው ። ልጁ ፡ አንድም ፡ የቅርብ ፡ ዘ
መድ ፡ በመንደራችን ፡ አልነበረውምና ፡ ታዛ
ቢ ፡ አጥቶ ፡ በፍጹም ፡ ተረስቶ ፡ ነበር ። የትው
ልድ ፡ መንደሩን ፡ ለቆ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ እንዴ
ት ፡ ይኖር ፡ እንደነበረ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ዳንያር ፡
በፈንታው ፡ የደረሰበትን ፡ መከራ ፡ በመግለጡ ፡ የሙ
ት ፡ ልጅ ፡ መራራ ፡ ጽዋንም ፡ በሙሉ ፡ የጠጣ ፡
መሆኑን ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ሕይወትም ፡ እንደተንከ
ባላይ ፡ ናዳ ፡ ተከታተለው ። ለረዥም ፡ ጊዜም ፡
በቻክማክስክ ፡ በረጋው ፡ ጨውማ ፡ ቀበሌ ፡ በጎ
ችን ፡ ያግድ ፡ ነበር ። በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ባለም ፡
ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በበረሃ ፡ ውስጥ ፡ ቦይ ፡ ይቆፍር ፡
ነበር ። በአዲሱ ፡ በመንግሥት ፡ የጥጥ ፡ እርሻ
ም ፡ ሥራ ፡ እንደዚሁም ፡ በታሽኬንት ፡ አቅ
ራቢያ ፡ በምትገኘው ፡ በአንግሬንስክ ፡ ማዕ

ድንም ፡ አገልግሎ ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡
የተጠራውም ፡ ከዚሁ ፡ ሥፍራ ፡ ነው ።

ሕዝቡም ፡ ዳንያር ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ መ
ንደሩ ፡ ተመልሶ ፡ በመምጣቱ ፡ ተስማሙበት ፤
«የቱን ፡ ያህል ፡ በባዕድ ፡ አገሮች ፡ ቢንከራተትም ፡
በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ተመለሰ ፡ እንዲህ ፡ ማለት
ም ፡ ለትውልድ ፡ አገሩ ፡ ውሃ ፡ በቃ ፡ ማለት ፡
ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከካ
ዛኽ ፡ ቋንቋ ፡ ቢጨምር ፡ ቋንቋውን ፡ ፈጽሞ ፡
አልረሳም ፡» አሉ ።

«ቱልፓርም*፡ የገዛ ፡ መንጋውን ፡ ዓለም ፡
ዳርቻ ፡ ላይ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ያገኘዋል ።
ላንድ ፡ ሰው ፡ የትውልድ ፡ አገሩና ፡ ወገኖቹ ፡ ከ
ሁሉ ፡ የሚቀርቡት ፡ ናቸው ። ተመልሰህ ፡ መ
ምጣትህ ፡ መልካም ፡ ነው ። እኛና ፡ የቅድ
ም ፡ አያቶችህ ፡ ነፍሶች ፡ ተደስተናል ። በአ
ላህ ፡ ፈቃድም ፡ ጀርመኖችን ፡ አጥፍተን ፡ እ
ንደገና ፡ በሰላም ፡ እንኖራለን ፡ አንተም ፡ ደግ
ሞ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ትዳር ፡ ይዘህ ፡ የራስ

---

* ቱልፓር — ባፍ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የሚነገ
ር ፡ አንድ ፡ ባለሞያ ፡ ፈረስ ፡ ነው ።



ህ ፡ ቤተሰብ ፡ ይኖርሃል ። እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡
የገዛ ፡ ጎጆህ ፡ ጢስ ፡ ይጤሳል!» ብለው ፡ የመ
ንደሩ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ተናገሩ ።

የዳንያርን ፡ ዘር ፡ በመቁጠር ፡ ዝምድና
ቸውን ፡ አረጋገጡለት ፡ አዲስ ፡ «ዘመድ ፡» ዳ
ንያር ፡ እመኻላችን ፡ ተገኘ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኦሮዝማት ፡ ይህን ፡ ረ
ዥምና ፡ ከትከሻው ፡ የጎበጠ ፡ አንካሳ ፡ ወታ
ደር ፡ ወደ ፡ መስክ ፡ ይዞት ፡ መጣ ። ታላቁን ፡ ኮ
ቱን ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጎ ፡ በፍ
ጥነት ፡ ተራመደ ። እንዲህ ፡ ያደረገበት ፡ ምክ
ንያቱም ፡ ከኦሮዝማት ፡ ፈረስ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እን
ዳይቀር ፡ ነው ። ከረዢሙ ፡ ዳንያር ፡ ቀጥሎ ፡ ደልዳላ
ው ፡ የጓዳችን ፡ መሪ ፡ ምንም ፡ ዕረፍት ፡ ስላልነበረ
ው ፡ ትንሽ ፡ ወፍ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። እነሱን ፡ ጎን ፡
ለጎን ፡ ቁመው ፡ በማየታቸው ፡ ልጆቹ ፡ ሳቁ ።

የዳንያርም ፡ ቁስል ፡ ገና ፡ አልዳነም ፡ ነበር ፤
ቅልጥሙም ፡ እንደ ፡ ሰለለ ፡ ስለነበረ ፡ መልካ
ም ፡ አጫጅ ፡ መሆን ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ከእኛ ፡
ከልጆች ፡ ጋር ፡ በማጫጂ ፡ መሣሪያዎች ፡
እንዲሠራ ፡ ብቻ ፡ ተደረገ ። እውነት ፡ ለመናገ
ርም ፡ አልወደድነውም ፡ ነበር ። ከሁሉ ፡ አስ

ቀድሞ ፡ ዝምተኛነቱን ፡ አልወደድንም ። ዳን
ያር ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፤ ሲናገርም ፡
አፉ ፡ ያመጣውን ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ በገዛ ፡ ሃሳቡ ፡
ከመመሰጥ ፡ የተነሳው ፡ የሚያወራው ፡ ከሚያስበው ፡
ጋራ ፡ አይገጣጠምም ፡ ነበር ። አንተን ፡ ማየ
ትና ፡ አለማየቱንም ፡ ማወቅ ፡ አትችልም ። ዳ
ሩ ፡ ግን ፡ በሚያልሙት ፡ ዓይኖቹ ፡ በቀጥታ ፡
የሚመለከትህ ፡ ይመስላል ።

«ከጦር ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡
ራሱን ፡ ማወቅ ፡ አልቻለም ፡ አሳዛኝ ፡ ሰው!»
ይሉ ፡ ነበር ።

ከሁሉ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡
ይህ ፡ በቀን ፡ ስለሚታየው ፡ ሕልም ፡ ሲታሰ
ብም ፡ ዳንያር ፡ የሚያደርገው ፡ ሥራ ፡ በፍጥነ
ትና ፡ በብልሃት ፡ ያከናውን ፡ ነበር ፤ በአንድ ፡
ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሰውን ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ይችል ፡
ነበር ። ምናልባትም ፡ ደስ ፡ ያላሰኙት ፡ የልጅ
ነቱ ፡ ዘመን ፡ ሀሳቡን ፡ ስሜቱን ፡ ለመሰወርና ፡
ቁጥብ ፡ መሆንን ፡ አስተምረውት ፡ ይሆናል ።

ስለ ፡ ከንፈሮቹም ፡ ዘወትር ፡ ተገጥመው ፡
ይታዩ ፡ ነበር ። ዓይኖቹ ፡ የተከዙ ፡ ነበሩ ፤ ቅን
ድቦቹ ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ ለዛለው ፡ ፊቱ ፡ ሕይወትን ፡



ያበረከቱለት ፡ ነበር ። በድንገትም ፡ ንቁ ፡ ሆኖ ፡
ይታይና ፡ ለኛ ፡ የማይሰማ ፡ ነገር ፡ የሚሰማው ፡
መስሎ ፡ በመታየት ፡ ቅንድቦቹ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ዓ
ይኖቹ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይንቀለቀሉ ፡ ነበር ። ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ የደስታ ፡ ገጽ ፡ ለረ
ኙም ፡ ጊዜ ፡ ይታይበት ፡ ነበር ። ሁላችንም ፡
እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሁናቴ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሆነ
ብን ፡ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ሌሎች ፡ አዳዲስ ፡
ፈሊጦችም ፡ ነበሩት ። በምሽትም ፡ ፈረሶቻች
ንን ፡ እናጉርና ፡ በድንኳኑ ፡ ዙሪያ ፡ እንሰበሰ
ብና ፡ ወጥ ፡ ቤቱ ፡ ምግባችንን ፡ እስኪያስናዳ
ልን ፡ እንጠብቃለን ። ዳንያር ፡ ግን ፡ ከኮረብ
ታዋ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ይቀመጥና ፡ እስኪመሽ ፡
ድረስ ፡ እዚያው ፡ ያመሽ ፡ ነበር ።

«እዚያ ፡ ምን ፡ ዘብ ፡ ይጠብቅ ፡ ይሆን ፡ ወ
ይስ ፡ ምን ፡ ያደርግ ፡ ይሆን?» እየተባባልን ፡
እንስቅ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አድናቆቴን ፡ ለማርካት ፡ ወደ ፡
ኮረብታው ፡ ተከትዬው ፡ ወጣሁ ። እዚያም ፡ ላ
ይ ፡ ምንም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ የለም ። ድ
ብዝዝ ፡ ባለው ፡ ብርሃን ፡ ርቆ ፡ እስከሚታየው ፡
አድማስ ፡ ድረስ ፡ ሜዳው ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ጨ

ለማውና ፡ ድንግዝግዝ ፡ ማሳዎችም ፡ ጥቂት ፡
በጥቂት ፡ ለዓይን ፡ ከመታየት ፡ ራቁ ።
ዳንያርም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ እጐኑ ፡ መገኘት ፡
ምንም ፡ ያላሰበበት ፡ መስሎ ፡ ነበር ፡ ጉልበቶ
ቹን ፡ በእጆቹ ፡ አቅፎና ፡ በሀሳብ ፡ ተውጦ ፡
አርቆ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡
ለእኔ ፡ ሊሰማ ፡ የማይችል ፡ ድምጽ ፡ የሚሰማ
ው ፡ መሰለኝ ። አልፎ ፡ አልፎም ፡ ቁጠኝነት ፡
ይሰማው ፡ ነበር ። ዓይኖቹንም ፡ ብልጥጥ ፡ አድ
ርጐ ፡ ይገልጣቸው ፡ ነበር ። አንድ ፡ የበጠበጠ
ው ፡ ነገር ፡ ነበር ፤ ብድግ ፡ ብሎም ፡ የሚዘረር ፡
መሰለኝ ። ዳኑ ፡ ግን ፡ ወደኔ ፡ ሳይሆንና ፡ እኔ
ንም ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥረኝ ፡ ቀረ ። ከዚህ ፡ በ
ኋላም ፡ አተኩሬ ፡ ተመለከትኩት ፤ ሆኖም ፡ ለይቼ ፡
ማየት ፡ አልተቻለኝም ። ዳንያርም ፡ እንደገና ፡ ዝ
ሎ ፡ ተቀመጠ ፡ አኳኋኑም ፡ ሁሉ ፡ በዕለቱ ፡
ሥራ ፡ የደከመ ፡ ሰውነቱን ፡ የሚያሳርፍ ፡ መስሎ ፡
ይገመት ፡ ነበር ።
የኅብረት ፡ እርሻ ፡ የድርቆሽ ፡ ሜዳዎቻ
ችን ፡ ጐርፋም ፡ በሆኑት ፡ በኩርኩሬው ፡ ወን
ዝ ፡ ዳር ፡ ተበትነዋል ። በመንደራችን ፡ ያ
ለው ፡ ወንዝም ፡ ከአንድ ፡ ሸለቆ ፡ ጥግ ፡ ይፈ



ልቃል ፤ በሸለቆውም ፡ ተጣድፎ ፡ ይወርዳል ።
ጨፌው ፡ ታጭዶ ፡ ድርቆሽ ፡ በሚቆለልበት ፡
ሞራትም ፡ የተራራ ፡ ወንዞች ፡ ሞልተው ፡ በሚ
ፈሱበት ፡ ወራት ፡ ነው ። ጭቃ ፡ ለበሱ ፡ ውሃ
ም ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ ገደማ ፡ ይነሳል ። ከወንዙ ፡ ኃ
ይለኛ ፡ መንቧቧት ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ከእ
ንቅልፌ ፡ ነቅቼ ፡ ከድንኳኔ ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡
እልና ፡ በጠራው ፡ ሰማያዊ ፡ ሰማይ ፡ ያሉትን ፡
ከዋክብት ፡ እመለከታለሁ ። ጸጥተኛው ፡ ሌሊ
ት ፡ ጨልሞአል ፤ ብርድን ፡ ያዘለ ፡ ነፋስ ፡ በ
ኃይል ፡ ነፈሰ ፤ ምድር ፡ አንቀላፍታ ፡ ቁጡ
ው ፡ ወንዝ ፡ ግን ፡ በዛቻ ፡ ተሞልቶ ፡ የሚወር
ድ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከ
ወንዙ ፡ ዳር ፡ የቀረብን ፡ ባንሆንም ፡ የውሃው ፡
አወራረድ ፡ በግልጥ ፡ ይሰማኝ ፡ ነበር ። ድን
ገተኛ ፡ ፍርሃት ፡ ሰፍሮብኝ ፤ ድንኳኑ ፡ ተቀዳ
ድዶ ፡ ጐርፍ ፡ የወሰደው ፡ መሰለኝ ። ጓደኞቼ
ም ፡ ከባድ ፡ የሆነውን ፡ የሞት ፡ ዓይነት ፡ እን
ቅልፍ ፡ ተጭኖአቸው ፡ ሳለ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዕረ
ፍት ፡ ሳይኖረኝ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እል ፡ ነበር ።
በኩርኩሬው ፡ ጐርፋማ ፡ መሬቶች ፡ ላይ ፡
ሌሊት ፡ ውብ ፡ ናት ፡ ግን ፡ ታስፈራለችም ። በመ

ስኩ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የተቀየዱ ፡ ፈረሶች ፡ ጥላ ፡
አልፎ ፡ አልፎ ፡ መታየት ፡ ይችል ፡ ነበር ። እ
ነሱም ፡ በጤዛ ፡ የተሞሉትን ፡ ማሮች ፡ ተመግ
በው ፡ ስለ ፡ ጠገቡ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያንገላታ
ቸው ፡ ይመስላሉ ። በዝግታ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡
ይተነፍሱም ፡ ነበር ። እነሱም ፡ አለፍ ፡ ብሎ ፡
የኩርኩሬው ፡ ወንዝ ፡ በዳር ፡ ያሉትን ፡ ለጋ ፡
አበቦች ፡ አጉብጦ ፡ ደንጊያዎችን ፡ በብርቱ ፡
ድምጽ ፡ ያጋጫቸው ፡ ነበር ። ዕረፍት ፡ የሌለው ፡
ወንዝም ፡ ሌሊትን ፡ አስፈሪ ፡ ያደርጋታል ።

እንደነዚያ ፡ በነበሩት ፡ ሌሊቶችም ፡ ዘወ
ትር ፡ ዳንያርን ፡ አስብ ፡ ነበር ። ሁልጊዜም ፡ በ
ወንዙ ፡ ዳር ፡ ከድርቆሽ ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ ይተኛ ፡
ነበር ። አይፈራም ፡ ነበርን? የወንዙስ ፡ ድምጽ ፡
አያደነቁረውም? በእውነቱስ ፡ እዚያ ፡ እንቅል
ፍ ፡ ይወስደው ፡ ነበርን? ስለምን ፡ ሌሊቶቹን ፡
ከወንዙ ፡ ዳር ፡ ብቻውን ፡ አደረ? እንዴት ፡ ያ
ለ ፡ ኃይልስ ፡ ወደዚያ ፡ መራው? እሱ ፡ አስደ
ናቂ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ከሌላ ፡ ዓለም ፡ የመጣ ፡ ነ
በር ። አሁን ፡ ወዴት ፡ ነበር? ዙሪያዬን ፡ ተመ
ለከትሁ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ አላየሁ ። የወንዙ ፡ ዳ
ር ፡ ደግሞ ፡ ከርቀቱ ፡ የተነሣ ፡ በቁልቁለት ፡



ላይ ፡ እንደሚገኙ ፡ ኮረብቶች ፡ እያነሰ ፡ ሄዶ ፤
የተራራው ፡ ሸንተረርም ፡ በጨለማ ፡ ተሸፈ
ነ ። በተራራው ፡ ጫፍ ፡ ላይም ፡ ማናቸው ፡
ነገር ፡ በጸጥታ ፡ ሆኖ ፡ ከዋክብት ፡ ብቻ ፡ ይታ
ዩ ፡ ነበር ።

ዳንያርም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከመንደሩ ፡
ወዳጆች ፡ አግኝቶ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ማንም ፡
ያስብ ፡ ይሆናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደተለመደ
ው ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ብቸኛ ፡ ነው ፡ ምክን
ያቱም ፡ ወዳጅነት ፡ ወይም ፡ ጠላትነት ፡ ገር
ነት ፤ ምቀኝነት ፡ የሚባሉትን ፡ ቃላት ፡ ትር
ጓሜ ፡ ያላወቀው ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በመንደሮችም ፡
አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ ማሳወቅና ፡ ለወዳ
ጆቻቸውም ፡ አለሁላችሁ ፡ የሚሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊ
ዜ ፡ በጐ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ክፉት ፡ ማድረግና ፡
እንደመንደር ፡ ሽማግሎች ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ነ
ገሮችን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አመጣጣቸው ፡ ማቀና
በር ፡ የሚችሉ ፤ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ የሚከበሩና ፡
ሴቶችም ፡ የሚያደንቁአቸው ፡ አሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዳንያር ፡ ያለ ፡ ዝም
ተኛና ፡ ጭምት ፡ በመንደሩ ፡ የዕለት ፡ ጉዳይ ፡
ምንም ፡ ተካፋይነት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፤ በሕዝ

ብ ፡ ዘንድ ፡ ችላ ፡ ይባላል ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡
ይፈራል ፤

«በጉም ፡ ሆነ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አያደርግም ።
አሳዛኙ ፡ ሰውዬ ፡ ይደናቀፋል ፡ ስለዚህ ፡ እን
ጆሻው ፡ ይሁን ።»

እንደ ፡ ልማዳችን ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡
ሰው ፡ የቀልድና ፡ የርኅራኄ ፡ ማሳያ ፡ ነው ። እ
ኛ ፡ ከዕድሜአችን ፡ አብልጠን ፡ ራሳችንን ፡ የ
ምንቆጥር ፡ ወጣቶችም ፡ ከአደጉት ፡ ሰዎች ፡
ጋር ፡ እኩል ፡ ለመራመድ ፡ በመጣጣር ፡ ዳ
ንያርን ፡ በስተኋላው ፡ እየተከተልን ፡ እንስቅ
በት ፡ ነበር ፤ በግንባር ፡ ግን ፡ ልንስቅበት ፡ አ
ልደፈርንም ። የውትድርና ፡ ሸሚዙን ፡ እወን
ዝ ፡ ሲያጥብ ፡ እያየን ፡ ሳቅንበት ። ሸሚዙ
ን ፡ ያጥብና ፡ ሌላ ፡ ስላልነበረው ፡ ለዛዛውን ፡
ይለብስ ፡ ነበር ።

አስገራሚው ፡ ነገር ፤ ዳንያር ፡ ደግና ፡ ቁ
ጥብ ፡ መስሎ ፡ ቢታይም ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡
ልንነግረው ፡ አልደፈርንም ፤ ምክንያቱም ፡ በ
ዕድሜ ፡ ስለ ፡ በለጠን ፡ አይደለም ፡ የሦስት ፡
አራት ፡ ዓመታት ፡ ብልጫ ፡ ምንም ፡ አልነበ
ረም ። ይህም ፡ የብልግና ፡ አነጋገር ፡ እንዳ



ንናገር ፡ ሊያግደን ፡ አይችልም ፡ ነበር ። ኩራተኛ ፡
ወይም ፡ ጭምት ፡ በመሆኑ ፡ አልነበረም ። በጭምት
ነቱ ፡ አንድ ፡ ሊደረስበት ፡ ያልተቻለ ፡ ነገር ፡ ቢኖር
ም ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡
ለመቀለድ ፡ ብንወድም ፤ ይህ ፡ ይዞታው ፡ ገታን ።
እኛም ፡ በእሱ ፡ በኩል ፡ ቁጥቦች ፡ ለመሆ
ን ፡ ያበቃን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ምክንያት ፡ በመሆ
ኑ ፡ ነው ። እኔ ፡ በጣም ፡ ችኮ ፡ ልጅ ፡ ነበርኩ ፡
መጨረሻ ፡ በሌላቸው ፡ ጥያቄዎቼም ፡ ሰዎችን ፡
አሰቆጣ ፡ ነበር ። ታላቁ ፡ ፍላጎቴም ፡ ከውት
ድርና ፡ የተሰናበቱትን ፡ ወታደሮች ፡ ስለጦ
ርነት ፡ ጉዳይ ፡ ደጋግሜ ፡ በመጠየቅ ፡ ነበር ።
ዳንያርም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለመሥራት ፡ በመጣ ፡
ጊዜ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ነባር ፡ ወታደር ፡
አንድ ፡ ነገር ፡ ለመረዳት ፡ ዘወትር ፡ አጋጣሚ ፡
ጊዜ ፡ እሻ ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከዕለቱ ፡ ሥራ
ችን ፡ በኋላ ፡ በሰፈር ፡ እሳት ፡ አንድደን ፡ ስን
ሞቅ ፡ ነበርን ።

«ዳንያር ፡ ሆይ ፤ ከመተኛታችን ፡ በፊት ፡
ስለጦርነቱ ፡ ታሪክ ፡ ተርክልን ፡» ብዬ ፡ ጠየ
ቅሁት ።

በመጀመሪያ ፡ ምንም ፡ አልተናገረም ፤ ቅርታ ፡ የገባው ፡ መስሎም ፡ አይታይ ፡ ነበር ። ዝም ፡ ብሎ ፡ አተኩሮ ፡ እሳቱን ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ተመለከተና ፡ በመጨረሻ ፡ ራሱን ፡ ቀና ፡ አድርጎ ፡ ተመለከተን ።

«ስለ ፡ ጦርነቱ ፡ ነው?» ብሎ ፡ ጠየቀ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ የራሱን ፡ ሀሳብ ፡ የሚመልስ ፡ መስሎ ፡ በመታየት ፡ በቁጣ ፡ ድምጽ ፡ «ስለ ፡ ጦርነት ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ ባታውቁ ፡ ይሻላል!» አለ ።

ዘወር ፡ ብሎ ፡ ደረቅ ፡ ቅጠሎችን ፡ ጨብጦ ፡ እሳት ፡ ጨመረና ፡ ወደኛ ፡ ሳይመለከት ፡ እሳቱን ፡ እፍ ፡ ይል ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳንያር ፡ ምንም ፡ አልተናገረም ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የተናገራቸው ፡ ጥቂቶቹ ፡ ቃላት ፡ ጦርነት ፡ በቀላሉ ፡ አፍ ፡ እንዳመጣ ፡ ሊነጋገሩበት ፡ የማይችል ፡ አርእስት ፡ መሆኑን ፡ ተገንዘብን ፤ የአልጋ ፡ ላይ ፡ ወሬ ፡ አለመሆኑንም ፡ አስተዋልን ። ጦርነቱም ፡ የብዙዎችን ፡ ደም ፡ ያደረቀና ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ የተቀረጸ ፡ በመሆኑ ፡ ስለ ፡ እሱ ፡ ጉዳይ ፡ መነጋገርን ፡ አልፈቀደም ። እኔም ፡ አፈርኩ ፡ ቀለ



ልኩም ፤ ከዚያች ፡ ዕለት ፡ ወዲህም ፡ ስለ ፡ ጦርነት ፡ ጉዳይ ፡ ምንም ፡ ጠይቄው ፡ አላውቅም ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እሱን ፡ ለማክበር ፡ የበቃንበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። መንደሩ ፡ በዳንያር ፡ በራሱ ፡ ተስፋ ፡ እንደቆረጠ ፡ ሁሉ ፡ እኛም ፡ ያቺን ፡ ምሽት ፡ ወዲያውኑ ፡ ረሳናት ። የእሱ ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ብቸኝነትና ፡ ጭምትነት ፡ ግዴለሽነትን ፡ ወይም ፡ ርኅራኄን ፡ አስነሣ ።

«ዕድለ ፡ ቢስ ፡ መጠጊያ ፡ የሌለው ፡ ጎልማሳ ፡ ነው ። ምግቡንም ፡ ከኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ ያገኛል ፡ እሱም ፡ ጸጥተኛና ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ግልገል ፡ ገራም ፡ ነው!» ሲሉ ፡ መንደረተኞቹ ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ የኑሮ ፡ ይዞታዎች ፡ ስለተላመዱአቸው ፡ በመጨረሻ ፡ በጭራሽ ፡ እሱን ፡ መከታተል ፡ እርግፍ ፡ አድርገው ፡ ተው ። ይህም ፡ መሆን ፡ የሚገባው ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ በማናቸው ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ማስረዳት ፡ ካልቻለ ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ይረሱታል ።

በማግሥቱ ፡ ማለዳ ፡ ዳንያርና ፡ እኔ ፡ ፈረሶቹን ፡ ወደ ፡ ውድማው ፡ ይዘን ፡ ሄድን ። ጃሚላም ፡ ፈጥና ፡ ልትከተለን ፡ ነበር ። ከሩቅ ፡ ተመልክታ ፡ ጮኸች ።

«ሄይ ፤ ኪቺኔ ፡ ባላ ፡ (ዋርሳዬ!) ፈረሶቹን ፡ ወደዚህ ፡ ነድተህ ፡ አምጣ ። ማሠሪያቸውስ ፡ ወዴት ፡ አለ?» አለችና ፡ ጋሪዎቹን ፡ መፈተሽ ፡ ጀመረች ። አመለካከትዋም ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነጂ ፡ ሲያስመስላት ፡ መገጣጠሚያዎቹ ፡ ሁሉ ፡ በደንብ ፡ መሆናቸውን ፡ በእግርዋ ፡ እየረገጠች ፡ ታረጋግጥ ፡ ነበረች ።

ፈረሶቹን ፡ እየነዳን ፡ ስንመጣ ፡ ትርኢታችን ፡ አስገራሚ ፡ ሆነባት ። የዳንያር ፡ ረዣዥምና ፡ ልሎች ፡ ቅልጥሞች ፡ ሠፋፊ ፡ እስከ ፡ ጉልበት ፡ የሚደርሱ ፡ ጫማዎች ፡ አጥልቀው ፡ ሊወልቁ ፡ የደረሱ ፡ ነበሩ ፡ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በቁሻሻ ፡ ተረከዞቼ ፡ ፈረሴን ፡ እኮለኩል ፡ ነበር ።

«እንዴት ፡ ያላችሁ ፡ መቀናጆ ፡ ናችሁ!» ራስዋን ፡ ዘንበል ፡ አድርጋ ፡ ተናገረች ። ቀጥላም ፡ «ከመጥረሩ ፡ በፊት ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጠን ፡ ማለፍ ፡ አለብንና ፡ ፍጠኑ ፡ ንዱ!» ብላ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠችን ።



ልጓሙን ፡ አጥብቃ ፡ ያዘች ፡ ፈረሶቹንም ፡ ወደ ፡ ጋሪው ፡ አቀረበችና ፡ ማሠር ፡ ጀመረች ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ማሠሪያዎች ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠብቁ ፡ ጠየቀችኝ ። ዳንያርም ፡ እዚያ ፡ ይኑር ፡ አይኑር ፡ ልብ ፡ አላደረገችም ፡ ነበር ።

ዳንያርም ፡ በራስዋ ፡ ተማምና ፡ የምታከናውነውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተገረመ ። እዚያ ፡ ቆሞ ፡ ከንፈሩን ፡ ሲመጥ ፡ አስተያየቱ ፡ የወዳጅነት ፡ አስተያየት ፡ አልነበረም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዘዴ ፡ የለበሰ ፡ አድናቆት ፡ ነበር ። ከሚዛኑ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተቆጠረ ፡ ጆንያ ፡ አነሣና ፡ በጸጥታ ፡ ወደ ፡ ጋሪ ፡ ወስዶ ፡ ጫነ ፤ ጃሚላም ፡ መቆጣት ፡ ጀመረች ።

«እኛ ፡ ሁላችን ፡ በራሳችን ፡ የምንሠራ ፡ ይመስልሃልን? የለም ፤ አይደለም ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፤ እንዲህ ፡ መሆን ፡ አይችልም ፡ እጅህን ፡ ስጠኝ ። አንተ ፡ ደግሞ ፡ ዋርሳዬ ፡ (ኪቺኔ ፡ ባላ ፡) ቆመህ ፡ ምን ፡ ትጠብቃለህ? ከጋሪው ፡ ላይ ፡ ውጣና ፡ ጆንያዎቹን ፡ አደራጅ!» አለችኝ ።

ጃሚላም ፡ የዳንያር ፡ እጅ ፡ ጨብጥ ፡ አደረገችና ፡ እጆቻቸውን ፡ አስተባብረው ፡ አን

ድ ፡ ጀንያ ፡ እህል ፡ እንደ ፡ ሜኑ ፡ አሳዛኙ ፡ ሰውዬ ፡ አፍሮ ፡ ፊቱ ፡ ቀላ ። እጆቻቸውን ፡ አስተባብረውና ፡ ጀንያውን ፡ ባንድ ፡ ተሸክመው ፡ በሜኑ ፡ ቁጥር ፡ የሁለቱም ፡ ራሶች ፡ ሊነካኩ ፡ ይደርሱ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ እንዴት ፡ እንደተበሳጩና ፡ ከንፈሩን ፡ ይነክስ ፡ እንደነበረ ፡ የጃሚላንም ፡ ፊት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ እንዳልፈለገ ፡ አወቅሁ ። እሷ ፡ ግን ፡ ከምንም ፡ አልቆጠረችው ፡ ነበር ። ከምትመዝነው ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ስትቀልድ ፡ ብቻዋን ፡ የነበረች ፡ መሰላት ። ጋሪዎች ፡ ተጭነው ፡ ልጓማቸውን ፡ ካነሣን ፡ በኋላ ፤ በአስተዋይነት ፡ ተመልክታ ፡ እየሳቀች ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤

«ሄይ ፤ አንተ ፤ ስምህ ፡ ማን ፡ ይባላል! ዳንያር? ወንድ ፡ መስለህ ፡ ስለምትታይ ፡ በል ፡ እንግዲህ ፡ መንገዱን ፡ አሳይ!»

ዳንያርም ፡ መሳቢያውን ፡ ነጠቀና ፡ ሄደ ። «ስለምን ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ ነህ!» ብዬ ፡ አዘንኩለት ።

ወደ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ መንገዳችን ፡ ረዥም ፡ ነው ። ሜዳውን ፡ ለማቋረጥ ፡ ሀያ ፡ ኪሎሜትር ፡ ያስኬዳል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሸለቆው ፡ አድርጎ ፡



ወደጣቢያው ፡ ያደርሳል ። ስለ ፡ እሱም ፡ ያለው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ መንገዱ ፡ ቁልቁለት ፡ ሆኖ ፡ ለፈረሶቹ ፡ ቀላል ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

መንደራችን ፡ በኩርኩሬው ፡ ዳር ፡ ይገኛል ። እሱም ፡ በታላላቅ ፡ ተራራዎች ፡ ግርጌ ፡ ጥቁር ፡ ተራራዎች ፡ እስከሚባሉት ፡ ይደርሳል ። ጥቋቁር ፡ የዛፍ ፡ ጫፎች ፡ የሚታዩበት ፡ መንደር ፡ ሸለቆው ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ይታያል ።

በቀን ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሄድን ፤ ጧት ፡ ማለዳ ፡ ከመንደር ፡ ተነሥተን ፡ ቀትር ፡ ላይ ፡ ከጣቢያው ፡ እንደርሳለን ።

ፀሐይም ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ያቃጥላል ፤ በጣቢያው ፡ ላይም ፡ ጉራ ፡ ስለሚበዛ ፡ መሹለኪያ ፡ ለማግኘት ፡ ያስቸግር ፡ ነበር ። የእህል ፡ ጀንያዎች ፡ የተጫኑባቸው ፡ ጋሪዎች ፡ ከሸለቆው ፡ መጥተው ፡ በብዛት ፡ ይታያሉ ። ከሩቅ ፡ ከኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ እህል ፡ ተጭነው ፡ የመጡ ፡ በቅሎችና ፡ በሮች ፡ ነበሩ ። ተነድተው ፡ የመጡትም ፡ በልጆችና ፡ በወታደር ፡ ባለቤቶች ፡ ሲሆኑ ፡ የፀሐይ ፡ ግለት ፡ ፊታቸውን ፡ ያጠቋቆራቸውና ፡ ቀለማ

ቸው ፡ በፀሐይ ፡ የፈዘዙ ፡ ልብሶችን ፡ የለበሱ ፤ ባዶ ፡ እግሮቻቸውም ፡ የነቁ ፡ ከንፈሮቻቸውም ፡ ከፀሐይ ፡ ግለትና ፡ አቧራ ፡ የተነሣ ፡ የተሰነጣጠቁና ፡ የሚደሙ ፡ ነበሩ ።

በተለይ ፡ እህል ፡ በሚጫንበት ፡ ሥፍራም ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነበር ። የተጻፈውም ፡ «እያንዳንዱ ፡ ቅንጣት ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡» ይል ፡ ነበር ። እዚያ ፡ የነበረው ፡ የነጆዎቹ ፡ ጩኸትና ፡ ብጥብጥም ፡ ሊገለጽ ፡ አይቻልም ። በአቅራቢያውም ፤ ከአነሥተኛ ፡ ግንብ ፡ በስተኋላ ፡ አንድ ፡ ሎኮሞቲቭ ፡ ልምምድ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። እሱም ፡ እሳት ፡ ይተፋና ፡ የተቃጠለ ፡ ብረት ፡ ሽታም ፡ ይሸት ፡ ነበር ። በሀዲድ ፡ ላይ ፡ የሚሮጡ ፡ ባቡሮችም ፡ በአቅራቢያው ፡ ያጉራሩ ፡ ነበር ። ግመሎችም ፡ ከመሬት ፡ መነሣት ፡ አቅቶአቸው ፡ ይፋጉ ፡ ነበር ። በቁጣም ፡ አፋቸውን ፡ እየከፈቱ ፡ ምራቃቸው ፡ ይዝለገለግ ፡ ነበር ።

በእህል ፡ ማስረከቢያው ፡ ጣቢያ ፡ የሚገኘው ፡ እህል ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ተራራ ፡ ተቆልሎ ፡ በፀሐይ ፡ የቀላ ፡ ቆርቆሮ ፡ በተከደነ ፡ ሠቀላ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። ጆንያዎቹም ፡ በትክክል ፡ ባልተገ



ጣጠሙ ፡ የእንጨት ፡ ሳንቃዎች ፡ ላይ ፡ ተደርድረው ፡ ከጣሪያው ፡ ሥር ፡ መከማቸት ፡ ነበረባቸው ። አየሩ ፡ በእህል ፡ ሽታ ፡ ተሞልቶ ፡ ትቢያውም ፡ ያፍን ፡ ነበር ።

«ሄይ ፡ አንተ! ተጠንቀቅ!» ብሎ ፡ ተቀባዩ ፡ ኃላፊ ፡ እንቅልፍ ፡ ያጡ ፡ ዓይኖቹን ፡ በማፍጠጥ ፡ ከታች ፡ ጮኸ ። «አንሁና ፡ ከጫፍ ፡ ላይ ፡ አኑሩአቸው ፡» ብሎ ፡ ጡጫውን ፡ እያሳየ ፡ ተራገመ ።

የሚራገመውስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነበር? እኛም ፡ ወስደን ፡ የምናኖርበት ፡ ቦታ ፡ ለይተን ፡ እናውቃለን ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላም ፡ ሴቶች ፤ ሽማግሌዎችና ፡ ልጆች ፡ ስንዴውን ፡ ዘርተው ፡ ካመረቱበት ፡ ሥፍራ ፡ ጭነን ፡ እዚህ ፡ አድርሰናል ፤ አሁን ፡ በመኸር ፡ ወራት ፡ ደግሞ ፡ አገጣጣሚው ፡ ሥራ ፡ ፈትቶ ፡ የነበረውን ፡ መሣሪያ ፡ ለማገጣጠም ፡ ይታገላል ። የሴቶቹ ፡ ወገቦችም ፡ በማጨድ ፡ ከጎበጡበትና ፡ ልጆችም ፡ እያንዳንዱን ፡ ቅንጣት ፡ በጥንቃቄ ፡ ከለቀሙበት ፡ ሥፍራ ፡ አምጥተናል ።

የጆንያዎቹን ፡ ክብደት ፡ እስካሁን ፡ አስታውሳለሁ ። ላንድ ፡ ኃይለኛ ፡ ሰውም ፡ ሥራ

ው ፡ መሆን ፡ ይችላል ። ወደ ፡ ፊት ፡ ሔድኩና ፡ ጥርሶቼን ፡ ነክሼ ፡ የጆንያውን ፡ አፍ ፡ አጥብቄ ፡ አሰርኩና ፡ የሳንቃዎቼን ፡ ሚዛን ፡ አዳላደልኩ ፡ እንዳይወድቅብኝም ፡ ተጠነቀቅሁ ። ከትቢያውም ፡ ጉሮሮዬ ፡ ቆሰለ ፡ በዓይኖቼም ፡ እንፃር ፡ እሳታዊ ፡ ብልጭታዎች ፡ ጨፈሩብኝ ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ፈዝዤ ፡ ነበር ፡ ጆንያዎቹንም ፡ ከመንሻተት ፡ የሚያግዳቸው ፡ አለመኖሩን ፡ አውቄ ፡ አንዱ ፡ ሀሳቤ ፡ ደግሞ ፡ አብሬ ፡ ከጆንያው ፡ ጋር ፡ መንከባለል ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በስተኋላዬ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ጆንያዎች ፡ ተሸክመው ፡ በኔው ፡ ዕድሜ ፡ የነበሩና ፡ ወይም ፡ የወታደሮች ፡ ሚስቶች ፡ እንደኔው ፡ ያሉ ፡ ልጆች ፡ የነበራቸው ፡ ነበሩ ። በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጆንያዎችን ፡ ይሸከሙ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይፈቅድላቸው ፡ ነበር? እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሴቶች ፡ ሲያከናውኑ ፡ እያየሁ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ማፈግፈግ ፡ ተገቢ ፡ እንዳይደለ ፡ ተረዳሁ ።

ጃሚላም ፡ እፊቴ ፡ ነበረች ። ቀሚሷም ፡ እስከ ፡ ጉልበቶቿ ፡ ድረስ ፡ አጥሬው ፡ ስለነበረ ፡ በፀሐይ ፡ የተለበለቡ ፡ ባቶቿን ፡ ማየት ፡ ቻል



ኩ ። የእሷን ፡ ለጋ ፡ ሰውነት ፡ በጆንያ ፡ ሸክም ፡ ማንገላታት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ጥረት ፡ መሆኑን ፡ ማየት ፡ ቻልኩ ። ለአንድ ፡ ሰኮንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ትላለች ፡ እኔ ፡ አከታትዬ ፡ በምፈጽመው ፡ አገልግሎት ፡ መድከምና ፡ መበርታቴንም ፡ የምትታዘብ ፡ ይመስላል ።

«በርታ ፤ ዋርሳዬ ፡ ደርሰናል!» አለች ።

ድምጿ ፡ ስሎ ፡ የቁም ፡ ሙት ፡ ሆናለች ።

ጆንያችንን ፡ አጋብተን ፡ ከተመለስን ፡ በኋላ ፡ ዳንያር ፡ ሲመጣ ፡ እናያዋለን ፡ ረዥም ፡ መንገድ ፡ አቋርጦ ፡ እንደመጣ ፡ ሰው ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ ያነክስ ፡ ነበር ። እንደተጠጋነውም ፡ ዳንያር ፡ ፊቱን ፡ አኮማትሮና ፡ ከስክሶ ፡ በእሳታዊ ፡ አመለካከት ፡ ጃሚላን ፡ ይመለከታታል ። የታከተውን ፡ ወገቧን ፡ አርቃ ፡ የተሸበሸበ ፡ ቀሚሷን ፡ ወደታች ፡ ሳብ ፡ አደረገች ። ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ እሷን ፡ ማየቱ ፡ ይመስል ፡ ይመለከታታል ፤ ጃሚላ ፡ ግን ፡ ችላ ፡ አለችው ።

ቢሆንም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ትስቅበት ፡ ወይም ፡ ችላ ፡ ትለው ፡ ነበር ። ፈረሶችን ፡

ተቀምጠን ፡ ጉዞአችንን ፡ ስንቀጥል ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፡ ትጮኸብኛለች ፡ «ና ፡ እንሂድ!» ትላለች ፡ አለንጋዋን ፡ በራሷ ፡ ታዞርና ፡ ካፉአጨች ፡ በኋላ ፡ ግልቢያ ፡ ትጀምራለች ። እኔም ፡ እከተላታለሁ ። ዳንያርን ፡ እንደርስበትና ፡ የግልቢያችን ፡ አቧራ ፡ ከመንገዱ ፡ አውጥቶም ፡ እንደገና ፡ ከጥርጊያ ፡ ጎዳናው ፡ ለመግባት ፡ ያለበትን ፡ ድካም ፡ እናያለን ። ይህ ፡ ለቀልድ ፡ ቢደረግም ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ መታገስ ፡ ይችላሉ ። ዳንያርም ፡ ምንም ፡ ግድ ፡ አልነበረውም ። ጃሚላ ፡ በጋሪው ፡ ላይ ፡ ጎብታ ፡ ቀጥ ፡ ብላ ፡ ትቆምና ፡ ስትስቅበት ፡ ምንም ፡ ሳይበገር ፡ በሚያሳየው ፡ ፈገግታ ፡ እንጮሃለን ። ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ ብዬ ፡ ስመለከተው ፡ በአቧራው ፡ ውስጥ ፡ እሷን ፡ ሲመለከት ፡ አየዋለሁ ። በአስተያየቱም ፡ አንድ ፡ በጐ ፡ ነገርና ፡ ይቅርታ ፡ የተሞላበት ፡ ነው ። በበኩሌ ፡ ግን ፡ ብርቱና ፡ የተሰወረ ፡ ሀዘን ፡ እንደነበረበት ፡ ተሰምቶኛል ።

የቀለደችበትና ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ቸል ፡ ያለችበት ፡ ምክንያት ፡ አላስቀየመውም ። ሁሉንም ፡ ለመሸከም ፡ የማለ ፡ መስሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አዝኜለት ፡ ጃሚላን ፡ ገሠጽሁ ።

«ለምን ፡ ትቀልጅበታለሽ? እሱ ፡ ጸጥተኛና ፡ ትሑት ፡ ነው!»

«እ!» ትስቅና ፡ ትከሻዎችዋን ፡ ታነቃንቃለች ። «ለቀልድ ፡ ነው ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፌዛዛ ፡ ምንም ፡ አይደርስበት ፡» ትላለች ።

ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ደግሞ ፡ እኔም ፡ እቀልድበት ፡ ጀመር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእሱ ፡ አተኩሮ ፡ አመለካከት ፡ አሰጋኝ ። ጀንያን ፡ አንሥታ ፡ ከጀርባዋ ፡ ላይ ፡ ስትጭን ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ! እህል ፡ በምናስረክብበት ፡ ጣቢያ ፡ በነበረው ፡ ፍጅትና ፡ ጩኸት ፡ እንዲሁም ፡ ሰዎች ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተመላለሱ ፡ ያደርጉት ፡ በነበረው ፡ ዋካታ ፡ መካከል ፡ የጃሚላ ፡ እምነት ፡ ዝግተኝነቷና ፡ አረማመዷ ፡ ብዙዎችን ፡ አስገረመ ። እሷም ፡ ከጣቢያው ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ የነበረች ፡ ትመስል ፡ ነበር ።

ቆም ፡ ብሎ ፡ እሷን ፡ አለመመልከትም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። ከጋሪው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ጆንያ ፡ እህል ፡ ለማንሣት ፡ ጃሚላ ፡ ተንጠራር

ታ ፡ ብድግ ፡ ታደርግና ፡ ትመልሳለች ፡ ትከሻ
ዎችዋን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ታስጠጋና ፡ ራስዋን ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ ስታደርግ ፡ አንገቷ ፡ በሙ
ሉ ፡ ይታያል ፡ ፀሐይ ፡ ያንጨፈረረው ፡ ፀጉርዋ
ም ፡ መሬት ፡ ሊነካ ፡ ይደርስ ፡ ነበር ። ዳንያር
ም ፡ እንደ ፡ ማረፍ ፡ ፈልጐ ፡ ቆም ፡ ይላል ፡ ዳ
ሩ ፡ ግን ፡ ዓይኖቹ ፡ እስከ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ይከተ
ሉአት ፡ ነበር ። እሱም ፡ ማንም ፡ ያላየው ፡ ይ
መስለው ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ማናቸውን
ም ፡ ነገር ፡ ልብ ፡ አድርጌ ፡ ስለተመለከትሁና ፡
ስለተረዳሁ ፡ ያየሁትን ፡ ጠላሁ ። የተዋረድሁ
ም ፡ መሰለኝ ፤ ምክንያቱም ፤ ዳንያር ፡ የጃሚላ ፡
ዕኩያ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ስላልገመትሁት ፡ ነው ።

«እርሱ ፡ እንኳ ፡ ወደፏ ፡ አትኩሮ ፡ ከተ
መለከተ ፡ እንግዴህ ፡ በሌሎች ፡ ሰዎችማ ፡ ምን ፡
ይባላል!» ጨሰኩ ። በልጅነቴ ፡ ምክንያት ፡
የቅናት ፡ መንፈስ ፡ እምብዛም ፡ አላደፋፈረኝ
ም ። ልጆችም ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ የ
ሚወዱአቸው ፡ ይቀናሉ ። አሁን ፡ ግን ፡ ለዳ
ንያር ፡ በማዘን ፡ ፈንታ ፡ በጣም ፡ አጥብቄ ፡
ጠላሁት ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በቀለደበት ፡ ቁጥር ፡
ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ።



ዳሩ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀልዳችን ፡ ሁሉ ፡
በፍጹም ፡ ተደመሰሰ ። እህል ፡ ከተቆጠረባቸው ፡
ጆንያዎች ፡ መኻል ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡
ሰማንያ ፡ ነጥር ፡ ሂሣብ ፡ የሚመመዝን ። ጆን
ያ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጆንያ ፡ የተሠራውም ፡ ከሻካ
ራ ፡ ጠጉር ፡ ነበር ። ሁልጊዜም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡
እንሸከመው ፡ ነበር ። አንድ ፡ ቀን ፡ በውድማ
ው ፡ ላይ ፡ በዳንያር ፡ ልንቀልድበት ፡ ፈለግን ።
ይህን ፡ ትልቅ ፡ ጆንያ ፡ እጋሪው ፡ ላይ ፡ ጫነ
ውና ፡ ሌሎችን ፡ ጆንያዎችም ፡ ጨመርንበት ።
በመንገዳችን ፡ ላይም ፡ ጃሚላና ፡ እኔ ፡ ወዳን
ዲት ፡ የሩሲያ ፡ መንደር ፡ ጐራ ፡ ብለን ፡ ካን
ድ ፡ ሰው ፡ ጓሮ ፡ ገባንና ፡ ፍሬዎችን ፡ ወሰድን ፡
በመንገዳችን ፡ ሁሉ ፡ እየተሳሳቅን ፡ ስንጓዝ ፡
ከፍሬዎቹ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ወረወረች ። እንደተ
ለመደውም ፡ አቧራውን ፡ ቀስቅሰን ፡ ደረስን
በት ። ከኛው ፡ ጋር ፡ ሸለቆውን ፡ አቋርጦ ፡ ከባ
ቡር ፡ ጣቢያ ፡ መሻገሪያ ፡ ደረስ ። በሩም ፡ ዝ
ግ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ እስከ ፡ ጣቢያው ፡ ድረስ ፡
አብረን ፡ ሄድን ። የማራገፊያችን ፡ ጊዜ ፡ እስ
ኪደርስ ፡ ድረስም ፡ ስለ ፡ ከባዱ ፡ ጆንያ ፡ ፈጽ
መን ፡ ዘንግተን ፡ ነበር ። ጃሚላም ፡ ከፋኛ ፡

ጐሸመችኝና ፡ ወደ ፡ ዳንያር ፡ ፊቷን ፡ መለስ ፡ አድርጋ ፡ ራሷን ፡ አቀርቅራ ፡ ቆመች ። እሱም ፡ ከጋሪው ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። ጆንያውንም ፡ በማሰብ ፡ ይመለከተው ነበር ፤ በግልጽም ፡ ምን ፡ ላድርገው ፡ ይሆን ፡ ይል ፡ ነበር ። ዞሪያውን ፡ ተመልክቶ ፡ ጃሚላ ፡ ሳቅዋን ፡ ለመሰወር ፡ ስትሞክር ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ ቀልቶ ፡ ምን ፡ እንዳለ ፡ ተረዳ ።

«ሱሪህን ፡ ወደላይ ፡ ሳብ ፡ አድርገው ፡ አለበለዚያ ፡ እመንገድ ፡ ትጥለዋለህ ፡» ብላ ፡ ጃሚላ ፡ ጮኸች ።

ዳንያርም ፡ በቁጣ ፡ መልክ ፡ ተመለከተንና ፡ ያደረገውን ፡ ከመረዳታችን ፡ በፊት ፡ ከጋሪው ፡ ግርጌ ፡ የነበረውን ፡ ጆንያ ፡ ጐትቶ ፡ እዳር ፡ አኖረውና ፡ ባንድ ፡ እጁ ፡ ደግፎ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ዘለለ ። እጀርባውም ፡ ላይ ፡ አሳረፈው ። በመጀመሪያም ፡ ምንም ፡ የሚያደርገው ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብለን ፡ አምነን ፡ ነበር ። ሌሎችም ፡ በጭራሽ ፡ ምንም ፡ ልብ ፡ ያደረጉት ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። አንድ ፡ ጆንያ ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ሁሉም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ፡ ይባል ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ዳንያርም ፡ ከበሩ ፡ ላይ ፡



በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ጃሚላም ፡ ተከታትላው ፡ ደረሰችበት ፤

«ጆንያውን ፡ ልቀቀው ፡ እያልኩ ፤ እቀልድ ፡ ነበር!»

«ወይድ!» ብሎ ፡ አጉመተመተና ፡ ከትልቁ ፡ ሳንቃ ፡ ወርዶ ፡ ቆመ ።

«ተመልከቱ ፡ ተሸክሞታል ፡» ስትል ፡ ጃሚላ ፡ ጮኸች ፤ ሙከራዋም ፡ ራሷን ፡ ትክክለኛ ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ።

እስካሁን ፡ ድረስም ፡ በቀስታ ፡ ትስቅ ፡ ነበረች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሳቋ ፡ የተገታ ፡ ሆኖ ፤ ራስዋን ፡ ለማሳቅ ፡ የምታስገድድ ፡ ትመስላለች ።

አሁን ፡ ደግሞ ፡ ዳንያር ፡ በጥብቅ ፡ ማንከስ ፡ መጀመሩን ፡ ልብ ፡ አደረግን ። ስለዚህስ ፡ ለምን ፡ አስቀድመን ፡ አላሰብንበትም ፡ ይሆን? ስለዚያ ፡ የቂልነት ፡ አፈጻጸሜም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ራሴን ፡ ይቅር ፡ ማለት ፡ አልቻልኩም ። እኔ ፡ ነበርኩ ፤ እኔ ፡ ደደቡ ፡ ነበርኩ ፤ ስለዚያ ፡ ያሰብኩት!

«ተመለስ!» ስትል ፡ ጃሚላ ፡ ጮኸችበት ፡ አሳሳቅዋም ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ሳቅ ፡ ነበር ።

ዳንያር ፡ ግን ፡ ፊቱን ፡ አላዞረም ፡ ከእሱ ፡ በስተኋላ ፡ የቀረቡት ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስለሆነው ፡ ጉዳይ ፡ ማስታወስ ፡ አልችልም ። ዳንያርም ፡ ከከባዱ ፡ ሸክም ፡ ሥር ፡ አጐንብሶ ፡ አየሁት ፡ ራሱም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። በጥርሶቹም ፡ ከንፈሩን ፡ ነክሶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። በቀስታ ፡ አዘገመ ፡ የሚያዘግመውም ፡ ቁስለኛ ፡ ቅልጥሙን ፡ እያንቀሳቀሰ ፡ ነበር ። እያንዳንዱ ፡ እርምጃም ፡ ራሱን ፡ እስኪያንቀሳቅስ ፡ ድረስ ፡ ሕመም ፡ ይሰማውና ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ እንዳደረገ ፡ ለአንድ ፡ ሴኮንድ ፡ ጊዜ ፡ ያርፍ ፡ ነበር ። ከፍ ፡ እያለ ፡ በወጣ ፡ መጠን ፡ ይበልጥ ፡ ይሰቃይ ፡ ነበር ። ጆንያው ፡ አንገላትቶት ፡ ነበር ። ከፍርሃትና ፡ ከሐፍረት ፡ የተነሣ ፡ አፌ ፡ ደረቀ ። በፍርሃት ፡ እየተንቀጠቀጥሁ ፡ የሰውነቴ ፡ የደም ፡ ሥር ፡ ሁሉ ፡ የሸክሙን ፡ ከባድነትና ፡ በቆሰለው ፡ ቅልጥሙ ፡ ምክንያት ፡ ይሰማው ፡ የነበረውን ፡ አሰቃቂ ፡ ሥቃይ ፡ ይሰማኝ ፡ ነበር ። እንደገና ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለስ ፡ አደረገና ፡ ሳየው ፡ ማናቸው ፡ ነገር ፡ እፊቴ ፡ ላይ ፡ የሚንሳፈፍ ፡ መሰለኝ ። ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተመለሰና ፡ ምድርም ፡ ከግሮቼ ፡ ሥር ፡ የተላወሰች ፡ መሰለችኝ ።

አንድ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ራሴን ፡ ጠቅ ፡ ካደረገኝ ፡ በኋላ ፡ ራሴን ፡ አወቅሁ ፤ ወዲያውኑም ፡ ጃሚላን ፡ ለይቼ ፡ ላውቃት ፡ አልቻልኩም ፤ እንደ ፡ ነጭ ፡ ጨርቅ ፡ ነጥታብኝ ፡ ነበር ፡ የዓይንዋ ፡ ብረትም ፡ ሠፋብኝ ፤ ከንፈሮቿም ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሳቅዋ ፡ በኋላ ፡ አልተሰበሰቡም ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተቀባዩ ፡ ኃላፊ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ በር ፡ ተሩእሩጠው ፡ መጡ ። ዳንያርም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተራመደ ። ጆንያውንም ፡ ለማስተካከል ፡ ሲሞክር ፡ ሳለ ፡ በድንገት ፤ በአንደኛው ፡ ጉልበቱ ፡ በመብረክረክ ፡ ተንበረከከ ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ጃሚላ ፡ ፊቷን ፡ ጋረደች ።

«ተወው! ጆንያውን ፡ ልቀቅ!» ብላ ፡ ጮኸች ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዳንያር ፡ መልቀቅ ፡ አልፈለገም ። ከእሱ ፡ በኋላ ፡ የነበሩትን ፡ እንዳይጥላቸው ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ እንዲንሻተት ፡ ማድረግ ፡ ይችል ፡ ነበር ። በጃሚላ ፡ ድምጽም ፡ ወደ ፡ ፊ

ት ፡ ተራመደ ፤ ቅልጥሙንም ፡ ዘረጋውና ፡ ሌላ ፡ እርምጃ ፡ ለመራመድ ፡ በሞከረ ፡ ጊዜ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚያንቃንቀው ፡ ዛፍ ፡ ይንቃንቅ ፡ ጀመር ።

«የምናምንቴ ፡ ልጅ ፡ ልቀቀው!» ብሎ ፡ እህል ፡ ተቀባዩ ፡ ሹም ፡ ጮኸበት ።

«ልቀቀው! ልቀቀው!» ሁሉም ፡ ጮኹበት ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ዳንያር ፡ ተደላድሎ ፡ ቆመ ።

«የለም ፤ አይለቀውም!» አንድ ፡ ሰው ፡ አረጋግጦ ፡ በቀስታ ፡ ተናገረ ።

እዚያ ፡ ከበታቹና ፡ ከበላዩ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ አብሮ ፡ ካልተንከባለለ ፡ በቀር ፡ እንደማይለቀው ፡ ተገነዘቡ ። ዝም ፡ ተባለ ። ከግድግዳው ፡ ማዶ ፡ ሎኮሞቲቭ ፡ መኪና ፡ አፋጨ ።

ዳንያርም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተራመደ ። እሱም ፡ ቆርቆሮ ፡ ወደተከደነው ፡ ዛኒጋባ ፡ ለመድረስ ፡ በተደረደሩት ፡ ሳንቃዎች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ በር ፡ አመራ ። ሚዛኑን ፡ ለማስተካከልም ፡ ሁለት ፡ እርምጃ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ቆም ፡ ይል ፡ ነበር ። ኃይል ፡ ካገኘ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ጉዞውን ፡ ቀጠለ ። በስተኋላው ፡ የነበሩትም ፡ እሱ ፡ ሲቆም ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይቆጣም ፡ ነበር ። ይህ ፡ ይዞታም ፡ አዳከማቸው ፡ የመጨረሻ ፡ ብርታታቸውንም ፡ ጨረሰባቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ማንኛቸው ፡ አልተቆጡም ፡ ወይም ፡ አልተራገሙም ፡ ነበር ። ሸክማቸውን ፡ ተሸክመው ፡ ወደፊት ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ። አካሄዳቸው ፡ ሊታይ ፡ በማይቻል ፡ ገመድ ፡ እንደተሳሰሩ ፡ መስለውና ፡ ባንድ ፡ አደገኛ ፡ መተላለፊያ ፡ ላይ ፡ እንደሚያልፉ ፡ ሆነው ፡ አንድ ፡ የሚያድጥ ፡ መንገድ ፡ ያለበትና ፡ ያንዱ ፡ ሕይወት ፡ በሌላው ፡ ሕይወት ፡ የተማመነ ፡ ሆኖ ፡ ይገመት ፡ ነበር ። ባካሄዳቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሆነ ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የሌለው ፡ እርምጃ ፡ ነበራቸው ። አንድ ፡ እርምጃ ፤ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ከዳንያር ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ቀርቷቸው ፡ ነበር ።

ከታሰበው ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ ጥቂት ፡ እንደቀረው ፡ ዳንያር ፡ ዛለ ፤ ቁስለኛው ፡ ቅልጥሙም ፡ መታዘዝ ፡ ተሣነው ። ጆንያውን ፡ ካለቀቀው ፡ በቀር ፡ በእርግጥ ፡ መውደቁ ፡ ነበር ።

ጃሚላ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ክንዶቿን ፡ ዘርግታ ፡ ይህ ፡ የሚረዳው ፡ መስሏት ።

«ሩጡ! ከኋላው ፡ ደግፉት!» ብላ ፡ ጮኸች ።

እኔው ፡ በበሩ ፡ ሮጥሁ ። በሰዎችና ፡ በጃንያዎች ፡ መኻል ፡ እየተጋፋሁ ፡ በመጨረሻ ፡ ደረስኩለት ። በክንዱ ፡ ሥር ፡ ተመለከተኝ ። በጠቆረውና ፡ በራሰው ፡ ግንባሩ ፡ ላይም ፡ የደም ፡ ስሮቹ ፡ ተቆጥተው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። ደም ፡ የመሰሉት ፡ ዓይኖቹም ፡ በቁጣ ፡ ገረፉኝ ። በስተኋላው ፡ በኩል ፡ ጀንያውን ፡ ልደግፍለት ፡ ፈለግሁ ።

በቁጣ ፡ ቃል ፡ «ወዲያ ፡ ሂድ!» ብሎ ፡ ተላወሰ ።

በመጨረሻም ፡ እያነከሰና ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ እየተነፈሰ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ክንዶቹ ፡ ዝለው ፡ በጐኖቹ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ነበር ። ሰዎችም ፡ መንገድ ፡ ስለለቀቁለት ፡ አለፈ ፤ የጣቢያው ፡ ሹም ፡ ግን ፡ ሊታገሥ ፡ ስላልቻለ ፤

«አብድሃል? እኔስ ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ አልመስልህም? እዚያ ፡ ታች ፡ ጀንያውን ፡ እንድትገለብጥ ፡ አልፈቅድልህም ፡ ነበርን? እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጀንያዎች ፡ የምትሸከምበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነው?» አለው ።

«ይህ ፡ የኔ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡» ብሎ ፡ ዳንያር ፡ በእርጋታ ፡ መለሰለት ።

ምራቁን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ተፋና ፡ ወደ ፡ ጋሪው ፡ አመራ ። ዳንያርም ፡ የእኛን ፡ ቀልድ ፡ እንደ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ቆጥሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ በመፈጸሙ ፡ በእሱ ፡ ተቆጥተን ፡ ከማፈራችን ፡ የተነሣ ፡ ቀና ፡ ብለን ፡ ልናየው ፡ አልደፈርንም ።

ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ በጸጥታ ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ ተጓዝን ። የዳንያር ፡ ሁናቴ ፡ እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ እስካሁን ፡ ቂም ፡ ይዞብን ፡ እንደሆነና ፡ ወይም ፡ ያደረግንበትን ፡ አድራጐት ፡ ረስቶ ፡ እንደሆነ ፡ ለይተን ፡ ማወቅ ፡ አልቻልንም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሕሊናችን ፡ ተክዞ ፡ ተጐሣቁለንም ፡ ነበር ።

በማግሥቱ ፤ በውድማው ፡ ላይ ፡ እህል ፡ ስንጭን ፡ ጃሚላ ፡ ገደ ፡ ቢሉን ፡ ጀንያ ፡ አነሣችና ፡ ጫፉን ፡ በእግርዋ ፡ ረግጣ ፡ ቀደደችው ።

«ይኸውልህ ፤ አሮጌ ፡ ጀንያህን ፡ ውሰድ!» ብላ ፡ በተገረመው ፡ መዛኝ ፡ ሰውዬ ፡ እግር ፡

ሥር ፡ ወረወረችውና ፡ «ለጓድ ፡ መሪውም ፡
ዳግም ፡ እንዳያስተን ፡ ንገረው!» አለች ።
«ምን ፡ ሆነሻል? ምንስ ፡ ደረሰብሽ?»
«ምንም ፡ አልደረሰብኝም ።»

ቀጥለው ፡ በነበሩት ፡ ቀኖች ፡ ሁሉ ፡ ዳን
ያር ፡ እንደተለመደው ፡ በጸጥታና ፡ በእርጋታ ፡
ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፤ በምንም ፡ ሁናቴ ፡ ስሜ
ቱን ፡ አይገልጥም ፡ ነበር ፤ ቅልጥሙ ፡ ግን ፡
በተለይም ፡ ጀንያ ፡ ሲሸከም ፡ መታመሙ ፡ በጉ
ልህ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። የዱሮው ፡ ቁስሉ ፡ እን
ደገና ፡ ፈነዳ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ዘወትር ፡ የበ
ደላችን ፡ ማስታወሻ ፡ ሆነን ። ዳኑ ፡ ግን ፡ ቢስ
ቅና ፡ ቢቀልድ ፡ ኖሮ ፡ በደላችን ፡ ይቀለን ፡
ነበር ።

ጃሚላ ፡ ደግሞ ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ እ
ንዳልሆነ ፡ ታስመስል ፡ ነበር ። ኩሩዪቱ ፡ ሴት ፡
እንደ ፡ ዘወትር ፡ ሁሉ ፡ ትስቅ ፡ ነበረች ። እኔ ፡
ግን ፡ መንፈሷ ፡ የቃዠ ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘብሁ ።

ዘግየት ፡ ብለን ፡ ከማቢያው ፡ ወደ ፡ ቤታ
ችን ፡ ስንጓዝ ፤ ዳንያር ፡ ከፊታችን ፡ ይጓዝ ፡
ነበር ። ሌሊቱም ፡ ውብ ፡ ነበር ። እነዚህን ፡ የ



ነሐሴ ፡ ሌሊቶች ፡ የሩቅ ፡ ቅርብ ፡ መስለው ፡
የሚታዩትን ፡ ብሩሃን ፡ ከዋክብት ፡ የማያውቅ ፡
ማን ፡ ይገኛል! አንዲት ፡ ኮከብ ፡ ነበረች ፤ ዙሪ
ያዋንም ፡ ውርጭ ፡ የሠፈረባት ፡ ትመስላለች ፡
ውርጫማዎቹ ፡ ጨረሮችዋም ፡ ከጨለማው ፡
ሰማይ ፡ ታች ፡ ባለችው ፡ ምድር ፡ በመገረም ፡
ያበሩ ፡ ነበር ። በሽለቆው ፡ አቋርጠን ፡ ስንጓ
ዝም ፡ በዓይኖቼ ፡ እኩተላት ፡ ነበር ። ፈረሶቹ
ም ፡ እቤት ፡ ለመድረስ ፡ በሶምሶማ ፡ ሲራመዱ ፡
በኩቴአቸው ፡ ጠጠሮችን ፡ ያፍጩ ፡ ነበር ። የ
ሜዳው ፡ ነፋስ ፡ ደግሞ ፡ የአበቡትን ፡ ዛፎች ፡
መዓዛ ፤ የአሸተውን ፡ የስንዴ ፡ ሽታ ፤ ያቀብለን ፡
ስለነበረ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከፈረሶቹ ፡ ላብና ፡ ከቅ
ጥራት ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ራሳችንን ፡ አዞረው ።

ባንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በጨለማ ፡ ቁጥ
ቋጦ ፡ የተሸፈኑ ፡ ፊፋዎች ፡ ከመንገዱ ፡ ላይ ፡
ተንጠልጥለው ፡ ነበር ። ከበታቻችንም ፡ ችፍ
ግ ፡ ካሉ ፡ የአበባ ፡ ቁጥቋጦችና ፡ ረግረግም ፡
ዛፎች ፡ እረፍት ፡ የሌለው ፡ ኩርኩሬው ፥ ይገ
ሠግሥ ፡ ነበር ። አልፎ ፡ አልፎም ፡ የባቡር ፡
ጩኸት ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ የባቡሩ ፡ መንኮራኩ
ር ፡ ድምጽም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ከሩቅ ፡ ተሰማ ።

በቀዝቃዛ ፡ ወቅት ፡ ፈረሶችን ፡ መጋለብ ፡ አስደሳች ፡ ነው ፤ የሚንቀሳቀሱትን ፡ ፈረሶች ፡ ጀርባዎች ፡ መመልከት ፡ የነሐሴን ፡ ሌሊት ፡ ሽታ ፡ ማሽተትና ፡ ማዳመጥ ፡ መልካም ፡ ነው ። ጀሚላም ፡ ከፊቴ ፡ ነበረች ። ልጓሙ ፡ አምልጦአት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ትዳብስና ፡ በዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ታዜም ፡ ነበር ። ዝምታችን ፡ የከበዳት ፡ መሆኑ ፡ ተሰማኝ ። በእንደዚህ ፡ ሌሊት ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ የማይቻል ፡ ነው ፤ ሌሊቱ ፡ የተፈጠረው ፡ ለማዜም ፡ ነው ።

ማዜም ፡ እንደጀመረችም ፡ ዜማዋ ፡ በፊት ፡ የነበረን ፡ ቀና ፡ መንፈስ ፡ እንዲመለስልንና ፡ አንድነታችን ፡ እንዲገለምስ ፡ የበደል ፡ አድራጎቷንም ፡ ለማጥፋት ፡ እንደነበረ ፡ ይገመታል ። እንደ ፡ መረዋ ፡ የሚጮህ ፡ ድምጽ ፡ ነበራት ፡ ያዜመችውም ፡ በመንደራችን ፡ ይዘፈን ፡ የነበረውን ፡ ዜማ ፡ ነው ፡ «ስታልፍ ፡ የራስ ፡ ሻሼን ፡ አውለበልባለሁ ።» «ፍቅሬም ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ሄዶአል ።» ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ዜማዎችን ፡ ታውቅ ፡ ስለነበረ ፡ ሁሉንም ፡ በተራ ፡ አዜመች ። ስታዜማቸውም ፡ ስሜት ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ መስማቱ ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ።



በድንገት ፡ ዜማዋን ፡ አቋርጣ ፤ «ዳንያር!» ብላ ፡ ተጣራች ።

«ሄይ ፤ ዳንያር ፡ ሆይ ፤ ለምን ፡ አንድ ፡ ዜማ ፡ አታዜምም? ወጣት ፡ አይደለህም?» አለችው ።

ግር ፡ ብሎት ፡ ፈረሱን ፡ ገታ ፡ አድርጎ ፡ «ጀሚላ ፤ አንቺ ፡ ዝፈኚ ፤ እኔ ፡ አዳምጣለሁ ።» አላት ።

«እኛ ፡ ጀሮች ፡ የሌሉን ፡ ይመስልሃል? ማንም ፡ አያስገድድህም ፤ ካልፈቀድህ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ ትችላለህ!» አለችና ፡ ጀሚላ ፡ ዘፈንዋን ፡ ቀጠለች ።

እንዲዘምር ፡ የጠየቀችበትን ፡ ምክንያት ፡ ማን ፡ ያውቃል! ምናልባት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብልጭ ፡ ብሎባት ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ልታናግረው ፡ ይሆናል። ምናልባት ፡ የመጨረሻው ፡ አስተያየት ፡ በሀሳብዋ ፡ ተቀርጾ ፡ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፡ ወዲያውኑ ፡ ቀጥላ ፡ ስለጮኸች ፡ ነው ።

«ዳንያር ፡ ሆይ ፤ እስቲ ፡ ንገረኝ ፤ ከሴት ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡ ይዞህ ፡ ታውቃለህ?» አለችና ፡ ሣቅ ፡ አለች ።

እሱ ፡ ዝም ፡ አላት ፡ እሷ ፡ ጃሚላም ፡ ዝም ፡ አለች ።

«በእርግጥ ፡ እንዲዘምር ፡ የምትጠይቀው ፡ ሰው ፡ አገኘች ፡» ብዬ ፡ አሰብኩ ።

ፈረሶቹም ፡ መንገዳችን ፡ ከሚያቋርጠው ፡ ወንዝ ፡ አዝግመው ፡ ደረሱ ። ኮቴአቸውም ፡ ርጥብና ፣ ብር ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ ያላቸውን ፡ ደንጊያዎች ፡ አማቱ ። ወንዙን ፡ ከተሻገርን ፡ በኋላ ፡ ዳንያር ፡ ፈረሶቹን ፡ መታና ፡ በለስላሳና ፡ በቁጥብ ፡ ድምጽ ፡ ማዜም ፡ ጀመረ ፡ ዜማውንም ፡ መንገዱ ፡ ሲያደናቅፈው ፡ ብቻ ፡ ያቆም ፡ ነበር ። ዜማውም ፣

ተራራዎቼ ፣ ሰማያዊ ፡ ነጭ ፡ ተራራዎቼ ፣ የአባቶቼና ፡ የቅድምአያቶቼ ፡ አገር ፣ የሚል ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተንገዳግዶ ፡ ሳለና ፡ ከዚህ ፡ የሚቀጥሉትን ፡ ቃላቶች ፡ በቀላል ፡ ዜማ ፡ አዜመ ፣ ተራራዎቼ ፡ ሰማያዊ ፡ ነጭ ፡ ተራራዎቼ ፣ የሕይወቴ ፡ አንቀልባ ።

አሁንም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ያስደነገጠው ፡ መሰሎ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

የታወከበትንም ፡ በግልጥ ፡ አሰብኩ ።



የሆነ ፡ ሆኖ ፡ በመቆሙ ፡ በውስጡ ፡ የሚላወስ ፡ ነገር ፡ ነበር ፣ የፍርሃት ፡ ዜማው ፡ ሊገልጥበት ፡ ቻለ ። ምናልባትም ፡ መልካም ፡ ድምጽ ፡ ነበረው ። ዳንያር ፡ ለመሆኑ ፡ ማመንም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ።

«በጄ! በጄ!» ብዬ ፡ ጮኽኩ ።

«ከዚህ ፡ በፊት ፡ ለምን ፡ አላዜምክም? አዚም! አዚም! በእውነት ፡ ትችላለህ!» ብላ ፡ ጃሚላ ፡ ጮኸች ።

ሸለቆው ፡ አለቀ ፡ ወደፊት ፡ ብርሃን ፡ አለ ። ለስላሳ ፡ ነፋስ ፡ ከሸለቆው ፡ ይነፍስ ፡ ነበር ። ዳንያርም ፡ ማዜም ፡ ጀመረ ። እንደ ፡ ቀድሞው ፡ በፍርሃት ፡ መልክና ፡ ባልተረጋገጠ ፡ ሁናቴ ፡ ሆኖ ፡ ማዜሙን ፡ ቀጠለ ፣ ጥቂት ፡ በጥቂትም ፡ ድምጹ ፡ እየጐላ ፡ መሄድ ፡ ጀመረ ። ሸለቆውንም ፡ ሞላው ፡ በአሻጋሪ ፡ የነበሩት ፡ ፈፋዎችም ፡ ዜማውን ፡ ያስተጋቡ ፡ ጀመር ።

የዜማውን ፡ ስልት ፡ አደነቅሁ ።

ምን ፡ ብዬ ፡ መጥራት ፡ እንደሚገባኝ ፡ አላወቅሁም ፣ አሁንም ፡ አላውቅም ፡ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግሞ ፡ ድምጽ ፡ ብቻ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ አረጋግጬ ፡ መወሰን ፡

አልችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያች ፡ ነፍስ ፡ የወጣው ፡ ድምጽ ፡ እንደ ፡ እሱ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መላከክ ፡ የሚችልና ፡ ያንድን ፡ ሰው ፡ ውስጣዊ ፡ እንፋሎት ፡ ለሕያውነት ፡ ማብቃት ፡ የሚችል ፡ ዜማ ፡ ነበር ።

የዳንያርን ፡ ዜማ ፡ እንደገና ፡ ለመፍጠር ፡ ብችል! ቃላት ፡ አልነበሩበትም ፡ ያለ ፡ ቃላት ፡ ጥልቅ ፡ የሆነውን ፡ የሰብአዊ ፡ ነፍስ ፡ ስሜትን ፡ ገለጠ ። አስቀድሞም ፡ ሆነ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ዜማ ፡ ሰምቼ ፡ አላውቅም ። እሱም ፡ ኪርጊዝ ፡ ወይም ፡ ካዛኽ ፡ አልነበረም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከሁለቱም ፡ የተጨለፈ ፡ ነገር ፡ ነበረበት ። ዳንያርም ፡ የሁለቱን ፡ ዝምድናቸው ፡ የተቃረበውን ፡ ነገዶች ፡ ዜማዎች ፡ ወስዶ ፡ በአዲስ ፡ የዜማ ፡ ስልት ፡ ስላስማማቸው ፡ እሱ ፡ የፈጸመው ፡ አድራጐት ፡ ከቶ ፡ በማንም ፡ ሊደረግ ፡ የማይቻል ፡ ነው ። ይህም ፡ የተራራዎችና ፡ የሜዳዎች ፡ ዜማ ፡ ሆኖ ፡ እንደ ፡ ኪርጊዝ ፡ ተራራዎች ፡ ከፍ ፡ ያለና ፡ እንደ ፡ ካዛኽ ፡ ሜዳዎች ፡ ይሰፋ ፡ ነበር ።



በአዳመጥኩትም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጡን ፡ አደንቅ ፡ ነበር ፤ «በእውነትም ፡ ዳንያር ፡ እንዲህ ፡ ነበር! ማንስ ፡ ሊያምነው ፡ ይችል ፡ ነበር?»

በለስላሳው ፡ መንገድ ፡ አድርገን ፡ ሜዳዎችን ፡ መሻገራችን ፡ ነበር ። የዳንያርም ፡ ድምጽ ፡ ሰፈፈ ፤ ደስ ፡ በሚያሰኝ ፡ ስልት ፡ ዜማዎቹ ፡ ተከታትለው ፡ ጐረፉ ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ተሰጥዎ ፡ ያለው ፡ ነው? ምንስ ፡ ደረሰበት? እሱም ፡ ይህች ፡ ዕለትና ፡ ሰዓት ፡ እስኪደርስለት ፡ ድረስ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር?

ሰዎችን ፡ በማስከፋት ፡ ፈገግ ፡ እንዲሉ ፡ ያደረጋቸውን ፡ ምክንያት ፡ በድንገት ፡ አስተዋልኩ ፤ አላሚነቱ ፡ ብቸኝነትን ፡ መውደዱ ፡ ጭምት ፡ መሆኑ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። በምሽት ፡ ከኮረብታ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በመመልከት ፡ ሌሊቶቹንም ፡ ብቻውን ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ ማሳለፉ ፡ ለሌሎች ፡ መሰማት ፡ የማይችሉትን ፡ የዜማ ፡ ስልቶች ፡ ማዳመጡና ፡ ዓይኖቹ ፡ በድንገት ፡ የሚፈጡበትና ፡ ቅንድቦቹ ፡ የሚኮማተሩበትን ፡ ምክንያት ፡ ማወቅ ፡ ቻልኩ ። ይህ ፡ ሰወዬም ፡ በፍቅር ፡ የተነደፈ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የነበረው ፡ ፍቅር ፡ አለመሆ

ኑን ፡ ተሰማኝ ፤ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ነ
በር ። እሱም ፡ የሕይወትና ፡ የምድር ፡ ፍቅር ፡
ነበር ። አዎ ፤ ይህን ፡ ፍቅር ፡ በውስጡ ፡
ይዞት ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሙዚቃም ፡ የሚመ
ራው ፡ ፋናው ፡ ነበር ። ምንም ፡ ግድ ፡ ያል
ነበረው ፡ ሰው ፡ ድምጹ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡
ከፍ ፡ ቢልም ፡ የእሱን ፡ ያህል ፡ ማዜም ፡ አ
ይችልም ።

የመጨረሻው ፡ የዜማ ፡ ስልቱ ፡ ያበቃ ፡
ሲመስል ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ማዕበል ፡ ዕንቅል
ፍ ፡ የያዛቸውን ፡ ሜዳዎች ፡ የሚያነቃ ፡ ይመስ
ላል ። ተወዳጅ ፡ የሀገር ፡ ዜማም ፡ በደስታ ፡
ተደመጠ ። ለአጨዳ ፡ የደረሰው ፡ የስንዴ ፡ አ
ዝመራ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሐይቅ ፡ ውሃ ፡ ተነጣ
ልሎ ፡ ይታያል ፡ የጐሕ ፡ ብርሃንም ፡ ከሜዳው ፡
ላይ ፡ ጮራውን ፡ ፈነጠቀ ። ያረጁ ፡ ዛፎች ፡ ከ
ወፍጮው ፡ አጠገብ ፡ የቅጠሎችን ፡ ድምጽ ፡
አሰሙ ። ከወንዙ ፡ ማዶም ፡ የገበሬዎቹ ፡ ሠፈ
ር ፡ እሳት ፡ በመጥፋት ፡ ላይ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡
በግልጽ ፡ ሊታይ ፡ የማይችል ፡ ፈረሰኛም ፡ በወ
ንዙ ፡ ዳር ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አቅጣጫ ፡ ፈረሱ
ን ፡ ይጋልብ ፡ ነበር ። እሱም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡



ለዓይን ፡ አይታይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡
ደግሞ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። ነፋሱንም ፡ በመዘ
ርዘር ፡ ላይ ፡ የነበሩት ፡ የፍራፍሬዎችና ፡ የማ
ሽላ ፡ ሽታ ፡ የእበት ፡ ጥፍጥፍ ፡ ትኩስ ፡ መዓዛ ፡
ከብዶት ፡ ነበር ።

ዳንያርም ፡ ማዜሙን ፡ ቀጠለ ፡ ማነኛው
ንም ፡ ዘንግቶ ፤ ደስተኛዪቱ ፡ የነሐሴ ፡ ሌሊት ፡
ብቻ ፡ በጸጥታ ፡ ታዳምጠው ፡ ነበረች ። ፈረሶ
ቹም ፡ ሳይቀሩ ፡ ዜማውን ፡ እንዳያደናቅፉት ፡ አ
ረማመዳቸውን ፡ ከለወጡ ፡ ቆይተዋል ።

በድንገት ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ያዜም ፡ የነበረው ፡
ድምጹ ፡ ዜማውን ፡ አቋርጦ ፡ በደንጋጤ ፡ ጮ
ኸና ፡ ፈረሶቹን ፡ መታቸው ። እኔም ፡ ጃሚላ ፡
ተከትላው ፡ የምትጋልብ ፡ መስሎኝ ፡ ልከተላት ፡
ቃጥቼ ፡ ነበር ፤ እሷ ፡ ግን ፡ አልተላወሰችም ።
ራስዋን ፡ ደፋ ፡ አድርጋ ፡ እንደተቀመጠች ፡
ቀረች ። ሁናቴዋም ፡ በአየር ፡ የተሠራጩትን ፡
የመጨረሻዎቹን ፡ የዜማ ፡ ስልቶች ፡ የምታደ
ምጥ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ዳንያርም ፡ ሔደ ። ከ
መንደሩ ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስም ፡ ማንኛችን
ም ፡ ምንም ፡ አልተናገርንም ፡ ነበር ። ቃላ
ት ፡ ብቻቸውን ፡ የሰውን ፡ ስሜት ፡ መግ

ለጽ ፡ ስለማይችሉ ፡ መነጋገር ፡ አላስፈለገም ፡
ነበር ።

ከዚያች ፡ ዕለት ፡ ወዲህ ፡ በሕይወታችን ፡
ለውጥ ፡ የደረሰብን ፡ መስሎን ፡ ነበር ። አንድ ፡
የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡
በማድረግ ፡ የምጠባበቅ ፡ እመስል ፡ ነበር ። ጧ
ት ፡ ጧትም ፡ በውድማው ፡ ጋሪዎቻችንን ፡ እን
ጭንና ፡ ወደ ፡ ጣቢያው ፡ ወስደን ፡ ለመመለ
ስ ፡ እንጣደፍ ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ ወደ ፡ ቤታ
ችን ፡ ስንመለስ ፡ የዳንያርን ፡ ዜማ ፡ ለማዳመጥ ፡
ነው ። ድምጹም ፡ ከሰውነቱ ፡ እንደ ፡ አንደኛ
ው ፡ ብልት ፡ ሆኖ ፡ በምዘዋወርበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ አ
ብሮኝ ፡ ይሄድ ፡ ነበር ። ጧት ፡ ተነሥቼ ፡ ጤዛ
ማ ፡ በሆኑት ፡ ጨፌዎች ፡ ፈረሶቹን ፡ ለማምጣት ፡
ስሮጥም ፡ አብሮኝ ፡ ነበር ፤ የምትስቀው ፡ ፀሐ
ይ ፡ ከተራራዎቹ ፡ ጀርባ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ ሰላም ፡
ባለች ፡ ጊዜ ፡ አብሮኝ ፡ ነበር ። ወርቃዊ ፡ የሆ
ኑት ፡ የስንዴ ፡ ዛላዎች ፡ ተወቅተው ፡ ለነፋስ ፡
ሲመነሹ ፡ ሁሉና ፡ በሜዳው ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡
በክብ ፡ የምትዞረውን ፡ አሞራ ፡ ሳይ ፡ በጠቅ
ላላው ፡ በማናቸው ፡ ሁናቴ ፡ ባየሁትና ፡ በሰ
ማሁት ፡ ስለ ፡ ዳንያር ፡ ዜማ ፡ አስብ ፡ ነበር ።



ማታ ፡ ማታ ፡ ሸለቆውን ፡ አቋርጠን ፡ ስ
ንጋልብም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ ያለፍኩ ፡ ይመ
ስለኛል ። ዓይኖቼን ፡ በከፊል ፡ ጨፍኜ ፡ እዳ
ምጠዋለሁ ። እዚያም ፡ ከልጅነቴ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡
የማውቃቸው ፡ ነገሮች ፡ ይቀሰቅሱኛል ። እሁ
ን ፡ የፀደይ ፡ ደመናዎች ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ያ
ለው ፡ ጢስ ፡ መስለው ፡ ከድንኳኖች ፡ በላይ ፡
እየተንጐማለሉ ፤ ያንዣብባሉ ፡ የፈረስ ፡ መን
ጋዎችም ፡ እንደ ፡ ደወል ፡ በምትጮኸው ፡ ም
ድር ፡ ላይ ፡ እየሮጡ ፡ ወደ ፡ በጋ ፡ ወራት ፡ መ
ሰማሪአቸው ፡ ይሰማራሉ ፤ ሰንጋ ፡ ፈረሶችም ፡
ረዣዥም ፡ ጋማና ፡ አመለካከታቸው ፡ የሚጋረ
ፈው ፡ ፈረሶችም ፡ ባዝራዎችን ፡ ይቀድሟቸዋ
ል ። የበግ ፡ መንጋዎችም ፡ በዝግታ ፡ በኮረብ
ቶቹ ፡ ላይ ፡ ይበተናሉ ። ካንድ ፡ ገደልም ፡ አን
ድ ፡ ፏፏቴ ፡ ይወርዳል ፤ ነጩ ፡ አረፋም ፡ ያን
ጸባርቃል ። ፀሐይም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ መርፌ ፡
በሆኑት ፡ ሣሮች ፡ በቀስታ ፡ ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ ት
ጠልቃለች ። በእሳታዊው ፡ አድማስ ፡ ጫፍ ፡
ላይ ፡ የሚጋልብ ፡ አንድ ፡ ብቸኛ ፡ ሰውም ፡ እ
ሷን ፡ የሚከታተል ፡ ይመስላል ። ፀሐይን ፡ ለ
መንካትም ፡ እጁን ፡ መዘርጋት ፡ ብቻ ፡ ያስፈ

ልገዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እሱው ፡ ራሱም ፡ በፀሐይ ፡ ደበዝበዝ ፡ ባለው ፡ ብርሃን ፡ ይጠፋል ።

ከወንዙ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ያለው ፡ የካዛኽ ፡ ሜዳ ፡ ሠፊ ፡ ነው ። ተራራዎቹን ፡ ገምሶ ፡ ለራሱ ፡ በቂ ፡ ሥፍራ ፡ ይዙአል ፡ በመኻላቸውም ፡ ባዶ ፡ ምድረ ፡ በዳን ፡ ፈጥሮአል ።

የመጀመሪያው ፡ የሚታወሰው ፡ የበጋ ፡ ወቅት ፡ የጦርነት ፡ እሳት ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጦ ፡ ለብልቦት ፡ ነበር ። የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ፈረሶች ፡ በጋለ ፡ አቧራ ፡ ደመናነት ፡ ሜዳውን ፡ አጨልመውት ፡ ነበር ፤ ፈረሰኞቹም ፡ በየአቅጣጫው ፡ ይጋልቡ ፡ ነበሩ ። በተቃራኒው ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ካዛኽ ፡ በከብት ፡ እረኞች ፡ ጩኸት ፡ ዓይነት ፡ እየጮኸ ፡ ሲሮጥ ፤ ያየሁትን ፡ አስታውሳለሁ ።

«ኪርጊዚያኖች ፡ ሆይ! ፈረሶቻችሁን ፡ ጫኑ ፤ ጠላት ፡ ደርሶብናል!» ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ በአቧራ ፡ ደመናና ፡ በትኩስ ፡ አየር ፡ ማዕበል ፡ ውስጥ ፡ ጠፋ ።

ሰው ፡ ሁሉም ፡ ይህን ፡ አደጋ ፡ ለመቀበል ፡ ተነሣ ። የመጀመሪያው ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡



ዋካታ ፡ ተከተለውና ፡ ከተራራው ፡ ወርዶ ፡ ሸለቆቹን ፡ አቋርጦ ፡ ተሻገረ ። በብዙ ፡ ሺ ፡ የሚቆጠሩ ፡ የሀገር ፡ ጀግኖችም ፡ ኮርቻዎችን ፡ ተጠጉ ፤ በግንባራቸውም ፡ ቀያይ ፡ የስንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ጨርቆች ፡ ተውለበለቡ ። በስተኋላ ፡ የፈረሶቹ ፡ ኮቴዎች ፡ ከቀሰቀሱት ፡ አቧራ ፡ ማዶ ፡ የእናቶቻቸውና ፡ የሚስቶቻቸው ፡ ልቅሶና ፡ ዋይታ ፡ ደረታቸውን ፡ እየመቱ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ሲንከባለሉ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። «ሜዳው ፡ ይጠብቃችሁ! የጦረኛችን ፡ የማናስ ፡ ውቃቢ ፡ ይጠብቃችሁ!»

ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ የሄዱበት ፡ መራር ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ቀረ ።

ለዚች ፡ ለታላቅ ፡ ዓለም ፡ ምድራዊት ፡ ውብትና ፡ ትካዜ ፡ የዳንያር ፡ ዜማ ፡ ዓይኖቼን ፡ ከፈተልኝ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ የት ፡ ተምሮ ፡ ነበር? ከማንስ ፡ ሰማው ፡ ይሆን? አገሩን ፡ የሚወድ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እትውልድ ፡ አገሩ ፡ ለመግባት ፡ የናፈቀና ፡ በፈቅሯም ፡ የተሰቃየ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ አደረብኝ ። በሚያዜምበት ፡ ጊዜም ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ እንደሚንከራተት ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ታየኝ ። ምናልባትም ፡

እነዚህ ፡ የትውልድ ፡ ሀገሩ ፡ ዜማዎች ፡ እስቀድመው ፡ በነፍሱ ፡ ላይ ፡ ተቀርጸውበት ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ እሳታዊውን ፡ የጦርነት ፡ ጉዳና ፡ በተከተለበት ፡ ጊዜም ፡ ይሆናል ።

ምድርን ፡ እንደሚወድዳት ፡ ያህል ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ አመስጋኝ ፡ ልጅ ፡ ሁኜ ፡ በዜማው ፡ ማማር ፡ ጋደም ፡ ብዬ ፡ ምድርን ፡ በኃይል ፡ እንዳቅፋት ፡ ፈለግሁ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ በውስጤ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ተሰማኝ ፤ ቃላት ፡ ላገኝለት ፡ የማይቻለኝ ፡ ነገር ፡ ሆነብኝ ፤ ልቃወመውም ፡ የማልችል ፡ ሆነ ። ስለ ፡ ራሴ ፡ ለመግለጥ ፡ አስገዳጅና ፡ ጉትጓች ፡ ሆነብኝ ። አዎ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ዓለምን ፡ እንዳይና ፡ እንድቀምስም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ስለ ፡ ራሴ ፡ ለመግለጽና ፡ ሌሎችም ፡ የእኔን ፡ ራዕይ ፡ እንዲያዩ ፡ ለማድረግ ፡ ሀሳቤንና ፡ ስሜቴን ፡ በመግለጽ ፡ ዳንያር ፡ ማድረግ ፡ እንደቻለው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ምድራችን ፡ ውበት ፡ ለሰዎች ፡ ለመንገር ፡ ፈቀድሁ ። ሠዓሊ ፡ ለመሆን ፡ መፈጠሬን ፡ ገና ፡ ስላለወቅሁት ፡ ባንድ ፡ ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ በፍርሃትና ፡ በደስታ ፡ እስትንፋሴን ፡ እገታለሁ ።



ሁልጊዜም ፡ ሥዕል ፡ መንደፍን ፡ እወድ ፡ ነበር ። መግለጫዎችንም ፡ በደብተሬ ፡ ላይ ፡ እቀዳቸዋለሁ ። ልጆች ፡ ሁሉም ፡ «ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ ቅጆች ፡ ናቸው ፡» ተባባሉ ። መምህራኑም ፡ እግድግዳ ፡ ላይ ፡ ለሚለጠፉት ፡ ጋዜጦች ፡ የሳልኳቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ ተመልክተው ፡ መምህራኑ ፡ አመስገኑኝ ። ጦርነቱ ፡ በፈነዳ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአገልግሎት ፡ ተጠሩ ። ስለዚህ ፡ ትምህርቴን ፡ አቋርጬ ፡ በኅብረት ፡ እርሻ ፡ ድርጅት ፡ ለማገልገል ፡ ተሠማራሁ ። በእኔው ፡ ዕድሜ ፡ የነበሩት ፡ ልጆችም ፡ እንደዚሁ ፡ አደረጉ ። ስለ ፡ ሥዕል ፡ መሣልና ፡ ብሩሾችም ፡ ፈጽሜ ፡ ስለ ፡ ረሳሁ ፡ እንደገና ፡ ስለዚሁ ፡ ሙያ ፡ አስባለሁ ፡ አላልኩም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የዳንያር ፡ ዜማ ፡ ነፍሴን ፡ ቀሰቀሳት ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ያየሁ ፡ መሰለኝ ፡ ዓለምን ፡ ግራ ፡ በገባ ፡ ሁኔታ ፡ ተመለከትሁ ፤ ፈዝዤም ፡ ነበር ።

በጃሚላስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ድንገተኛ ፡ ለውጥ ፡ ደረሰባት! ያቺ ፡ ተወዳጅ ፡ ምላስ ፡ ቀልጣፋና ፡ ሳቂታ ፡ ልጃገረድ ፡ እንዳልነበረች ፡

ሆነች ። የጠራው ፡ ፀደይ ፡ ትካዜ ፡ ጭጋጋማ ፡
ዓይኖችዋን ፡ ሸፈነው ። ወደ ፡ ጣቢያው ፡ ለመድረ
ስ ፡ ባደረግነው ፡ ረዥም ፡ ጉዞአችን ፡ ጊዜም ፡
በሀሳብ ፡ ሰጥማ ፡ ነበረች ። ያልተረጋገጠ ፡ የሕ
ልም ፡ ፈገግታም ፡ ከንፈሮችዋን ፡ ይነካው ፡ ነበር ፤
እሷ ፡ እራሷ ፡ ብቻ ፡ በተረዳችው ፡ ነገር ፡ ለስ
ላሳ ፡ ትደሰት ፡ ነበር ። ለብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከ
ባዱን ፡ ጆንያ ፡ አንስታ ፡ ከትከሻዋ ፡ ላይ ፡
አድርጋ ፡ ትቆም ፡ ነበር ። ባንድ ፡ ባልታወቀ ፡
ምክንያት ፡ በድንጋጤ ፡ ባንድ ፡ በፍጥነት ፡ እ
ንደሚወርድ ፡ አነሥተኛ ፡ ወንዝ ፡ ውስጥ ፡ እ
ንዳለች ፡ በማስመሰል ፡ ለመሻገር ፡ መቻልና ፡
አለመቻልዋን ፡ ያላወቀች ፡ መስላ ፡ ተገኘች ።
ከዳንያር ፡ ራቅ ፡ ብላ ፡ ፊቱን ፡ ለማየት ፡ አትደ
ፍርም ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ በውድማው ፡ ከሥቃይ ፡
የተነሣ ፡ ተስፋ ፡ ሊጣልበት ፡ የማይገባ ፡ የቅ
ርታ ፡ ንግግር ፡ ተናገረች ።

«ሸሚዝህን ፡ አውልቅ ፡ አጥብልሃለሁ ፡»
አለች ።

በወንዙ ፡ ካጠበችውም ፡ በኋላ ፤ ይደርቅ ፡
ዘንድ ፡ አሰጣችውና ፡ አቅራቢያው ፡ ቁጭ ፡



አለች ። የሸበሸበውንም ፡ በጥንቃቄ ፡ እየዘረ
ጋች ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ በጆንበር ፡ ትይዩ ፡ ዘር
ግታ ፡ እትከሻዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚውሉት ፡ ማለ
ቃቸውን ፡ ተረድታ ፡ ራስዋን ፡ እየነቀነ
ቀች ፡ መላልሳ ፡ በጸጥታና ፡ በትካዜ ፡ ትዳብሰ
ው ፡ ነበረች ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ጃሚላ ፡ እንደ ፡ ቀድ
ሞዋ ፡ ፈንድቃ ፡ ሳቀች ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ዓ
ይኖቿ ፡ እንደተለመደው ፡ ይቁለጨለጩ ፡ ነበር ።
ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለፍላፊዎች ፡ ወጣት ፡
ሴቶች ፡ ልጃገረዶችና ፡ ከወታደር ፡ አገልግሎት ፡
የተሰናበቱ ፡ ሰዎች ፡ ሳር ፡ ሲቆልሉ ፡ ው
ለው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ለመመለስ ፡ እግ
ረ ፡ መንገዳቸውን ፡ መጥተው ፡ ከውድማው ፡
ተገኙ ።

«ሄይ ፤ እናንት ፡ ባለ ፡ ብዙ ፡ ርስቶች ፡
ነጭ ፡ ዳቦ ፡ ለመብላት ፡ የምትፈልጉት ፡ እና
ንተ ፡ ብቻ ፡ አይደላችሁም ፡ ደህና ፡ አድርጋ
ችሁ ፡ ያዙን ፡ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ እወንዝ ፡ እ
ንጥላችኋለን ፡» ከወታደር ፡ አገልግሎት ፡ የተ
ሰናበቱትም ፡ ጮኹና ፡ መንሾቻቸውን ፡ አዙ
ረው ፡ ቀለዱ ።

«እኛን ፡ ማስፈራራት ፡ አትችሉም ፡ ለል
ጃገረዶቹ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አገኝላቸዋለሁ ፤
እናንተ ፡ ግን ፡ ለራሳችሁ ፡ ፈልጉ!» ብላ ፡ ጃሚ
ላ ፡ በደስታ ፡ መለሰችላቸው ።

«ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ከሆነም ፡ ዘንድ ፡ እን
ደገና ፡ ሁላችሁንም ፡ እንጥላችኋለን !»

ጉልማሶቹና ፡ ልጃገረዶቹ ፡ ትግል ፡ ተያ
ያዙ ። እየተሳሳቁና ፡ እያወኩ ፡ እርስ ፡ በርሳቸ
ውን ፡ ገፍትረው ፡ እውሃው ፡ ውስጥ ፡ ለመጣ
ል ፡ ሞከሩ ።

«ያዙአቸው! ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጐትትዋቸው!»
ጃሚላ ፡ ሳቀች ፤ ከሌሎቹ ፡ ይበልጥ ፡ ድምጿን ፡
ከፍ ፡ አድርጋ ፡ እየጮኸች ፡ በብልሃት ፡ ተቃ
ዋሚዎችን ፡ ታዳክም ፡ ነበረች ።

በሚያስገረም ፡ ሁኔታም ፡ የወጣቶች ፡ ዓ
ይኖች ፡ ከጃሚላ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አርፈው ፡ ነበር ።
እያንዳንዳቸውም ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ ሊይዙአት ፡
ፈቀዱ ፡ በድንገትም ፡ ሦስት ፡ ጉልማሶች ፡ አ
ፈፍ ፡ አደረጉአትና ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ወሰ
ዱአት ።

«ሳሚን ፤ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ከውኃው ፡
ውስጥ ፡ እንጥልሻለን!»



«ኑ ፡ እናወዛውዛት!» ተባባሉ ።

ጃሚላ ፡ ታገለች ፡ ተፈራገጠችም ፤ በመኻል ፡
ሳቀችና ፡ ወዳጅ ፡ ልጃገረዶች ፡ ይረዱአት ፡ ዘንድ ፡
ተጣራች ፤ እነሱ ፡ ግን ፡ ተደናግሮአቸው ፡ ከ
ወንዙ ፡ ዳር ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ይሮጡ ፡ ነበር ። ሻ
ሻቸውንም ፡ እወንዙ ፡ እየነከሩ ፡ ያወጡ ፡ ነበር ።
ወጣቶች ፡ ይስቁ ፡ ዘንድ ፡ ጃሚላ ፡ ከወንዙ ፡ ገ
ባች ። በውሃም ፡ ውስጥ ፡ ሰውነቷን ፡ በሙሉ ፡
ነከረችና ፡ ከዱሮው ፡ ይልቅ ፡ አማረች ። የራ
ሰው ፡ ከጥጥ ፡ የተሠራው ፡ ቀሚሷም ፡ ከገላ
ዋ ፡ ላይ ፡ ተለጠፈ ፤ የወጣት ፡ ክብ ፡ ዳሌዋንና ፡
ደረቷንም ፡ ይበልጥ ፡ አሳመረው ፡ እሷ ፡ ግን ፡
ምንም ፡ ነገር ፡ ልብ ፡ ሳታደርግ ፡ ሳቀች ፡ ወ
ዲህና ፡ ወዲያ ፡ ስትሮጥ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ በፊ
ቷ ፡ ላይ ፡ ይንቆረቆር ፡ ነበር ።

ወጣቶች ፡«ሳሚን ፡» እያሉ ፡ በሀሳባቸው ፡ ጸኑ ።

ጃሚላም ፡ ሳመቻቸውና ፡ ዘላ ፡ ከወንዙ ፡
ገባች ፡ እዚያም ፡ እንዳለች ፡ ሳቀች ። በውኃ ፡
ርሶ ፡ የነበረውን ፡ ጉንጉን ፡ የራስ ፡ ጸጉርም ፡
ከፊቷ ፡ ላይ ፡ ወዲያ ፡ ትረጭ ፡ ነበረች ።

በውድማው ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ በወጣ
ቶቹ ፡ ድብድብ ፡ ሳቁ ። ሽማግሌዎች ፡ እህል ፡

ወቂዎችም ፤ አካፎቻቸውን ፡ አስቀምጠው ፡ ከዓይኖቻቸው ፡ ላይ ፡ እንባቸውን ፡ ያብሱ ፡ ነበር ። በጥቁር ፡ ፊታቸው ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ያሸበሸቡት ፡ ቆዳቸው ፡ ወለል ፡ ብለው ፡ በደስታ ፡ ገጽ ፡ ታዩ ፡ የወጣቶች ፡ መንፈስ ፡ እንዲህ ፡ ታድሶ ፡ ማየታቸውም ፡ አስደስታቸው ። እኔም ፡ ደግሞ ፡ ከልብ ፡ ሳቅሁ ፤ ጀሚላን ፡ ከወጣቶች ፡ እንድጠብቃት ፡ የቆረጥኩበትን ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ፈጽሜ ፡ ረሳሁት ።

ዳንያር ፡ ብቻ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። እኔም ፡ በድንገት ፡ ልብ ፡ አደረግሁና ፡ ሳቄን ፡ አቆምሁ ። በውድማው ፡ ዳር ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ብቻውን ፡ እግሮቹን ፡ አንፈራጦና ፡ ተደላድሎ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። በበኩሌም ፡ ሮጦ ፡ ጀሚላን ፡ ከወጣቶች ፡ እጅ ፡ የሚነጥቃት ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ። አተኩሮ ፡ ተመለከታት ፤ አመለካከቱም ፡ ትካዜና ፡ አድናቆት ፡ የተቀላቀሉበት ፡ ሆኖ ፡ ደስታና ፡ ሥቃይም ፡ ጭምር ፡ ታዩበት ። የጀሚላ ፡ ቁንጅና ፡ የተድላና ፡ የትካዜ ፡ ምንጭ ፡ ሆነበት ። ወጣቶች ፡ እየተጠጓት ፡ በተራ ፡ እንድትስማቸው ፡ ባስገደድዋት ፡ ጊዜ ፤ ራሱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ ተነሥቶ ፡ የሚሄድ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ቦታ ፡ አልተላወሰም ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀሚላ ፡ ደግሞ ፡ ልብ ፡ አደረገችው ። በቅጽበት ፡ ሳቅዋን ፡ አቆመችና ፡ ራስዋን ፡ ደፋች ።

«እንግዲህ ፡ ቀልድ ፡ ይብቃ!» ብላ ፡ በድንገት ፡ ወጣቶችን ፡ አረመች ። ከእነሱ ፡ አንዱ ፡ ሊያቅፋት ፡ ሞከረ ።

«ወይድ!» ብላ ፡ ጀርባውን ፡ ገፈተረች ። በስርቆት ፡ ገጽ ፡ ዳንያርን ፡ ተመለከተችና ፡ ወደ ፡ ቁጥቋጦው ፡ ሮጣ ፡ ገብታ ፡ የራሰውን ፡ ቀሚስ ፡ ትጠመዝዝ ፡ ጀመረች ።

ስለ ፡ ግንኙነታቸውም ፡ ሳስተውለው ፡ ያልቻልኩት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነበር ፤ እውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ስፈልግም ፤ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ለማሰላሰል ፡ እፈራ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የጀሚላን ፡ ቅርታ ፡ ልብ ፡ አድርጌ ፡ ባስተዋልኩ ፡ ጊዜ ፡ እሷ ፡ ራሷ ፡ ከዳንያር ፡ ትርቅና ፡ አትጠጋውም ፡ ነበር ። እንደቀድሞ ፡ ብትስቅና ፡ ብትቀልድበት ፡ ይሻል ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በጨለማ ፡ ወደ ፡ መንደራችን ፡ ስንሄድ ፡ የዳንያር ፡ ዜማ ፡ ለሁለቱ ፡ የደስታን ፡ ምኞት ፡ አሳደረብኝ ።

በሸለቆው ፡ አቋርጠን ፡ ስንጓዝ ፡ ጀሚላ ፡ ጋሪው ፡ ተቀምጣ ፡ ትሔድ ፡ ነበር ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ግን ፡ በእግርዋ ፡ ሔደች ። እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ በጕ ኑ ፡ ተጠግቼ ፡ መጓዝን ፡ ፈቀድሁ ፡ ምክንያቱ ም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጉዞ ፡ አብረው ፡ እየተጓ ዙ ፡ ማዳመጥ ፡ የተሻለ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በመ ጀመሪያም ፡ እያንዳንዳችን ፡ የራሳችንን ፡ ጋሪ ፡ እንከተል ፡ ነበር ፤ ወዲያውኑ ፡ ሳናውቀው ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ስሜት ፡ ጐትቶ ፡ ከዳንያር ፡ ዘ ንድ ፡ ያስጠጋን ፡ ነበር ። የፊቱንና ፡ የዓይኖቹን ፡ ሁናቴ ፡ ለማየት ፡ ፈለግን ፤ ዘማሪው ፡ ያ ፡ ጭምት ፤ ሰው ፡ የማይጠጋው ፡ ዳንያር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል!

ልብ ፡ አድርጌ ፡ በተመለከትኋት ፡ ቁጥር ፡ ጀሚላ ፡ ተክዛና ፡ ፈዝዛ ፡ ትታያለች ፤ ቀስ ፡ ብ ላም ፡ እጅዋን ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ትዘረጋለች ፤ እሱ ፡ ግን ፡ አያየውም ፤ ምክንያቱም ፡ ሩቅ ፡ ስለሚመ ለከት ፡ ነው ፤ እጆቹም ፡ ከራሱ ፡ በስተኋላ ፡ ይ ወዛወዛሉ ፤ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ የጀሚላ ፡ እጅ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ከጋሪው ፡ ላይ ፡ ያርፋል ። እንደገና ፡ ደግሞ ፡ እጅዋን ፡ ትነጥቅና ፡ መ ራመዱን ፡ ታቆማለች ። እዚያም ፡ እመኻል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ፈዝዛ ፡ ትቆምና ፡ በዓይኖቿ ፡ ትመለከተዋለች ፤ ኋላም ፡ መራመድ ፡ ትጀምራ ለች ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጀሚላና ፡ እኔ ፡ ሁለታችን ም ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ በአንድ ፡ ዓይነትና ፡ ዕ ኩል ፡ በሆነ ፡ ስሜት ፡ የታወክን ፡ መሰለኝ ፡ ነበር ። በነፍሳችን ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ የነበረው ፡ ስሜት ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ይዘልቅ ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ው ፡ የደረሰ ፡ መሰለኝ ።

ጀሚላም ፡ በሥራዋ ፡ ትጠመድ ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በውድማው ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በምናደርገው ፡ ዕረፍት ፡ አታርፍም ፡ ነበር ። በእህል ፡ ወቂዎቹ ፡ አጠገብ ፡ ትቆማለች ፤ አ ንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በቀላሉ ፡ በአካፋ ፡ እህሉን ፡ ለነፋስ ፡ ትሰጣለች ፡ አካፋውን ፡ ጣል ፡ ታደ ርግና ፡ ደግሞ ፡ እገለባው ፡ ቁልል ፡ ላይ ፡ ትወ ጣለች ። እዚህም ፡ እጥላው ፡ ውስጥ ፡ ቁጭ ፡ ትልና ፡ ብቻዋን ፡ በመሆንዋ ፡ የሠጋች ፡ በመ ምሰል ፡ ትጠራኛለች ።

«ዋርሳዬ ፡ እዚህ ፡ ና ! እስቲ ፡ ለጥቂት ፡ ጊ ዜ ፡ እንረፍ ፡» ትለኛለች ።

አንድ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ታጫውተኛለች ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ አደርግ ፡ ነበር ፤ የሚያስተክ

ዛት ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ ትነግረኛለች ፡ ብዬ ፡ በጣም ፡ እናፍቅ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አላለች ። በቀስታ ፡ ራሴን ፡ ከጭንዋ ፡ ላይ ፡ አደረገችና ፡ ሩቅ ፡ ትመለከት ፡ ጀመር ። በጣቶቿ ፡ የራስ ፡ ጸጉሬን ፡ እየደባበሰች ፡ በቀስታ ፡ በሞቁና ፡ በሚንቀጠቀጡ ፡ እጆቿም ፡ ፊቴን ፡ ዳሰስ ፡ አደረገች ። ዓይኖቼን ፡ ገልጬ ፡ ቀና ፡ ብዬ ፡ ተመለከትኋት ፡ እፊቷም ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ሀሳብና ፡ ትካዜ ፡ ይታይባት ፡ ስለነበረ ፡ በእሷ ፡ ሁናቴ ፡ ራሴን ፡ ማወቅ ፡ ቻልኩ ። አንድ ፡ ነገር ፡ ያሰቃያት ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ነገርም ፡ በነፍሷ ፡ ላይ ፡ ተቆልሎና ፡ በስሎም ፡ ነበር ፤ ልውጣ ፡ እያለም ፡ ያስቸግራት ፡ ነበር ፤ እሷም ፡ ፈርታው ፡ ነበረች ። በጣም ፡ ተመኘች ፤ የምኞት ፡ ሥቃይ ፡ ተጫናት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በፍቅር ፡ ማዕበል ፡ የተዋጠች ፡ ለመሆንዋ ፡ ራሷን ፡ ማሳመን ፡ አልቻለችም ፤ በበኩሌም ፡ ዳንያርን ፡ እንድታፈቅርው ፡ አልፈልግም ፡ ነበር ፡ ምክንያቱም ፡ የወላጆቼ ፡ ምራትና ፡ የወንድሜ ፡ ባለቤት ፡ ነች ።

እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሀሳቦች ፡ ተነባብረው ፡ ሠፍረውብኝ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከአእምሮዬ ፡ አውጥቼ ፡



አባረርኋቸው ። ታላቁ ፡ ደስታዬም ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ከንፈር ፡ የተከፈሉትን ፡ ለስላሳ ፡ ከንፈሮቿንና ፡ በእንባ ፡ የተንቆረዘዙ ፡ ዓይኖቿን ፡ ማየቴ ፡ ነበር ። እንዴት ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያላትና ፡ እንዴትስ ፡ ቆንጆ ፡ ነበረች! ፊቷስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሳቢና ፡ ማራኪ ፡ ነበር! ይህ ፡ ተሰማኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ልረዳው ፡ አልቻልኩም ፡ ነበር ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ራሴን ፡ እጠይቃለሁ ፤ በአንድ ፡ ሥዕል ፡ ሳይና ፡ ባንድ ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ባለ ፡ ሙያዎች ፡ እንደሚገለጸው ፡ ሀሳብ ፡ ሁሉ ፡ ምናልባት ፡ ፍቅርም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ስሜት ፡ ያፈራል? ጃሚላን ፡ በመመልከት ፤ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሂጄ ፡ ለሰማያትና ፡ ለምድር ፡ ልጮኽላቸው ፡ ፈቀድሁ ፤ በእኔ ፡ ያደረውን ፡ ናፍቆትና ፡ የፍስሐ ፡ ፍላጐት ፡ አሸንፍ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ይሆን ፡ ብዬ ፡ ልጠይቃቸው ፡ ፈለግሁ ። አንድ ፡ ጊዜም ፡ መልሱን ፡ ያገኘሁ ፡ መሰለኝ ።

እንደ ፡ ወትሮአችን ፡ ከጣቢያው ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ በመመለስ ፡ ላይ ፡ ነበርን ። መሽቶም ፡ ነበር ፤ ከዋክብትም ፡ የንብ ፡ መንጋ ፡ መስለው ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፤ ሜዳ

ውም ፣ እንቅልፍ ፣ የወሰደው ፡ መሰለ ፤ የዳን
ያር ፡ ዜማ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ መረዋ ፡ ጸጥታው
ን ፡ እያናጋ ፡ ወደሩቁ ፡ ጨለማ ፡ ጭልጥ ፡ ይ
ል ፡ ነበር ። ጃሚላና ፡ እኔም ፡ ተከተልነው ።

በዚያች ፡ ዕለት ፡ ሌሊትም ፡ በዳንያር ፡ ም
ን ፡ እንደሆነ ፡ አላውቅም ፡ ጥልቅ ፡ ትካዜ ፡ ተሰ
ምቶት ፡ ነበር ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ የድምጹ ፡
ብቸኝነትም ፡ በዓይኖቻችን ፡ ላይ ፡ የሀዘን ፡ እ
ንባ ፡ አወረደብን ።

ጃሚላም ፡ ከጋሪው ፡ ጎን ፡ አጥብቃ ፡ ራስዋን ፡
ደፍታ ፡ የጋሪውን ፡ ጎን ፡ በመያዝ ፡ ተራመደች ።
የዳንያርም ፡ ድምጽ ፡ እንደገና ፡ ባስተጋባ ፡ ጊዜ ፡
ራስዋን ፡ ቀና ፡ አደረገችና ፡ ከጋሪው ፡ ውስጥ ፡
ዘሏ ፡ ገብታ ፡ እጎኑ ፡ ቁጭ ፡ አለች ። ከድንጋ
ይ ፡ እንደተፈጠረች ፡ መስላ ፡ ተቀመጠች ። እጆች
ዋንም ፡ እደረትዋ ፡ ላይ ፡ አስተቃቅፋቸው ፡ ነበረ
ች ። እኔም ፡ በአጠገባቸው ፡ እየተራመድሁና ፡
ልቀድማቸውም ፡ እየተጣደፍሁ ፡ በተሻለ ፡ ሁ
ናቴ ፡ ሁለቱን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ማየትን ፡
ወደድሁ ። ዳንያርም ፡ ስለ ፡ ጃሚላ ፡ እጎኑ ፡
መኖር ፡ ምንም ፡ ሳይሰማው ፡ ማዜሙን ፡ ቀጠለ ።



ክንዶቿ ፡ ሲዝሉ ፡ አየኋቸው ፡ ራሷንም ፡ በቀ
ላሉ ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ አሳረፈች ። ፈረስ ፡ የአ
ለንጋውን ፡ ግርፊያ ፡ ተከትሎ ፡ እርምጃውን ፡
እንደሚያስተካክል ፡ ሁሉ ፡ የሱም ፡ ድምጽ ፡
ለጊዜው ፡ ወለም ፡ ዘለም ፡ አለና ፡ ከበፊቱ ፡
በበለጠ ፡ ኃይል ፡ አስተጋባ ።

የሚያዜመውም ፡ የፍቅር ፡ ዜማ ፡ ነበር ።

ገረመኝ ። ሜዳው ፡ በሞላ ፡ ያበበና ፡ የጓ
ነ ፡ ጨለማንም ፡ የገፈፈ ፡ መሰለ ፤ ሁለት ፡ ፍቅ
ር ፡ ያንገላታቸውንም ፡ አየኋቸው ። አላዩኝም ፡
በጭራሽ ፡ ያልተፈጠርኩ ፡ መሰላቸው ፡ በዜ
ማው ፡ ስልት ፡ ሲንቀሳቀሱ ፡ ለማየት ፡ ከጎና
ቸው ፡ ተራመድሁ ፤ በዓለም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ረስተው ፡ ነበር ። እኔ
ም ፡ ለይቼ ፡ አላወቅኋቸውም ፡ ነበር ። ያው ፡
የምናውቀው ፡ አሮጌ ፤ አንገቱ ፡ ላይ ፡ የተቀደደ ፡
የወታደር ፡ ሸሚዝ ፡ የለበሰው ፡ ያው ፡ ዳንያር ፡
ነበር ፤ ዓይኖቹ ፡ ግን ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ያ
በሩ ፡ ነበር ። እሱን ፡ የተጠጋችውም ፡ የእኔ
ዬቱ ፡ ጃሚላ ፡ ነበረች ። እሷም ፡ ተሸንፋና ፡ ገ
ራም ፡ ሆና ፡ የእንባ ፡ ጠብታዎች ፡ እብሌኖቿ ፡
ላይ ፡ ተንቆርዝው ፡ ያብለጨልጩ ፡ ነበር ። እ

ነዚህም ፡ አዲስ ፡ የተወለዱ ፡ ሁለት ፡
ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ በመቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡
ተድላቸው ፡ ከቶ ፡ ያልተቀደመ ፡ መሰለ ። ይህ
ስ ፡ ተድላ ፡ አልነበረምን? ዳንያርስ ፡ ስለ ፡ ት
ውልድ ፡ አገሩ ፡ ያለውን ፡ የጠለቀ ፡ ፍቅር ፡
አያካፍላትም ፡ ነበር? እንደዚህ ፡ ያለውን ፡
ዜማ ፡ ለማስገኘት ፡ ስለ ፡ አበቃችው ፡ ሀገሩ ፡
አላጫወታት ፡ ይሆን? አዎ ፤ ያዜምላት ፡
ነበር ።

አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ሁል ፡ ጊዜም ፡ እንዳ
ደረገው ፡ ሁሉ ፡ የዳንያር ፡ ዜማ ፡ ቀሰቀሰኝ ፤
ተሸነፍኩም ። በድንገትም ፡ የምፈልገውን ፡
ነገር ፡ አወቅሁ ። በሥዕል ፡ ልሥላቸው ፡ ፈለ
ግሁ ።

ስለ ፡ ራሴ ፡ ሀሳብም ፡ ተሸበርኩ ፤ የሆነ ፡
ሆኖ ፡ ፍላጐቴና ፡ ምኞቴ ፡ ከፍርሃት ፡ ይበልጥ ፡
ነበር ። በደስታ ፡ ተመስጠው ፡ እንደነበሩት ፡ አ
ድርጌ ፡ እሥላቸዋለሁ ። በደስታ ፡ እንደተዋጡ ፡
አድርጌ! አዎ ፡ እዚያ ፡ እንደ ፡ ነበሩበት ፡ ሁኔ
ታ ፡ አድርጌ ፡ በትክክል ፡ እሥላለሁ ። ነገር ፡
ግን ፡ በሚገባ ፡ ልሥል ፡ እችል ፡ ይሆን? ፍርሃ
ትና ፡ ደስታ ፡ ትንፋሼን ፡ አቋረጡት ። ባንዲ



ት ፡ ቀጭን ፡ የአፋፍ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ የምሄ
ድ ፡ መሰለኝ ። ደስም ፡ ብሎኝ ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡
ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምኞቴ ፡ ለወደፊት ፡
ምን ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ እንደሚያደርስብኝ ፡ ገና ፡
አልተረዳሁም ፡ ነበር ። ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ም
ድር ፡ ሊመለከታት ፡ የሚገባው ፡ ዳንያር ፡
እንደሚያያት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አሰብኩ ።
ዜማዎቹን ፡ ለማሳየት ፡ ቀለማት ፡ ያስፈልጉኛ
ል ፡ አልኩ ። ተራራዎችና ፡ ሜዳዎችን ፡ ሰዎ
ችን ፡ ሣሮችን ፡ ደመናዎችንና ፡ ወንዞችንም ፡ እሥላ
ለሁ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ሀሳቡ ፡ በሕሊናዬ ፡ ተመላ
ለሰ ። «ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀለማትን ፡ የት ፡ አገኝ ፡ ይ
ሆን? ከትምህርት ፡ ቤትም ፡ ምንም ፡ አይሰጡ
ኝ ፡ ምክንያቱም ፡ ለራሳቸው ፡ ስለሚያስፈል
ጉአቸው ፡ ነው!» ዋናው ፡ ችግሬ ፡ ይህ ፡ እን
ደነበረ ፡ ሁሉ ፡ እኮ !

በድንገት ፡ ዳንያር ፡ ዜማውን ፡ አቋረጠ ።
ጃሚላም ፡ ፍዝዝ ፡ ብላ ፡ በእጆቿ ፡ አቀፈች
ውና ፡ ወዲያው ፡ በቅጽበት ፡ ደግሞ ፡ እጆቿን ፡
ከእሱ ፡ ላይ ፡ አነሣች ፤ ለጥቂት ፡ ጊዜም ፡ ግር ፡
አላትና ፡ ከእሱ ፡ ወዲያ ፡ ፈቀቅ ፡ አለችና ፡ ከ
ጋሪው ፡ ዘላ ፡ ወረደች ። ዳንያርም ፡ በማመን

ታት ፡ ልጓሙን ፡ ሳበ ። ፈረሶቹም ፡ ቆሙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራስዋን ፡ ቀና ፡ አደረገችና ፡ በሰያፍ ፡ ተመለከተችው ፡ በአንባዎችዋም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤

«ምን ፡ ትመለከታለህ?» ብላ ፤ ላንድ ፡ አፍታ ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ አለችና ፡ እንደገና ፡ በግልምጫ ፡ «መንገድህን ፡ ቀጥል ፡ እንጂ ፡ አትመልከተኝ!» አለችው ። ከጋሪ ፡ ላይ ፡ ወጣችና ፡ «አፍህን ፡ ከፍተህ ፡ የምትመለከተው ፡ ምንድን ፡ ነው?» ጮኸችብኝ ። «ጋሪው ፡ ላይ ፡ ውጣና ፡ ልጓሙን ፡ ያዝ! አ ፤ አበሳጨኸኝ!»

ፈረሶቹን ፡ እየመታታሁ ፡ «ምን ፡ ሆንች?» እያልኩ ፡ እገረም ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ምን ፡ እንደሆነች ፡ በመላ ፡ ለማወቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ አልነበረም ፤ በጣሙን ፡ ተበሳጭታ ፡ ነበረች ፤ ምክንያቱ ፡ ባል ፡ አግብታ ፡ ባሏ ፡ ሳራቶቭ ፡ ላይ ፡ ሀኪም ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ለማሰላሰል ፡ አልፈቀድሁም ። በእሷና ፡ በራሴ ፡ ተቆጥቼ ፡ ነበር ፤ ዳንያር ፡ ዳግም ፡ የማያዜም ፡ እንደገና ፡ ድምጹን ፡ የማልሰማ ፡ መሆኑን ፡ ባውቅ ፡ ኖሮ ፡ እጠላት ፡ ነበር ።



ሰውነቴን ፡ በሞላ ፡ ወረረኝ ፡ ተመልሼ ፡ እድርቆሹ ፡ ላይ ፡ እስክወድቅ ፡ ድረስ ፡ መቆየት ፡ አልቻልኩም ። በጨለማው ፡ ይሮጡ ፡ የነበሩ ፡ ፈረሶች ፡ ጆርባዎች ፡ ይዋልሉ ፡ ነበር ፡ ጋሪውም ፡ አለ ፡ መጠን ፡ ተንኳኳ ፡ መግቻዎቹ ፡ ልጓሞችም ፡ ከእጄ ፡ ለማምለጥ ፡ ፈለጉ ።

ከውድማው ፡ ላይ ፡ በግድ ፡ መቀነቻውን ፡ ጐትቼ ፡ ከጋሪው ፡ ሥር ፡ ጣልኩት ። እድርቆሹ ፡ ላይ ፡ እንደደርስኩ ፡ ፊልፍዬ ፡ እውስጡ ፡ ገባሁ ። በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ዳንያር ፡ ፈረሶቹን ፡ አሠማራ ።

በማግሥቱም ፡ በደስታ ፡ ከእንቅልፌ ፡ ነቃሁ ። ጃሚላንና ፡ ዳንያርን ፡ እሥላለሁ ። አጥብቄ ፡ ዓይኖቼን ፡ ጨፈንኩና ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ እንደምሥላቸው ፡ አሰብኩ ። ያስፈለገኝም ፡ ብሩሽና ፡ ቀለም ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ ባገኝ ፡ እጀምር ፡ ነበር ።

ወደ ፡ ወንዙ ፡ በሩጫ ፡ ወረድኩና ፡ ታጥቤ ፡ ወደ ፡ ታጐሩት ፡ ፈረሶች ፡ ተመልሼ ፡ መጣሁ ። ቀዝቃዛና ፡ ርጥብ ፡ ጨፌም ፡ ባዶ ፡ ቅልጥሞቼን ፡ ከፋኛ ፡ ጨረፋኝ ፡ የነቃው ፡ ጫማዬንም ፡ ለበለበኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ ተሰ

ማኝ ። ስሮጥም ፡ በአካባቢዬ ፡ ስለሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማስታወሻ ፡ ወሰድኩ ። ፀሐይም ፡ በተራራዎቹ ፡ ጀርባ ፡ በመውጣት ፡ ላይ ፡ ትገኝ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ በቦዩ ፡ አጠገብ ፡ ተዘርቶ ፡ የነበረ ፡ ሡፍ ፡ አበባ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ ፊቱን ፡ መለሰ ። ነጫጭ ፡ ጫፎች ፡ ያላቸው ፡ አበቦችም ፡ በስስት ፡ አጀቡት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጸንቶ ፡ ቆሞ ፡ የጧትን ፡ ፀሐይ ፡ ይሻማ ፡ ነበር ፤ በብጫዎቹ ፡ ምላሶቹም ፡ ይቅማቸውና ፡ የተሸከማቸውን ፡ ቅንጣቶች ፡ ይመግባቸው ፡ ነበር ። እዚያም ፡ የጋሪው ፡ መንኮራኩር ፡ ባወጣው ፡ ፈር ፡ ውሃ ፡ ተንኳለለ ፡ እዚያም ፡ ጥሩ ፡ መዓዛ ፡ ያለው ፡ የማር ፡ ቀበሌ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። የትውልድ ፡ ሀገሬን ፡ መሬት ፡ አቋርጠው ፡ ለሻገር ፡ ወፎች ፡ በላይ ፡ እየበረሩ ፡ ይሽቀዳደሙ ፡ ነበር ። አዬ! የጧትን ፡ ፀሐይ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀለማት ፡ የለበሱትን ፡ ተራራዎች ፤ ጤዛ ፡ ያዘሉትን ፡ ጨፈዎች ፡ ከቦዩ ፡ ዳር ፡ በቅሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ሡፍ ፡ አበባ ፡ ለመማረክ ፡ እንድችል ፡ ምነው ፡ ቀለማትን ፡ ባገኘሁ!

ወደ ፡ ውድማው ፡ ተመልሼ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ የነበረኝ ፡ ደስተኛ ፡ ስሜት ፡ ጨለመ ።



ጃሚላን ፡ አየኋት ። ተኮሳቁላለች ፡ ፊቷም ፡ ገርጥቷል ፡ ከዓይኖቿ ፡ ግርጌም ፡ ጥቋቁር ፡ እንደማዲያት ፡ ጥሎባት ፡ ስለነበር ፤ ምናልባት ፡ ከማሰብ ፡ የተነሣ ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይወስዳት ፡ አድራለች ። እኔን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ፈገግታ ፡ አላሳየችም ፡ ወይም ፡ አልተናገረችም ፡ ኦሮዝማት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ጃሚላ ፡ ሮጣ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ሄደችና ፡ እንዲህ ፡ አለች ፤

«አሮጌ ፡ ጋሪህን ፡ መልሰህ ፡ ውሰደው! ወደምትፈቅደው ፡ ሥፍራ ፡ ላከኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ዳግም ፡ ጣቢያው ፡ ሄጄ ፡ እህል ፡ አላስረክብም!»

«ልጄ! ምን ፡ ሆንሽ? ፈረስ ፡ የሚነክስ ፡ ዝንብ ፡ ነከሰሽን?» ብሎ ፡ በገርነት ፡ ጠየቃት ።

«የፈረስ ፡ ዝንቦች ፡ ጥዶችን ፡ ይነክሳሉ! ምክንያቱንም ፡ አትጠይቀኝ! አልሄድም ፡ ብያለሁ ፡ የምለውም ፡ ይኸኑ ፡ ብቻ ፡ ነው!» አለች ።

ከኦሮዝማት ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ ፈገግታም ፡ ጠፋ ።

«ስለምትፈልጊው ፡ ጉዳይ ፡ ግድ ፡ የለኝም! እንደተለመደው ፡ ተግባርሽን ፡ ታደርጊያለሽ!» ብሎ ፡ በምርኩዙ ፡ መሬትን ፡ ወገረ ።

«ያስቀየመሽ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ንገሪኝ ፡ ይህን ፡ ምርኩዝ ፡ እራሱ ፡ ላይ ፡ እሰብረዋለሁ! ባትነግሪኝ ፡ ግን ፡ አታቂዩኝ ፤ የምታስረክቢውም ፡ የወታደሮቹ ፡ እንጀራ ፡ ነው ፡ የገዛ ፡ ባልሽም ፡ እዚያ ፡ አለ!» ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውን ፡ ዞሮ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

ጃሚላ ፡ ተበጠበጠች ፤ ፊቷም ፡ ፍም ፡ መሰለ ፤ ዳንያርን ፡ ስትመለከትም ፡ በቀስታ ፡ ተንፈሰች ። እሱም ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ጀርባውን ፡ ጋረደላትና ፡ በመንቆራጠጥ ፡ ከፈረሱ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ማሠሪያ ፡ እየደባበሰ ፡ ቆመ ። የተለዋወጡትን ፡ ንግግር ፡ ሰምቶ ፡ ነበር ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ጃሚላ ፡ በነበረችበት ፡ ቦታ ፡ አለንጋዋን ፡ በጣቶቿ ፡ እየነካካች ፡ ቆየች ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ፈንጠር ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ጋሪው ፡ ገሠገሠች ።

ከወትሮው ፡ ይልቅ ፡ ያንለት ፡ በጊዜ ፡ ተመለስን ። ዳንያርም ፡ በመንገድ ፡ ሁሉ ፡ ፈረሶቹን ፡ አሽቀዳደመ ። ጃሚላም ፡ ከፍቶአትና ፡ ተክዛ ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ በግንባርም ፡ የተለበለበውንና ፡ የጠቆረውን ፡ ሜዳ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ዓይኖቼን ፡ ማመን ፡ አቃተኝ ። ለምን ፤ ትናንትና ፡ ልዩ ፡ ነበር ። ይህም ፡ በተረት ፡ መልክ ፡



እንደሰማሁት ፡ ሆነብኝ ። ሕሊናዬን ፡ ያንቃቃው ፡ የደስታ ፡ መልክም ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡ እንኳን ፡ አይለየኝም ። ብሩህ ፡ የሕይወት ፡ ሜፍን ፡ ጨብጫለሁ ፡ በሀሳቤም ፡ እንደገና ፡ እፈጥረዋለሁ ፡ ሀሳቤን ፡ በሞላ ፡ እስኪሸፍንብኝ ፡ ድረስ ፡ ዝርዝሩን ፡ ሁሉ ፡ እከተላለሁ ። ከመዛኝ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ያልተጻፈበት ፡ ነጭ ፡ ወረቀት ፡ ካልሰረቅሁ ፡ ፊጽሜ ፡ አላርፍም ። ሮጥኩኝና ፡ ከድርቆሹ ፡ ጀርባ ፡ ተሸሸግሁ ። እዚያም ፤ ልቤ ፡ እየመታ ፡ ባንድ ፡ እመንገድ ፡ ባገኘሁት ፡ ሳንቃ ፡ ላይ ፡ አኖርኩት ።

«የአላህ ፡ በረከት ፡ ይውረድበት!» ብዬ ፡ በዝግታ ፡ ተናገርሁ ፤ አባቴም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከፈረስ ፡ ላይ ፡ ሲያስቀምጠኝ ፡ እንደዚሁ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ በእርሳሴ ፡ ነካሁት ። እነዚህም ፡ ያልተማርኳቸው ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ መስመሮች ፡ ናቸው ። የዳንያር ፡ መልክ ፡ ከወረቀቱ ፡ ላይ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፤ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተረሳኝ ። በነሐሴ ፡ ወር ፡ ሌሊት ፡ ሜዳው ፡ ምን ፡ እንደሚመስል ፡ አሰብኩ ። ራሱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ዘንበል ፡ አድርጎ ፡ ደረቱ ፡ እራቁቱን ፡ እየታየ ፡ የዘመረው ፡

ዜማ ፡ ተሰማኝ ። አየሁትም ፤ ጀሚላም ፡ ትከሻውን ፡ ደገፍ ፡ ብላ ፡ አየኋት ። ጋሪውና ፡ ሁለታቸውም ፡ ነበሩ ፤ ከጋሪው ፡ ግንባር ፡ ላይም ፡ መሳቢያዎቹ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ነበር ። የፈረሶቹ ፡ ጀርባዎችም ፡ ይንገጫገጫሉ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ ሜዳውን ፡ የራቁት ፡ ከዋክብት ፡ ይታያሉ ።

በዚሁ ፡ ሥራዬ ፡ ተጠምጄ ፡ ስለነበር ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ልሰማ ፡ አልቻልኩም ፤ ከላዬም ፡ የሚናገር ፡ ድምጽ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤

«ደንቁረሃል?» የሚል ፡ ድምጽ ፡ ነበር ። ጀሚላ ፡ ነበረች ። ተበጠበጥኩና ፡ አፈርኩ ፤ የምንድፈውን ፡ ሥዕሌን ፡ ለማሸሸና ፡ ለመደበቅ ፡ ግን ፡ ቅልጥፍና ፡ ጐደለኝ ።

«ጋሪዎቹ ፡ ሁሉም ፡ ተጭነዋል ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ እየጮኽን ፡ ስንፈልገህ ፡ ነበርን! እዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ?» ብላ ፡ ጠየቀችና ፡ ሥዕሌን ፡ በእጅዋ ፡ አነሣች ። «ህም!» ብላ ፡ በቁጣ ፡ ተቆናጠረች ።

ሞቴንም ፡ ተመኘሁ ። ለረዥም ፡ ጊዜም ፡ ሥዕሉን ፡ ተመለከተችና ፡ በመጨረሻ ፡ በትካዜ ፡ በሞጨሞጨት ፡ ዓይኖቿ ፡ ተመለከተችኝ ።



«ለእኔ ፡ ስጠኝ ፤ ዋርሳዬ ፡ ለመታሰቢያ ፡ አስቀምጠዋለሁ ።» ስትል ፡ በዝግታ ፡ ተናገረች ፡ ወረቀቱን ፡ አጥፋ ፡ ከብብቷ ፡ ሥር ፡ ሸጐጠችው ።

እመንገድ ፡ ገብተን ፡ በጉዞ ፡ ላይ ፡ ነበርን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ አልመሰለኝም ። ያየሁትን ፡ ነገር ፡ አስመስዬ ፡ መሳሌም ፡ ሕልም ፡ መስሎ ፡ ታየኝ ። ሆኖም ፡ ከልቤ ፡ ሥር ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ የድል ፡ ማድረጌ ፡ ስሜት ፡ ታወቀኝ ። ትምክህት ፤ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ የሚበልጥ ፡ ድፍረት ፤ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ሳቢ ፡ የሆነ ፡ ሀሳብም ፡ ራሴን ፡ አሰከረው ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ሥዕሎች ፡ ለመሳል ፡ ፈቀድሁ ። እነዚህም ፡ በእርሳስ ፡ መንደፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በቀለም ፡ የሚሳሉ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ፈጣኑ ፡ አረግመዳችንም ፡ ምንም ፡ አላሰብኩም ። ፈረሶቼን ፡ ያሽቀዳድም ፡ የነበረው ፡ ዳንያር ፡ ነበር ። ጀሚላም ፡ ተከተለችው ። ዙሪያውን ፡ ትመለከት ፡ ነበር ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የሚነካ ፡ ፈገግታን ፡ ሕሊናዊ ፡ በሆነ ፡ ይዞታ ፡ ታሳያለች ። እኔም ፡ ደግሞ ፡ ጥርሶቼን ፡ ፈገግ ፡ አደረግሁ ። ምክንያቱም ፡ የእዚህ ፡ ትርጉሙ ፡ በኛ ፡

አለመቀየምዋን ፡ የሚገልጽ ፡ ነበር ፤ ብትጠይ ቀውም ፡ ዳንያር ፡ በዚያች ፡ ምሽት ፡ በደስታ ፡ ያዜምላት ፡ ነበር ።

ፈረሶቻችን ፡ በመጫኛ ፡ ቢሳቡም ፡ ቅሉ ፡ በዚያን ፡ ዕለት ፡ ከጣቢያው ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ደረስን ። ዳንያርም ፡ ማራገፍ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ተቀዳድመን ፡ ጋሪዎቹን ፡ ያዝን ። ም ን ፡ ደረሰበት? ለምንስ ፡ ተጣደፈ? አልፎ ፡ አል ፎም ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡ እየሮጠ ፡ የሚያልፈውን ፡ ባቡር ፡ ጩኸት ፡ ያዳምጣል ። ጃሚላም ፡ የእ ሱን ፡ አመለካከት ፡ ተመልክታ ፡ ምን ፡ እንደ ሚያስብ ፡ ለማወቅ ፡ ተጣጣረች ።

«ወደዚህ ፡ ና ፡ የፈረሱ ፡ ጫማ ፡ ሳልቶአ ል ። ለማውለቅ ፡ አግዘኝ ፡» ስትል ፡ ጠራችኝ ።

ዳንያርም ፡ ከኮቴው ፡ መላቀቁን ፡ በተረ ዳ ፡ ጊዜ ፡ በጉልበቶቹ ፡ መኻል ፡ ያደርግና ፡ ያ ስተካክለው ፡ ነበር ። ጃሚላም ፡ አተኩራ ፡ ዓ ይኖቹን ፡ ትመለከትና ፡ በቀስታ ፡ ትጠይቅ ፡ ነ በር ።

«ምን ፡ ሆነሃል? አታስተውልምን? ወይንስ ፡ በዓለም ፡ ያለሁት ፡ ሴት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነኝ?» አ ለችው ።



ዳንያርም ፡ አሻግሮ ፡ ተመለከተና ፡ ምን ም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ቀረ ።

«ለእኔስ ፡ ቀላል ፡ ይመስልሃል?» ብላ ፡ ተነፈሰች ።

የዳንያር ፡ ቅንድቦች ፡ ተለጠጡ ፡ በፍቅ ርና ፡ በሀዘን ፡ ተመልክቶአት ፡ እኔ ፡ ልሰማው ፡ ባልተቻለኝ ፡ ድምጽ ፡ በዝግታ ፡ ተናገራት ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጥኖ ፡ ጋሪው ፡ ሲሄድም ፡ ደ ስ ፡ ብሎት ፡ ነበር ። ሲራመድም ፡ የፈረሱን ፡ ጫ ማ ፡ በእጁ ፡ ዳሰሰው ። በጃሚላ ፡ ቃላት ፡ እን ዴት ፡ ያለ ፡ መጽናናትን ፡ ማግኘት ፡ቻለ? አን ድ ፡ ሰው ፡ «ለእኔስ ፡ ቀላል ፡ ይመስልሃል?» ብ ሎ ፡ ቢናገርና ፡ ቢተነፍስ ፤ አንድ ፡ ሌላ ፡ መጽ ናናትን ፡ ሊያገኝበት ፡ ይችላል?

አሁን ፡ ማራገፋን ፡ አብቅተን ፡ ወደ ፡ ቤታ ችን ፡ ልንመለስ ፡ ነበር ። እመንገዳችን ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ በረሃብ ፡ የጸወለገ ፡ ቁስለኛ ፡ ወታደር ፡ ወዝ ፡ የጠገበ ፡ ካፖርት ፡ ለብሶ ፡ በትክሻውም ፡ አኮፋዳ ፡ አንጠልጥሎ ፡ ከእህል ፡ ማስረከቢያ ው ፡ ጣቢያ ፡ ክልል ፡ ሲገባ ፡ አጋጠመን ። ወ ዲያውኑ ፡ አንድ ፡ ባቡር ፡ ደረሰ ። ይህ ፡ ወታ ደርም ፡ ዙሪያውን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ጮኸ ።

«ከኩርኩሬው ፡ መንደር ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡
እዚህ ፡ አለ?»
«እኔ ፡ ከኩርኩሬው ፡ መንደር ፡ ነኝ ፡» ሰ
ውዬው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ በመገረም ፡ መል
ስ ፡ ሰጠሁ ።
«የማን ፡ ልጅ ፡ ነህ?» ብሎ ፡ ወደኔ ፡ እየተ
ራመደ ፡ ወታደሩ ፡ ጠየቀ ። በድንገትም ፡ ጀሚ
ላን ፡ አያት ፡ እሷም ፡ ድንገተኛ ፡ የጥርስ ፡ ፊገ
ግታ ፡ ደስታ ፡ ፊቷን ፡ አለበሳት ።
«ከሪም? አንተ ፡ ነህ?» ብላ ፡ እንባ ፡ እያ
ነቃት ፡ ጮኸች ።
«ጀሚላ ፡ እህቴ!» አለና ፡ እጅዋን ፡ አጥብ
ቆ ፡ ጨበጣት ። ጐረቤትዋ ፡ ነበር ።
«እንዴት ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ነበር? በእርግ
ጥም ፡ እሷን ፡ መመልከቴ ፡ የዕድለኛነቴ ፡ ምል
ክቱ ፡ ነው!» ፡ ደንግጦ ፡ ተናገረ ። «ሰዲቅን ፡
ደህና ፡ ትቼው ፡ መጣሁ ። አብረን ፡ ሀኪም ፡
ቤት ፡ ነበርን ። አሳህ ፡ ቢጠብቀው ፡ ባንድና ፡
በሁለት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሀኪም ፡ ቤት ፡
ይወጣል ። እኔ ፡ ስነሳ ፡ ደብዳቤ ፡ ለሚስቱ ፡
እንዲጽፍና ፡ እንዳደርስላትም ፡ ቃል ፡ ገብቼ ፡
ስለነበረ ፤ እነሆ ፡ ተፈርሞበት ፡ የታሸገ ፡ ደብ



ዳቤ ፡ ተቀበይ!» አላትና ፡ ከሪም ፡ አንድ ፡ አን
ቮልፕ ፡ አስረከባት ።
ጀሚላም ፡ ከእጁ ፡ ነጠቀችና ፡ አፍራ ፡
ፊቷ ፡ ቀላ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፊቷን ፡ አባብሳ ፡
በስርቆሽ ፡ አመለካከት ፡ ዳንያርን ፡ ተመለከ
ተችው ። እሱም ፡ ከጋሪው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡
ይገኝ ፡ ነበር ። በውድማው ፡ ላይ ፡ አድርጐ ፡
እንደነበረው ፡ ሁሉ ፡ በዚያች ፡ ዕለትም ፡ ብቻ
ውን ፡ በጋሪ ፡ አጠገብ ፡ የቆመ ፡ ሥዕል ፡ ነበር ።
እሷን ፡ በቀጥታ ፡ እንደተመለከተም ፡ ዓይኖቹ ፡
ተስፋ ፡ የቆረጡ ፡ መሰሉ ።
በዚሁ ፡ ጊዜም ፡ ሰዎች ፡ ከያለበት ፡ ተጠ
ራቀሙ ፤ ወታደሩም ፡ ወዳጆቹንና ፡ ዘመዶቹን ፡
ከሰዎቹ ፡ መኻል ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ቻለ ፤ ብዙ ፡
ጥያቄዎችም ፡ ጐረፉለት ። ጀሚላም ፡ ስላመጣላት ፡
ደብዳቤ ፡ ለማመስገን ፡ ጊዜ ፡ ከማግኘቷ ፡ በፊት ፡
የዳንያር ፡ ጋሪ ፡ መንገጫገጭ ፡ ጀመረ ፡ ከጣ
ቢያውም ፡ ክልል ፡ ወጥቶ ፡ አቧራውን ፡ እ
የቀሰቀሰ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።
«አብዶ ፡ ይሆናል!» በማለት ፡ ሰዎቹ ፡ ጮ
ኹበት ።
እዚያ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎችም ፡ ወታደሩን ፡
ይዘውት ፡ ሄዱ ፤ ጀሚላና ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ በግቢ

ው ፡ ውስጥ ፡ ቁመን ፡ በፍጥነት ፡ የሚጠፋውን ፡ ትቢያ ፡ እንመለከት ፡ ነበርን ።

«ሙሽሪት ፡ እንሂድ» አልኳት ።

«አንተ ፡ ሂድ ፡ እኔን ፡ ግን ፡ ተወኝ!» ስትል ፡ በመመረር ፡ ተናገረች ።

እንደዚሁ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ለየብቻ ፡ ሆነን ፡ በፈረሶቻችን ፡ ወደ ፡ ቤታችን ፡ ተመለስን ። አሰቃቂው ፡ ሙቀትም ፡ ክንፈሮቼን ፡ ጠበሰኝ ። የተሰነጣጠቀችውና ፡ የተቃጠለችው ፡ ከቀኑ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ የገረጣችው ፡ ምድርም ፡ የምትበርድ ፡ መስላ ፡ ጨው ፡ የፈሰሰባቸው ፡ ግራጫ ፡ ቀለም ፡ በመሰሉ ፡ ጓሎች ፡ ተሸፍና ፡ ነበር ። ወላዋይዋና ፡ መልክ ፡ የለሽ ፡ ፀሐይም ፡ ጨው ፡ በሚመስለው ፡ ነጭ ፡ ጭጋግ ፡ ውስጥ ፡ ታበራለች ። እዚያ ፡ ከድንግዝግዙ ፡ አድማስ ፡ በላይ ፡ ቢጫማ ፡ ቀይ ፡ ደመናዎች ፡ በመጠራቀም ፡ ላይ ፡ ነበሩ ። የደረቁ ፡ ነፋስ ፡ ኃይል ፡ ደግሞ ፡ በነጭ ፡ አቧራ ፡ የፈረሶቼን ፡ አገጮች ፡ ሸፈነ ፤ ጋማቸውን ፡ እያውለበለበ ፡ አለፈ ። በኮረብታዎች ፡ የነበሩትን ፡ ቁጥቋጦች ፡ ነዳቸው ።

«ይዘንብ ፡ ይሆን?» ብዬ ፡ አሰብኩ ።



ብቸኝነት ፡ ተሰማኝ ። ጉጉም ፡ ሆንሁ! ፈረሶቼን ፡ አገሠገሥኩ ፤ እነሱም ፡ ዝግ ፡ ብለው ፡ ይራመዱ ፡ ነበር ። የከሱ ፡ ቅልጥመ ፡ ረጃጅም ፡ አሞሮችም ፡ ወደ ፡ ረባዳ ፡ ሥፍራ ፡ ተቻኩለው ፡ አመሩ ። የፀወለጉ ፡ ቅጠሎችም ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ በነፋስ ፡ ይጠረጉ ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማሮችም ፡ በኛ ፡ አገር ፡ አይበቅሉም ። ከካዛክ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ በነፋስ ፡ ኃይል ፡ የመጡ ፡ ነበሩ ። ፀሐይ ፡ ጠለቀች ። አንድም ፡ ነፍስ ፡ ለዓይን ፡ አይታይም ፡ ሙቀት ፡ ካገረጣው ፡ ሜዳ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ የለም ።

ከውድማው ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ፡ ጨልሞ ፡ ነበር ። አየሩም ፡ ነፋስ ፡ የሌለው ፡ ጸጥ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ዳንያርን ፡ ጠራሁ ።

«ወደ ፡ ወንዙ ፡ ሄዱአል ፡» ሲል ፡ ጠባቂው ፡ መለሰልኝ ። «ዝግ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደየቤቱ ፡ ሄዱአል ። ነፋስ ፡ ካልነፈሰ ፡ በቀር ፡ በውድማው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም!»

ፈረሶቼን ፡ አስማራሁና ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ለመውረድ ፡ ቁርጠኛ ፡ ሀሳብ ፡ አደረግሁ ። ከገደሉ ፡ አቅራቢያ ፡ ዳንያር ፡ የሚወዳትን ፡ ቦታ ፡ አውቅ ፡ ነበር ።

እዚያ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ከጉልበቶቹ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ከበታቹ ፡ ይወርድ ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ ያዳምጥ ፡ ነበር ። ወደ ፡ እሱ ፡ ለመጠጋት ፡ ፈቀድሁ ፤ በክንዶቹ ፡ እቅፍ ፡ አድርጌው ፡ አንድ ፡ የሚያጽናና ፡ ነገር ፡ ልናገረው ፡ ፈለግሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እችላለሁ? ራቅ ፡ ብዬ ፡ ከጎኑ ፡ ቆምኩና ፡ በመጨረሻ ፡ ትቼው ፡ ተመለስሁ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ እገለባው ፡ ላይ ፡ ተጋድሜ ፡ ቆየሁ ። እዚያ ፡ ተንጋልዬ ፡ ደመና ፡ የጋረዳትን ፡ ሰማይ ፡ እየተመለከትሁ ፡ ሕይወት ፡ የተማታና ፡ ያልተያያዘ ፡ ችግር ፡ የሚያጋጥመው ፡ ለምን ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ ለመረዳት ፡ በመገረም ፡ አሰላስል ፡ ነበር ።

ጃሚላም ፡ ገና ፡ ተመልሳ ፡ አልመጣችም ፡ ነበር ። ምን ፡ ሆና ፡ ይሆን? ልተኛ ፡ አልቻልኩም ፤ ሆኖም ፡ ታክቶኝ ፡ ነበር ። ከተራራዎቹ ፡ ከብዶ ፡ ይታይ ፡ በነበረው ፡ ደመናም ፡ መብረቅ ፡ ፈነዳ ።

ዳንያርም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ውድማው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እንቅልፍ ፡ አልወሰደኝም ፡ ነበር ። መንገዱን ፡ በዓይኑ ፡ እየጠበቀ ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ዓላማ ፡ ተንጎራደደ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አጠገቡ ፡ በነበረው ፡ ገለባ ፡ ጋደም ፡ አለ ። መንደራችንን ፡ ለቆ ፡ እንደሚሄድም ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኜ ፡ ነበር! ነገር ፡ ግን ፡ ወዴት ፡ መሄድ ፡ ይችላል? ብቸኛና ፡ መጠጊያ ፡ የሌለው ፡ ማንም ፡ የማይቆየው ፡ ሰው ፡ ነው ። ሳንቀላፋ ፡ ሳለሁም ፡ የቀረበ ፡ ጋሪ ፡ መንኰራኩር ፡ ድምጽ ፡ ሰማሁ ። ምናልባትም ፡ ጃሚላ ፡ መመለሷ ፡ ይሆናል ።

ገለባው ፡ ተንቀሳቅሶ ፡ ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ ለምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ተኝቼ ፡ እንደነበረ ፡ አላወቅሁም ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሰው ፡ አለፈ ፡ አንድ ፡ የረጠበ ፡ ክንፍም ፡ የነካኝ ፡ መሰለኝ ። ዓይኖቼን ፡ ገለጥሁ ። ጃሚላ ፡ ነበረች ። ከወንዙ ፡ ተመልሳ ፡ መምጣቷ ፡ ስለነበረ ፡ ቀሚሷ ፡ ቀዝቅዞና ፡ ለዝዞ ፡ ነበር ። ቆም ፡ ብላ ፡ በናፍቆት ፡ ሁኔታ ፡ ዙሪያዋን ፡ ከአየች ፡ በኋላ ፡ ከዳንያር ፡ ጎን ፡ ቁጭ ፡ አለች ።

«ዳንያር ፤ መጥቻለሁ ፤ እኔው ፡ ራሴ ፡ ወዳንተ ፡ መጥቻለሁ ፡» ስትል ፡ በለስላሳ ፡ ድምጽ ፡ ተናገረች ።

ማናቸው ፡ ነገር ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ምንም ፡ ድምጽ ፡ ሳይኖረው ፡ የመብረቅ ፡ አለሎ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወረደ ።

«ተቀይመሃልን? በጣም ፡ ተቀይመሃል?»

አሁንም ፡ ጸጥታ ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ የአፈር ፡ ኃል ፡ ወደ ፡ ውሃው ፡ ተንከባለለ ።

«ስሕተቴ ፡ ነው? ስሕተትህ ፡ አይደለም።»

ነጐድጓድም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ አጉረመረመ ። የጃሚላ ፡ ትርኢትም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ብልጭታ ፡ በግልጥ ፡ ታየ ። ዳንያርን ፡ ተጠማጠመች ። ትከሻዎቿም ፡ እሱን ፡ እንዳቀፈች ፡ ጐሉ ። ቀጥላም ፡ ከገለባው ፡ ላይ ፡ በጐኑ ፡ ተንጋለለች ።

ከሚዳውም ፡ ትኩስ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰ ፡ ገለባውንም ፡ አንገዋለለው ። ከውድማው ፡ ሜፍ ፡ ላይ ፡ ተክሎ ፡ የነበረውን ፡ ድንኳን ፡ ነቅሎ ፡ እንደ ፡ ዕብድ ፡ አባድሮ ፡ ነዳው ። አንድዬ ፡ ደግሞ ፡ ደረቅ ፡ ጉርምርምታ ፡ ተሰማና ፡ ሰማያውያን ፡ ብልጭታዎች ፡ ደመናውን ፡ ከፋፈሉት ። አስደንጋ ፡ ጭና ፡ አሸባሪም ፡ ነበር ። አንድ ፡ ውሽንፍር ፡ መጣ ። እሱም ፡ የበጋ ፡ ወራት ፡ የመጨረሻው ፡ ውሽንፍር ፡ ነበር ።



«ካንተ ፡ ይበልጥ ፡ እወደው ፡ ይመስልሃል?» ብላ ፡ ጃሚላ ፡ በትካዜ ፡ በቀስታ ፡ ተናገረች ። «ከቶ ፡ ካንተ ፡ ይበልጥ ፡ አልወደውም! ከቶ! ... ከቶ! እሱ ፡ አፍቅሮኝ ፡ አያውቅም ። በቁራጭ ፡ ፖስታ ፡ ሰላምታ ፡ ሰደደልኝ ። እሱን ፡ አልፈልገውም ፡ እንዲህ ፡ ዘግይቶ ፡ የመጣልኝን ፡ ፍቅሩንም ፡ አልፈልገውም ፤ ሰዎችም ፡ የፈለጉትን ፡ ይበሉ ፡ ግድ ፡ የለኝም! ፍቅሬ ፡ ሆይ ፡ አልሰድህም! ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሬ ፡ ከልብ ፡ አፍቅሬሃለሁ ። አንተን ፡ ከማወቄና ፡ ከመምጣትህ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደድሁህ ። መጣህልኝም ። አንተን ፡ እንደምጠብቅህ ም ፡ አውቀህ ፡ መጣህ።»

ጠማማ ፡ ቀላል ፡ ሰማያዊ ፡ የመብረቅ ፡ ብልጭታዎች ፡ ከገደሉ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ መቱ ። በረዶማ ፡ የዝናብ ፡ ጠብታዎችም ፡ ከገለባው ፡ ላይ ፡ ተርከፈከፉ ።

«ጃሚላ ፤ ፍቅሬ ፡ ጃሚላ!» ብሎ ፡ ዳንያር ፡ በዝግታ ፡ ተናገረ ፡ በካዛኽና ፡ ኪርጊዝ ፡ የፍቅር ፡ መግለጫዎች ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ ጠራት ። «እኔም ፡ ደግሞ ፡ ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሬ ፡ አፍቅሬሻለሁ ፤ በጦር ፡ ሜዳ ፡ እርዶች ፡ ላይ ፡ ሳለሁ ፡

ስላንቺ ፡ አልሜ ፡ ነበር ፤ ፍቅሬ ፡ ያለውም ፡ በትውልድ ፡ አገሬ ፡ መሆኑን ፡ አወቅሁ! እሱም ፡ አንቺው ፡ ነበርሽ ፡ ጃሚላ!»

«ወደኔ ፡ ዘወር ፡ በይልኝና ፡ ዓይኖችሽን ፡ ልመልከታቸው!»

ማዕበልም ፡ ተጫነን ።

የድንኳኑ ፡ ጣሪያም ፡ ከድንኳኑ ፡ ተገፎ ፡ እንደ ፡ ቆሰለች ፡ ወፍ ፡ በነፋስ ፡ ይርገበገብ ፡ ነበር ። ከታችም ፡ ዝናብ ፡ በነፋስ ፡ ኃይል ፡ መጥቶ ፡ ምድርን ፡ የሚስማት ፡ ይመስል ፡ ነበር ። የመብረቅ ፡ ጉርምርምታም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ተነዳ ። በሩሃኑ ፡ የመብረቅ ፡ ብልጭታዎች ፡ ደግሞ ፡ ተራራዎችን ፡ አበሩ ፤ ነፋሱም ፡ ተቆጥቶ ፡ ሸለቆውን ፡ ይጋረፍ ፡ ነበር ።

እኔም ፡ ከገለባው ፡ ውስጥ ፡ ተሸጉጬ ፡ ራሴን ፡ ደበቅሁ ። የገዛ ፡ ልቤም ፡ በደረቴ ፡ ያደርግ ፡ የነበረው ፡ ሩጫ ፡ ተሰማኝ ። ተደስቼ ፡ ነበር ። ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ሕመሙ ፡ አገግሞ ፡ የፀሐይን ፡ ብርሃን ፡ ለማየት ፡ እንደ ፡ በቃ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ደስታ ፡ ተሰማኝ ። ዝናቡና ፡ የመብረቅ ፡ ብልጭታዎችም ፡ ከገለባው ፡ ውስጥ ፡ እንዳለሁ ፡ ደረሱብኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ብሎኝና ፡ ተዝ



ናንቴ ፡ እገለባው ፡ ውስጥ ፡ ተኛሁ ። የሰማሁት ፡ ድምጽም ፡ የሚወርደው ፡ ዝናብ ፡ ወይም ፡ የዳንያርና ፡ ጃሚላ ፡ ሹክሹክታ ፡ መሆኑን ፡ ለይቼ ፡ ማወቅ ፡ አልቻልኩም ፡ ነበር ።

የዝናቡ ፡ ወራት ፡ መጀመሩ ፡ ነበር ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላም ፡ የበልግ ፡ ወራት ፡ ይሆናል ። የበልግ ፡ ወራት ፡ ለዛዛ ፡ ቁጥቋጦና ፡ የርጥብ ፡ ገለባ ፡ ሽታ ፡ በአየሩ ፡ ነበር ። በበልግ ፡ ወራትስ ፡ ምን ፡ ይቆየናል? የሆነው ፡ ቢሆንም ፤ ስለዚያ ፡ አላሰብኩም ።

በዚያ ፡ በበልግ ፡ ወራትም ፡ ሁለት ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ አቋርጬው ፡ የነበረውን ፡ ትምህርት ፡ ለመቀጠል ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ገበታ ፡ ተመልሼ ፡ ገባሁ ። ከትምህርት ፡ ሰዓት ፡ በኋላም ፡ አዘውትሬ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ቁልቁለት ፡ ወርጄ ፡ አሁን ፡ ባዶ ፡ ሆኖ ፡ በሚገኘው ፡ ውድማ ፡ ዳር ፡ እቀመጥ ፡ ነበር ። የመጀመሪያውን ፡ ሥዕል ፡ የነደፍኩትም ፡ እዚቹ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ሥራዬ ፡ ጥሩ ፡ አለመሆኑን ፡ ተገንዘብኩ ።

«እነዚህ ፡ ቀለማት ፡ ጥሩ ፡ አይደሉም! እውነተኛ ፡ ጥሩ ፡ ቀለም ፡ በነበረኝ!» ምንም ፡

እንኳን ፡ እውንነተኛ ፡ ቀለም ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ ባላውቅም ፡ እንዲያው ፡ እመኝ ፡ ነበር ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከአለፈ ፡ በኋላ ፡ ዘግይቼ ፡ እውነተኛ ፡ የዘይት ፡ ቀለም ፡ በቆርቆሮ ፡ ታሽጎ ፡ አየሁት ።

እንዲህ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ አስተማሪዎች ፡ ትክክለኞች ፡ መስሉኝ ። መማር ፡ አስፈልጎኝ ፡ ነበር ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሕልም ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ከወንድሞቼ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ወሬ ፡ ስላልመጣ ፤ እናቴ ፡ እኔን ፡ አንዱን ፡ ልጅዋን ፡ ሠርቼ ፡ ለሁለቱም ፡ ቤተሰቦች ፡ እንጀራ ፡ የማበረክተውን ፡ መልቀቅ ፡ አልፈቀደችም ። ስለዚሁ ፡ ጉዳይም ፡ ላማክራት ፡ አልፈቀድሁም ፡ አልደፈርኩምም ፡ ነበር ። ይህም ፡ ሳይበቃ ፡ ደግሞ ፡ የዚያ ፡ ዓመት ፡ በልግ ፡ ውብ ፡ ስለነበር ፡ ውበቱን ፡ በሥዕል ፡ ማስቀረቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ሁኖ ፡ ተሰማኝ ።

ውርጫሙ ፡ ኩርኩሬውም ፡ ባሕረ ፡ ሽሽ ፡ ሆነ ፤ በፍጥነት ፡ ከሚወርደው ፡ እንሥተኛ ፡ ውሃ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ድንጋይዎች ፡ በጥቁር ፡ አረንጓዴና ፡ በወርቅማ ፡ ቀለም ፡ የእንጨት ፡ ሽበት ፡ ተሸፍነዋል ። ለጋዎችና ፡ የተራቆቱት ፡



የጽጌረዳ ፡ ተክሎችም ፡ በማለዳው ፡ ውርጭ ፡ ቀልተው ፡ ታዩ ፡ አንዳንድ ፡ ትንንሽ ፡ ዛፎች ፡ ግን ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ጽኑና ፡ አጭር ፡ የሆኑትን ፡ ቢጫ ፡ ቅጠሎች ፡ አላራገፉም ፡ ነበር ።

ጢስ ፡ የጠገቡት ፤ ዝናብ ፡ ያራሳቸው ፡ የዕረኞቹ ፡ ድንኳኖችም ፡ ጉርፍ ፡ ሜዳውን ፡ አጥለቅልቆት ፡ ስለነበረ ፡ በወየበው ፡ ሳር ፡ ላይ ፡ ቀልተው ፡ ነበር ፤ በዝናብ ፡ የረጠቡት ፡ ጢሳማ ፡ የሆኑ ፡ የእረኞች ፡ ድንኳኖች ፡ ከቀዩ ፡ ሳር ፡ መስክ ፡ ባሻገር ፡ ጥቁር ፡ ነጠብጣብ ፡ መስለው ፡ ሲታዩ ፡ በጢስ ፡ መውጫው ፡ ቀዳዳ ፡ ደግሞ ፡ ሰማያዊ ፡ የመሰለ ፡ ጢስ ፡ እየተትጐለጐለ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። የክሱት ፡ ድንጉላ ፡ ፈረሶችም ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አሽካኩ ፤ ባዝራዎቹም ፡ ደግሞ ፡ ይፈረጥጡ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ጸደይ ፡ እመጣ ፡ ድረስ ፡ እነሱን ፡ በእርጋታ ፡ ለማገድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። ከተራራዎቹ ፡ የወረዱት ፡ የበግ ፡ መንጋዎች ፡ ደግሞ ፡ የማሳዎችን ፡ ብሮች ፡ ለዋወሱ ፡ ደረቁና ፡ የጠቆረው ፡ ሜዳ ፡ ከመረገጥ ፡ ብዛት ፡ ቀጫጭን ፡ መስቀልኛ ፡ መተላለፊያዎች ፡ ተዘርግተውበት ፡ ነበር ።

ወዲያውኑም ፡ የሚዳው ፡ ነፋስ ፡ መንፈስ ፡ ጀመረ ፤ ሰማይም ፡ ጭጋግማና ፡ በረዶ ፡ መም ጣቱን ፡ የሚያስታውቀው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ዝናብም ፡ መ ውረድ ፡ ጀመረ ። ባንዲት ፡ ውብ ፡ በሆነች ፡ ዕለ ት ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረድኩ ፤ አሻዋ ፡ ላይ ፡ በሚ በቅለው ፡ እሳታዊ ፡ የተራራ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ተማ ረክሁ ። በጽጌረዳ ፡ ተክሎች ፡ ሥር ፡ ቁጭ ፡ አልኩኝ ፤ እሱም ፡ ከወንዙ ፡ የራቀ ፡ አይደለም ። ምሽት ፡ ተቃረበ ። በድንገትም ፡ ሁለት ፡ ሰዎ ች ፡ አየሁ ። ምናልባትም ፡ ወንዙን ፡ ተሻግረ ው ፡ መጥተው ፡ ይሆናል ። እነሱም ፡ ዳንያር ና ፡ ጃሚላ ፡ ነበሩ ። ከስጋውና ፡ ቁርጠኛ ፡ ከሆ ነው ፡ ፊታቸው ፡ ላይ ፡ ዓይኔን ፡ ማንሳት ፡ አ ልቻልኩም ። ዳንያርም ፡ የወታደር ፡ ዕቃ ፡ መ ቋጠሪያ ፡ ከረጢቱን ፡ ከትከሻው ፡ ላይ ፡ አን ጠልጥሎ ፡ በፍጥነት ፡ ተራመደ ፡ የግልጥ ፡ ካ ፖርቱ ፡ ጠርዝም ፡ የእሮጌ ፡ ረዥም ፡ ጫማዎ ቹን ፡ ጫፍ ፡ መቱ ። ጃሚላ ፡ ደግሞ ፡ ነጭ ፡ የ ራስ ፡ ሻሽ ፡ ራስዋ ፡ ላይ ፡ አሥራ ፡ ነበረች ፡ ወ ደ ፡ ኋላዋም ፡ ተንሻቶባት ፡ ነበር ። ለበዓል ፡ ቀኗ ፡ የምትለብሰውን ፡ ዋናውን ፡ ቀሚስ ፡ በደንብ ፡ የተጠለፈ ፡ የሴት ፡ ኮት ፡ በላዩዋ ፡ ላይ ፡ ለብሳ ፡ ነበ



ረች ። ባንድ ፡ እጅዋ ፡ አንድ ፡ አነሥተኛ ፡ ጥቅ ል ፡ ይዛ ፡ በሌላው ፡ እጅዋ ፡ ደግሞ ፡ ከዳንያር ፡ ከረጢት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ገመድ ፡ ጨብጣለ ች ። ይነጋገሩም ፡ ነበር ።

በአንድ ፡ አነሥተኛ ፡ በሆነ ፡ ወንዝ ፡ መው ረጃ ፡ ቀጫጭን ፡ ሣር ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መተላ ለፊያዎች ፡ አቋርጠው ፡ ሽመጠጡ ። እኔም ፡ የማይርገውን ፡ እጥቼ ፡ በዓይኔ ፡ ብቻ ፡ ተጠባ በቅኋቸው ። እነሱን ፡ መጥራት ፡ ይገባኝ ፡ ነበር? ነገር ፡ ግን ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ ልተነፍ ስ ፡ አልቻልኩም ።

የመጨረሻዎቹ ፡ ቀያይ ፡ ጨረሮችም ፡ ከ ተራራው ፡ ሸንተረር ፡ ላይ ፡ በነበረው ፡ ደመና ፡ ጠፉ ፡ ወዲያውኑም ፡ መጨለም ፡ ጀመረ ።

ዳንያርና ፡ ጃሚላ ፡ ወደ ፡ ሀዲዱ ፡ መን ገድ ፡ ጐን ፡ ሲጓዙ ፡ ላንድ ፡ ጊዜም ፡ እንኳ ን ፡ ፊታቸውን ፡ ዘወር ፡ አላደረጉም ፡ አልተ ገላመጡም ። ራሶቻቸውም ፡ በችፍኑ ፡ ቁጥቋ ጦ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከታዩ ፡ በኋ ላ ፡ አልታይ ፡ አሉ ።

«ጃሚላ-አ-አ-አ!» ብዬ ፡ ድምጼን ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ ተጣራሁ ።

«አ-አ-አ!» የሚል ፡ የጥሪዬ ፡ ማሚቶ ፡ ተመልሶ ፡ ተሰማኝ ።

የውርጭ ፡ ነጠብጣቦች ፡ እርጨታም ፡ ፊቴን ፡ መታኝ ። ልብሴም ፡ ደግሞ ፡ ራሰ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከጫማዬ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ መሬት ፡ ጐንበስ ፡ ብዬ ፡ ሳልመለከት ፡ ሮጥሁ ፤ አደናቅፎኝም ፡ ወደቅሁ ። እዚያው ፡ እንደ ፡ ወያቅሁም ፡ ራሴን ፡ ቀና ፡ ሳላደርግ ፡ ትኩሱ ፡ እንባዬ ፡ ፊቴን ፡ አለበሰኝ ፤ ከባድ ፡ ጨለማም ፡ ወርዶ ፡ ከትከሻዎቼ ፡ ላይ ፡ ያረፈ ፡ መሰለኝ ። እንደመርፌ ፡ ቀጫጭን ፡ የሆኑ ፡ ሣሮች ፡ በማዘን ፡ ዋይ ፡ ሲሉ ፡ ሰማሁ ።

«ጃሚላ! ጃሚላ!» ስል ፡ ተንሰቀሰቅሁ ።

ለእኔ ፡ ቅርብና ፡ ወዳጆቼ ፡ የነበሩትን ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ በደህና ፡ ሰንብቱ ፡ እል ፡ ነበር ። እዚያው ፡ እመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተጋድሜ ፡ ሳለ ፡ ጃሚላን ፡ የማፈቅራት ፡ ለመሆኑ ፡ ተገነዘብሁ ። አዎ ፤ የመጀመሪያዋ ፡ ፍቅሬ ፡ ነበረች ፤ የልጅነት ፡ ጊዜዬ ፡ ፍቅሬ ፡ ነበረች ።

ራሴ ፡ በራሰው ፡ ክንዴ ፡ ተሸፍኖ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጋደምሁ ፡ ቆየሁ ። ከጃሚላና ፡ ዳንያር ፡ ሌላም ፡ በደህና ፡ ሰንብት ፡ የ



ምለው ፡ ነበረኝ ፡ ልጅነቴንም ፡ በደህና ፡ ሰንብት ፡ እለው ፡ ነበር ።

በመጨረሻም ፡ በጨለማ ፡ እንደምንም ፡ ተወላግጄ ፡ እቤት ፡ ገባሁ ፡ በእጥር ፡ ግቢው ፡ ክልልም ፡ ታላቅ ፡ ረብሻ ፡ ሆኖ ፡ ርካቦች ፡ ተጋጩ ፤ ሰዎቹም ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ይጭኑ ፡ ነበር ፤ ሰካራሙ ፡ ዑስማን ፡ ደግሞ ፡ ከሰንጋው ፡ ላይ ፡ ጉፍ ፡ ብሎ ፡ የተቻለውን ፡ ያህልም ፡ በኃይል ፡ ይጮህ ፡ ነበር ።

«ያን ፡ ብራሪ ፡ ዲቃላ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ከመንደራችን ፡ ማባረር ፡ ይገባን ፡ ነበር! ለመላው ፡ ቤተሰባችን ፡ ጸጸት ፡ ሆነብን! ዓይኔን ፡ በጣልኩበት ፡ ኖሮ ፤ በቅጽበት ፡ እገድለው ፡ ነበር! በመግደሉ ፡ ቢፈረድብኝም ፡ ግድ ፡ የለኝም!

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ባለጌ ፡ ዘዋሪ ፡ ሴቶቻችንን ፡ ነጥቆ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ አልፈቅድም! ጐበዞች ፡ ሆይ ፤ አያመልጥም ፤ እጣቢያው ፡ ላይ ፡ እንይዘዋለን!» ደሜ ፡ ረጋ ፤ በየትኛው ፡ መንገድ ፡ ይሄዱ ፡ ይሆን? ባንድ ፡ ጊዜም ፡ በአውራው ፡ መንገድ ፡ ሳይሆን ፡ በአቋረጭ ፡ የማይሄዱ ፡ ለመሆናቸው ፡ እርግጠኛ ፡ ሆኜ ፤ ወደ ፡

ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገባሁና ፡ ያባቴን ፡ ከበግ ፡ ቆዳ ፡ የተሠሩ ፡ ኮት ፡ አንሥቼ ፡ አጠለቅሁና ፡ ማንም ፡ እንዳያውቀኝና ፡ እንባዬንም ፡ እንዳያይብኝ ፡ ራሴን ፡ ሸፈንኩ ፡፡

ከዚያ ፡ በኋላስ ፡ በመንደሩ ፡ ውስጥ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ወሬና ፡ ሐሜታ ፡ ሆኖ ፡ ይሆን! ሴቶቹም ፡ በጀሚላ ፡ ለመፍረድ ፡ ተሽቀዳደሙ ፡፡

«እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ትታ ፡ ደስታዋን ፡ መርገጧ ፡ ሞኝነቷ ፡ ነው!»

«ወደ ፡ እሱ ፡ የሳባት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ይገርመኛል!»

«አታስቢ ፤ ቆንጆዋ ፡ ልጅ ፡ አእምሮዋን ፡ መልሳ ፡ ትገዛለች ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጊዜው ፡ ያለፈ ፡ ይሆንባታል ፡፡»

«የምለውም ፡ ይኸኑ ፡ ነው! ሰዲቅስ ፡ ምን ፡ ይጐድለዋል? ደግ ፡ ባልና ፡ ትዳሩንስ ፡ አክባሪ ፡ አይደለም? ስለምን ፤ በመንደሩ ፡ ካሉት ፡ ባለ ፡ ትዳሮች ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ አያንስም!»

የቀድሞይቱን ፡ ዋርሳዬን ፡ (ዲጅን፡) ያልፈረድኩባት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ነበርኩ ፡፡



ዳንያር ፡ በነፍሱ ፡ ከሁላችንም ፡ ይበልጥ ፡ ሀብታም ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አውቄ ፡ ነበር ፡፡ ጀሚላም ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ ብትኖር ፡ አትደሰትም ፡ ብዬ ፡ ላምን ፡ አልቻልኩም ፡፡ ለእናቴ ፡ ብቻ ፡ አዘንኩላት ፤ ጀሚላ ፡ ትታት ፡ በሄደች ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞው ፡ ብርታትዋ ፡ ከዳት ፡፡ ተዳክማና ፡ ተኰሳቁላ ፡ ነበረች ፤ ዕድል ፡ የቀድሞውን ፡ ልማድ ፡ ሁሉ ፡ ሰብሮ ፡ እንደሚጥለው ፡ ለመቀበል ፡ አለመቻሏን ፡ አሁን ፡ ተገነዘብኩ ፡፡

አንድ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍም ፡ በማዕበል ፡ ከተመነገለ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ቀና ፡ አይልም ፡፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከመርፌ ፡ ክር ፡ ያስገባላት ፡ ዘንድ ፡ የእናቴ ፡ ትምክህት ፡ አይፈቅድም ፡ ነበር ፡፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ተመልሼ ፡ እቤት ፡ እንደገባሁ ፡ የመርፌዩቱን ፡ ቀዳዳ ፡ አረጋግጣ ፡ ማየት ፡ አቅቷት ፡ እጆቿ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ስታለቅስ ፡ አየሁ ፡፡

«እንካ ፤ ክሩን ፡ አስገባልኝ ፡፡» ስትል ፡ ተናገረችና ፡ በኃይል ፡ ተነፈሰች ፡፡

«ጀሚላ ፡ መልካም ፡ ፍጻሜን ፡ አታገኝም ፡ አይቀናትም ፤ አዬ! እንዴት ፡ ያለች ፡ ቤት ፡

ጠባቂ ፡ በሆነች! አሁን ፡ ግን ፡ የለችም ፤ ሄዳለች ። እኛን ፡ ናቀችን ።

ለምን ፡ ሄደች? እዚህስ ፡ ሳይመቻት ፡ ቀርቶ ፡ ይሆን?»

እናቴን ፡ አቅፌ ፡ በእውነቱ ፡ ዳንያር ፡ ምን ፡ መሳይ ፡ ሰው ፡ እንደነበረ ፡ አረጋግጬ ፡ ልገልጽላትና ፡ ልነግራት ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይበልጥ ፡ አዋርዳታለሁ ፡ በማለት ፡ ልነግራት ፡ ሳልደፍር ፡ ቀረሁ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በበኩሌ ፡ የፈጸምኩት ፡ መልካሙ ፡ ክፍል ፡ ምሥጢር ፡ መሆኑ ፡ ቀረ ።

ወዲያውኑም ፡ ሰዲቅ ፡ ተመልሶ ፡ መጣ ። በእውነትም ፡ ተክዞ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ነገር ፡ ጠጥቶ ፡ ሞቅ ፡ ሲለው ፡ ግን ፡ ዑስማንን ፡ እንዲህ ፡ ይለው ፡ ነበር ፤

«ከሄደች ፡ መልካም ፡ መገላገል ፡ ነው! አንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ትወድቃለች ። በቂ ፡ ሴቶች ፡ በዙሪያችን ፡ ይገኛሉ ። ወርቃዊ ፡ ጸጉር ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ እንኳን ፡ ብትሆን ፡ ያንደ ፡ ወራዳ ፡ ሰው ፡ ያህል ፡ ዋጋ ፡ የላትም ።»



«እርግጥ!» ብሎ ፡ ዑስማን ፡ መለሰለት ። «እሱን ፡ ሳልይዘው ፡ በመቅረቴ ፡ ብቻ ፡ አዝናለሁ ፤ ምክንያቱም ፡ ብይዘው ፡ ኑሮ ፡ ወዲያውኑ ፡ እገድለው ፡ ነበር ። ስለ ፡ እሷ ፡ ግን ፡ ጸጉርዋን ፡ ከፈረሴ ፡ ጅራት ፡ ላይ ፡ አብተው ፡ ነበር! ምናልባትም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አቅጣጫ ፡ ወደ ፡ ጥጥ ፡ ማሳዎች ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ካዛኽስ ፡ አምርተው ፡ ይሆናል ። በአካባቢአችን ፡ ከተልከሰከሰ ፡ ይህ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ አይደለም! ነገር ፡ ግን ፡ ሊገባኝ ፡ አልቻለም ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዴት ፡ መሆን ፡ ቻለ? ማንም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ማንስ ፡ ተጠራጠረ? ውሸት ፤ ራሷ ፡ የወጠነችው ፡ ነው! ምነው ፡ እጆቼን ፡ ባሳረፍኩባት!»

ራሴንም ፡ «እንዴት ፡ አድርጋ ፡ እመስኩ ፡ ላይ ፡ እንዳጭበረበረችህ ፡ አትዘነጋውም ። እንዴት ፡ ያለ ፡ ቀላልና ፡ ትንሽ ፡ ልብ ፡ አለህ!» እል ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እቤት ፡ ውዬ ፡ ለትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ጋዜጣ ፡ ሥዕል ፡ እሥል ፡ ነበር ። እናቴም ፡ እምድጃ ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ ትል ፡ ነበር ።

በድንገት ፡ ስዲቅ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። ወደኔ ፡ በሮጠ ፡ ጊዜ ፡ ገርጥቶና ፡ ፊቱ ፡ ተጰጥሮ ፡ አንድ ፡ ቁራጭ ፡ ወረቀት ፡ ከፊቴ ፡ ላይ ፡ ወረወረብኝ ።

«ይህን ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ?» አለ ።

ተለጕምሁ ። እሱም ፡ የመጀመሪያው ፡ ሥዕሌ ፡ ነበር ። ከዚሁ ፡ ቁራጭ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ዳንያርና ፡ ጀሚላ ፡ እኔን ፡ ሲመለከቱ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላሉ ።

«አዎን ፤ እኔ ፡ ነኝ ፡ የሳልኩት ። »

«ይህስ ፡ ማነው?» ገጹን ፡ እያሳየ ፡ ተናገረኝ ።

«ዳንያር ፡ ነው ፡» አልኩ ።

«ከሃዲ!» ብሎ ፡ ስዲቅ ፡ ጮኸብኝ ።

ሥዕሉንም ፡ ቀዳደደና ፡ ከጫማው ፡ ሥር ፡ ጥሎ ፡ ረጋገጠው ፤ በሩንም ፡ በኃይል ፡ ዘግቶብኝ ፡ ወጣ ።

እናቴም ፡ ከረዥም ፡ ጊዜ ፡ ትካዜ ፡ በኋላ ፤ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ጠየቀችኝ ፤

«ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ አውቀህ ፡ ነበር?»

«አዎ ፡ አውቅ ፡ ነበር ።»



ምድጃውን ፡ ደገፍ ፡ ብላ ፡ እኔን ፡ በንቀትና ፡ በዘለፋ ፡ ገጽ ፡ እየተመለከተች ፡ ቆመች ። እኔም ፡ «እንደገና ፡ እሥላቸዋለሁ ።» ባልኳት ፡ ጊዜ ፡ በሀዘን ፡ ራስዋን ፡ ነቀነቀች ።

እወለሉ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ የተቀዳደዱ ፡ ወረቀቶች ፡ በተመለከትሁ ፡ ጊዜ ፡ ልቤ ፡ ያፈነኝ ፡ መሰለኝ ። ከሃዲ ፡ ነው ፡ ይበሉኝ! ማንንስ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠሁ? ቤተሰቤን? ወገኔን? የሆነ ፡ ሆኖ ፡ እውነትን ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጠኋትም ፤ እውነትም ፡ የእነዚህን ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ እውነት ፡ አላስተባበልኩባቸውም ።

እናቴ ፡ ልታስተውለው ፡ ስለማትችል ፡ ይህን ፡ እንኳን ፡ ማለት ፡ አልቻልኩም ።

ማነኛውም ፡ ነገር ፡ ከዓይኖቼ ፡ ላይ ፡ ዋኘብኝ ። የወረቀት ፡ ቁርጥራጮችም ፡ ነፍስ ፡ ዘርተው ፡ እወለሉ ፡ ላይ ፡ የሚለዋወሱ ፡ መሰሉ ። ዳንያርና ፡ ጀሚላ ፡ ከወረቀቱ ፡ ላይ ፡ እኔን ፡ የሚመለከቱበት ፡ አመለካከታቸው ፤ የማይረሳ ፡ ማስታወሻ ፡ በድንገት ፡ ዳንያር ፡ በዚያች ፡ በማትረሳ ፡ ነሐሴ ፡ ወር ፡ ሌሊት ፡ ያዜማት ፡ ጣፋጭ ፡ ዜማ ፡ እንዳዲስ ፡ የምትሰማኝ ፡ መሰለኝ ። ከመንደሩ ፡ ወጥተው ፡ መሄዳቸው ፡

ሲታወስም ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንዝ ፡ ዘንድ ፡ ል
ቃወመው ፡ ያልቻልኩት ፡ ምኞት ፡ አደረብኝ ።
እነሱ ፡ እንደ ፡ ሔዱት ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ ወደ ፡
መጨረሻ ፡ ደስታ ፡ ላይ ፡ ማሳረፍ ፡ በሚችለው ፡
አስቸጋሪ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ በጽናትና ፡ በድፍረት ፡
እጓዛለሁ ።

«ለመማር ፡ ከዚህ ፡ ለቅቄ ፡ እሄዳለሁ ።
ለአባቴም ፡ ሥዕል ፡ ሳይ ፡ እሆናለሁ ፡ ብለሽ ፡
ንገሪአቸው ፡» ለእናቴ ፡ ነገርኩአት ።

ይህን ፡ ስነግራትም ፡ የምትገሥጸኝና ፡ የ
ምታለቅስ ፡ መሆንዋ ፡ ተሰማኝ ። በጦር ፡ ሜዳ ፡
ላይ ፡ የቀሩትን ፡ ወንድሞቼን ፡ እንዳዲስ ፡ አስ
ታውሳ ፡ ታለቅስብኛለች ፡ ብዬ ፡ ነበር ። ነገር ፡
ግን ፡ በነገርኳት ፡ ጊዜ ፡ ይግረሙው ፡ ብላ ፡ አ
ላለቀሰችም ። በለስላሳና ፡ በሐዘን ፡ ገጽ ፡ ብቻ ፤

«ለማድረግ ፡ የምትፈልገው ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡
ዘንድ ፡ ጫጩቶቼ ፡ ሁሉም ፡ አድገው ፡ ጠን
ካሮች ፡ ሆነዋል ፤ በፈልጉበት ፡ አቅጣጫም ፡
መብረር ፡ ችለዋል ። የቴን ፡ ያህል ፡ መብረር ፡
እንደምትችልስ ፡ እንዴት ፡ እናውቃለን? ተ
ነሣ ፡ ሂድ ። ምናልባት ፡ እውነትህ ፡ ይሆናል ፡
እዚያ ፡ ስትደርስ ፡ ደግሞ ፡ ሀሳብህን ፡ ትለው



ጥ ፡ ይሆናል ። ሥዕል ፡ መሣልና ፡ ቀለምን ፡
መለቅለቅም ፡ ሙያ ፡ አይደለም ። እንዲህ ፡ ለመ
ሆኑም ፡ ተምረህ ፡ ትደርስበታለህ ። አትርሳን ፡
ብቻ ።» አለች ።

ከዚያች ፡ ዕለት ፡ ጀምሮ ፡ ትንሿ ፡ ቤት ፡
ከኛ ፡ ተነጠለች ። ወዲያውኑም ፡ ጥናቴን ፡
ጀመርኩ ።

የታሪኩ ፡ መጨረሻም ፡ እስከዚህ ፡ ድረ
ስ ፡ ነው ። ከኪነ ፡ ጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡
ትምህርቴን ፡ አከናውኜ ፡ እንደወጣሁ ፤ በከ
ፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቼ ፡ ትምህርቴ
ን ፡ እንድቀጥል ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተሰጠ
ኝ ። እዚያም ፡ ተምሬ ፡ ተመርቄ ፡ ከወጣሁ ፡
በኋላ ፡ ለሙያ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀብዬ ፡
በሥዕል ፡ ሳይነት ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጀምሮ ፡
ሳልመው ፡ የነበረው ፡ ሕልም ፡ ከመልካም ፡
ፍጻሜ ፡ ደረሰልኝ ።

ይህን ፡ ለማስታወስም ፡ አስቸጋሪ ፡ አይ
ሆንም ። እሱም ፡ የዳንያርና ፡ የጃሚላ ፡ ሥዕል ፡
ነበር ። ከበልግ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በሜዳው ፡ አ
ቋርጠው ፡ ሲሄዱ ፡ ይታያሉ ። ከፊት ፡ ለፊታ
ቸውም ፡ ሠፊውና ፡ ብሩሁ ፡ አድማስ ፡ ይታያል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ሥዕሌ ፡ ፍጹም ፡ ሙሉ ፡ ባይ ሆንም ፡ ቅሉ ፡ ዕውቀት ፡ ከመቅጽበት ፡ ስለማይገኝና ፤ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ የኪን ፡ ጥበብ ፡ ሥራዬ ፡ ስ ለሆነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጋ ፡ እስጠዋለሁ ።

በሥራ ፡ ቅር ፡ የተሰኘሁባቸው ፡ ጊዚያ ት ፡ አሉ ። በራሴ ፡ ያልተማመንኩባቸውና ፡ ተስፋ ፡ የቆረጥሁባቸው ፡ ጊዚያትም ፡ ይገኛሉ ። በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ጊዚያትም ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ክተወዳጀው ፡ በዚሁ ፡ ሥዕል ፡ እሳብበት ፡ ነበ ር ። እሱም ፡ የዳንያርና ፡ የጀሚላ ፡ ሥዕል ፡ ነው ። እመለከታቸውና ፡ እናግራቸውም ፡ ነበርኩ ።

«አሁንስ ፡ ወዴት ፡ አላችሁ? እንዴት ፡ ያ ለ ፡ መንገድስ ፡ ትከተላላችሁ? በካዛኽስታን ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ መንገዶች ፡ አሉን ፤ ከአል ታይ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ሳይቤሪያም ፡ እንደዚ ሁ ፡ ብዙ ፡ መንገዶች ፡ ይገኛሉ! ብዙ ፡ ጉበ ዞች ፡ ሰዎችም ፡ እዚያ ፡ ይሠራሉ ። ምናልባ ት ፡ ሁለታችሁም ፡ እዚያ ፡ ትሠሩ ፡ ይሆን? የ እኔዩቱ ፡ ጀሚላ ፡ ሆይ ፤ ተገላምጠሽ ፡ ሳትመ ለከቺ ፡ ወጥተሽ ፡ ሄድሽ ። ምናልባት ፡ ታክቶ ሽ ፡ ይሆናል ፤ ምናልባትም ፡ ደግሞ ፡ በራስሽ ፡ እምነት ፡ አጥተሽ ፡ ይሆናል?



ዳንያርን ፡ ደገፍ ፡ በይና ፡ የፍቅር ፡ ዜማ ውን ፡ ስለ ፡ ምድር ፤ ስለ ፡ ሕይወት ፡ ያዚምልሽ! ሜዳውም ፡ ተቀብሎ ፡ ያሽብርቀውና ፡ መልሶ ፡ እንዲያስተጋባ ፡ ያድርገው! እስቲ ፡ ያን ፡ የነ ሐሴ ፡ ሌሊት ፡ አስታውሺ! ቀጥይ ፡ ጀሚላ ፡ ባደረግሽውም ፡ አትጸጸቺ ፤ ምክንያቱም ፡ እስ ቸጋሪውን ፡ ተድላ ፡ አግኝተሻልና!»

እነሱን ፡ ስመለከታቸው ፡ የዳንያርን ፡ ድ ምጽ ፡ እሰማለሁ ። እኔም ፡ እንድነሣ ፡ ይጠራ ኛል ፤ እንዲህም ፡ ማለት ፡ ለጉዞዬ ፡ የምሰና ዳበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ። ሜዳውን ፡ አቋርጬ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ አገሬ ፡ መንደር ፡ እሄድና ፡ እዚያ ፡ አዳዲስ ፡ ቀለሞችን ፡ አገኛ ለሁ ።

እስቲ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሥዕል ፡ ብሩሾቼ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ከዳንያር ፡ ዜማ ፡ ጋር ፡ ያዚም! እያንዳንዱ ፡ የሥዕል ፡ ብሩሾቼ ፡ እንቅስቃሴ ም ፡ ከሚመታው ፡ ከጀሚላ ፡ ልብ ፡ ጋር ፡ ያ ስተጋባ!

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የ ፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋ ጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚኽ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ትርጉም ፤ ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።

አድራሻው ፤ 21, Zubovsky Boulevard,
Moscow, USSR.